ም ዕ ራ ፍ ስ ድ ስ ት

የንግሥናዋን

አክሊል የደፋች

ቤተ ክርስቲያን

የመዋቢያ ዘመን

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን (አስቴር) የእግዚአብሔርን አላብ በመረዳት ለንጉሥ ክብር ለመኖር ንግሥት አስጢን የጣለችውን ክብር ለማንሳት አቋሟን አስተካክላለች:: ስለሆነም ንጉሡ በመታሸት ቅርጽ እንዲኖራት ወሰነ:: በሌላ አገላለፅ አስቴር እውነተኛውን አገልግሎት ለማገልገል ሁሉንም የአገልግሎት ስጠታዎች ለማስተናገድ በርዋን የከፈተች ሆነች:: ከዚህ የተነሣ ለአንድ ዓመት በመታሸት ቅርጽ እንድትይዝ ተወሰነ::

> "ሴቶቹ የቀኑጅና ክብካቤ እየተደረገላቸው የሚቆዩት አስከ አንድ ዓመት ነበር÷ ይኸውም የሰውነታቸው ቅርጽ እንዲስተካከል ለመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት በከርቤና በዘይት እንደገና ለቀሪዎቹ ስድስት ወራት ባልሳም በተባለ ጣፋጭ ሽቶ ይታሻሉ ..."(አስቴ 2÷12)

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን (አስቴር) በመጀመሪያ ለስድስት ወራት ያህል <u>በከርቤና በዘይት</u> ታሸች:: ከርቤ በበረሃ የሚበቅል መራራ ሙጫ ነው ነገር ግን ሽቶነት አለው:: እንግዲህ አስቴር ቅርጽ እንዲኖራት ከምትታሸበት አንዱ ነገር <u>ከርቤ</u> ነው:: ብዙ ክርስቲያኖች ቀንበር የሚሰብረውን የመንፈስ ቅዱስን ቅባት ይፈልጋሉ:: በዘይቱ ብቻ ነው መታሸት የሚወዱት ከርቤው እንዲነካቸው አይፈልጉም ምክንያቱም መራራ ስለሆነ ነው:: ከርቤ የሚመሰለው በውስጣዊ ጥንካሬ ነው:: አዚህ ላይ ከርቤ መራራ ስለሆነ ብዙ ሰባኪያን እንደሚሉት ውስጣዊ ጥንካሬን ለማግኘት እንደ እግዚአብሔር ቃል ባልሆነ መራራ ነገር ውስጥ ማለፍ አለብን ማለት አይደለም:: ለምሳሌ በበሽታ÷ በድኽነት÷ በጉስቁልና በተለያየ በኑሮ ውጣ ውረድ በማለፍ ውስጣዊ ጥንካሬ አይገኝም:: ውስጣዊ ጥንካሬ ማለት እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር በመኖር ማስመስከር ማለት ነው:: በእግዚአብሔር ቃል መኖር የግድ ዋጋ ያስከፍላል የምንከፍለው ዋጋ ደግሞ አንደ ከርቤ መራራና ሙጫ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ሽታው እጅግ የሚማርክና ደስ የሚያሰኝ ነው:: አገልጋዮች በቅባት ከማገልገላቸው በፊት ውስጣዊ ጥንካሬ ሊኖራቸው ያስፈልጋል:: ካለበለዚያ

የተሰጣቸውን ኃላፊነት አንደሚገባ ላይወጡት ይችላሉ:: ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብፅ ክባርነት ቤት ለማውጣት አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት በምድረ በዳ በከርቤ ለአርባ ዓመታት ውስጣዊ ጥንካሬን አግኝቶአል ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔርን ዓላማ ይዞ በምድረ በዳ በጠነከረ ሕይወት ሌሎችን በምድረ በዳ ሊመራ የቻለው:: ኢያሱም ውስጣዊ ጥንካሬ ያለው ሰው ነበር ይሀንንም ያስመሰከረው እግዚአብሔር ቀብቶት የሕዝቡ መሪ ከመሆኑ በፊት ከሙሴ ጋር በምድረ በዳ ሲያልፍ ባጋጠመው ነገር ሁሉ የአምላኩን የእግዚአብሔር ቃል እየታዘዘ በመኖሩ ነበር::

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእስራኤል ተገልጦ በቅባት ከማገልገሉ በፊት በምድረ በዳ በከርቤ በመታሸት ውስጣዊውን ጥንካሬ አሳይቶአል:: ዲያብሎስ ባቀረባቸው ፈተናዎች ሁሉ አሸናፊነቱን አስመስክሮአል:: እንዲሁም በደረሰበት መከራ ሳይናወጥ የእግዚአብሔርን ዓላማ የመስቀሉን ሥራ ፈፅሟል:: ክርስቶስ በቃልም በሥራም ብርቱ የሆነ ነቢይ ስለሆነ የተናገረውን በመኖር የሚያሳይ አንከንም ያልተገኘበት በመሆኑ መዓዛው አንደ መልካም ከርቤ ቤተ ክርስቲያንን የሚማርክ ነው::

> "ውዴ በጡቶቼ መካከል ሲያርፍ <u>መዓዛው አንደ ተቋጠረ ከርቤ ነው</u>" (መኃ. መኃ 1÷13)

ደግሞ የኖረበትንና ተፈትኖ ያለፈበትን ነገር ስለሆነ የሚናገረው ክክንፈሮቹ የሚወጣው ቃል የከርቤ መዓዛ ነበረው::

> "ከንፈሮቹ መዓዛው የሚጣፍጥ <u>የከርቤ ሽቶ</u> እንደሚያፈሱ የዱር አበባዎች ናቸው"
>
> (መኃ.መኃ 5÷13)

አንዳንድ አገልጋዮች ያልኖሩበትና ተፈትነው ያላለፉበትን ለሌሎች አድርጉ ብለው ሲናገሩ ከከንፈሮቻቸው የሚወጣው ቃል ምንም መዓዛ የሌለው ሰዎችን የማይማርክ ደረቅ ቃል ብቻ ነው:: ነገር ግን ተፈትናና ነጥራ የወጣች÷ አድርጉ ክማለትዋ በፊት ማድረግን የተለማመደችውን ውስጣዊ ጥንካሬ ያላት÷ ከንጉሡ ጋር አብራ በማላለፍ አርሱን ወደ መምሰል የደረሰችውን የአግዚአብሔር ቃል ሲመስክርላት :-

"ከምድረ በዳ የምትመጣዋ ያቺ ማን ናት ቁመትዋ እንደ ጢስ ምሰሶ ቀጥ ያለ ነው መዓዛዋም ነጋዴ እንደሚሸጠው ዕጣንና ከርቤ ደስ የሚያሰኝ ነው"

(መኃ.መኃ.3÷6)

ስለዚህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን (አስቴር) በከርቤ መታሸት ውስጥ ስላለፈች ባላት እውነተኛ እግዚአብሔርን የመምሰል ኑሮ ብዙዎችን የምትማርክና አምላክዋን ደስ የምታሰኝ ናት:: ይህ ብቻ አይደለም በዘይትና ባልሳም በተባለ ጣፋጭ ሽቶ ትታሻለች ከዚህ የተነሣ አስቴር የሚጎድላት ነገር አይኖርም::

1. በከርቤ በመታሸት
   --> እውነተኛ የክርስትና ኑሮ ትኖራለች::
2. በዘይት በመታሸት
   --> ቀንበርን ሁሉ ትሰብራለች ::
3. በጣፋጭ ሽቶ በመታሸት
   --> በመልካም መዓዛዋ ብዙዎችን ትጠራለች ::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የንግሥናዋን ዘውድ በራስዋ ላይ ከመድፋትዋ በፊት ቅርጽ የሚሰጥዋት ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌላውያን፥ እረኞችና አስተማሪዎች በከርቤና በዘይት እንዲሁም በጣፋጭ ሽቶ በመታሸት ዘመን ያለፉ እውነተኛ አገልጋዮች በመሆን የመጨረሻውን የወንጌል አገልግሎት የሚያገለግሉ ናቸው ::

በአስቴር ምዕራፍ ሁለት ቁጥር አሥራ ሁለት መጨረሻ አካባቢ የእግዚአብሔር ቃል ሲነግረን "ከዚያም በኋላ..." የሚል ቃል እናገኛለን "ከዚያም በኋላ" የሚለው ቃል አስቴር መታሸት ባለባት ነገር ሁሉ ከታሸች በኋላ በከርቤ፥ በዘይት፥ በጣፋጭ ሽቶ ካለፈች በኋላ ወደ ንጉሥ እንድትገባ ይደረጋል ::

በምዕራፍ ሁለት ቁጥር አሥራ አምስት መጀመሪያ ላይ ደግሞ "በዚህ ዓይነት" የሚል ቃል እናገኛለን አስቴር ታሽታ ቅርጽ በያዘችበት ዓይነት፤ የአምስቱ የአገልግሎት ስጦታ ባለቤት በሆነችበት ዓይነት፤ የሰውነትዋ ቅርጽ በጣም ሰዎችን በሚማርክበት ዓይነት ወደንጉሡ የምትገባበት ጊዜ ደረሰ::

አስቴርን አሁንም ከሌሎች ለየት የሚያደርጋት ወደ ንጉሡ ስትቀርብ እራሴ ይሰማማኛል ወይንም ንጉሡን እማርክበታለሁ፥ደስ ያሰኘዋል ብላ ያሰበችውን ከራስዋ አመለካከት ያፈለቀችውን ልብስ ሳይሆን ከእርስዋ አመለካከትና ምርጫ ውጭ የሆነውን ልብሰ ነበር የለበሰችው::

"…. እርስዋም ወደ ንጉሡ የመቅረብ ተራዋ በደረሰ ጊዜ የለበሰችው የምርጥ ሴቶች መኖሪያ ቤት ኃላፊ የነበረው ኛንደረባው ሄጋይ እንድትለብስ በመከራት መሠረት ነበር::"

(አስቴ 2÷15)

እዚህ ላይ ኛንደረባው የመልእክ ምላሌ ነው ይህንንም በሚቀጥሉት ምዕራፎች ላይ እናየዋለን:: አስቴር ከንጉሡ ተልኮ በመጣው ኛንደረባ በተነገራት መሠረት ልክ እንደ ቆርኔሌዎስ የመላእክትን አገልግሎት የተቀበለች ናት:: ስለዚህ ከሰማይ በመጣው ምሪት ንጉሡ የሚፈልገውን ልብስ የለበሰች ናት:: አስቴር የራስዋን አመለካከት አሽቀንጥራ የጣለች በሰማያዊው አሳብ ብቻ የምትጓዝ ነች::

ስለዚህ ቁመናዋ እጅግ ያማረ፥ ቅርጿ በመታሸት የተስተካከለ፥ ብዙ ሰዎችን የምትማርክ፥ ጥሩ የሆነውን ሰማያዊ ምግብ በመመገብ ውበት የፈሰሰባት፤ ከዚህም እልፋ ከሰማይ በመጣው ድምፅ በተመረጠላት ልብሰ እጅግ ማራኪ ሆና እሽብርቃና ደምቃ ልዩ ውበት ኖሯት ወደ ንጉሡ በተራዋ ስትገባ የንጉሡን ዓይኖች በተለየ ሁኔታ ማረከች:: ንጉሡም እንዲህ በማለት መለሰላት:-

"ውዴ ሆይ! እንደ ቲርጻ ከተማ የተዋብሽ ነሽ
እንደ ኢየሩሳሌምም እጅግ ያማርሽ ነሽ
የጦር ዓርማ ይዞ እንደሚጓዝ ሠራዊት
የሚያሰፈራ ግርማ አለሽ
እባክሽ ዓይኖችሽን ከእኔ ላይ አንሺ
ምክንያቱም እነሱ እኔን ማርከው
አስረኛ አድርገውኛል "

(መኃ.መኃ 6÷4-5)

ወደ ሱሳ ከተማ ለንጉሡ ተመርጠው የመጡ ብዙ ልጃገረዶች ቢኖሩም ነገር ግን በተለየ ሁኔታ የንጉሡን ዓይኖች የማረከችው አስቴር ብቻ

ነበረች:: ከውበትዋ ማራኪነት የተነሣ ከሌሎቹ ልጃገረዶች አብልጦ ወደዳት ቃሉም ሲገልጽልን :-

"ንጉሡም ከሌሎቹ ልጃገረዶች ሁሉ አስበልጦ ወደዳት፤ ከሌሎቹ ሁሉ ይበልጥ በፊቱ ተቀባይነትና መወደድን አገኘች..." (አስቴ 2÷17)

በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔር ቃል በመኃልየ መኃልይ ላይ ንጉሡ ሲመለክርላት:-

"ሰልሳ ነገሥታት÷ ሰማንያም ቁባቶችና ስፍር
ቁጥር የሌላቸው ቈነጃጅት አሉኝ
እኔ ግን የምወደው አንዲትዋን ብቻ ነው
እርስዋም ምንም እንከን የሌለባት
እንደ ርግብ የተዋበች ናት..."
(መኃ.መኃ6÷8-9)

አስቴር የእግዚአብሔርን ዓላማ ይዛ የተነሣች የዘመኑን የእግዚአብሔር ዕቅድ የተረዳች እራስዋን ለአምላክዋ የቀደሰች ስለሆነች በቤተ መንግሥት ውስጥ ካሉ ብዙ ልጃገረዶች መካከል የንጉሡን የክብር አገልግሎት እንድታገለግል የንጉሡ ዓይኖች በተለየ ሁኔታ ለተለየና ድንቅ ለሆነ ዓላማ በእርስዋ ላይ ዐረፉ:: ከዚህ የተነሣ ንግሥት አስጢን እምቢ ብላ የገፋችውን አሳታሚዊ ነፀብራቅ የሚያወጣውን÷ መንፈሳዊ ብርሃን የሚፈነጥቀውን÷ ጠላቶችዋን እንደ ንግሥት የምትገዛበትን "...መንግሥታዊውን ዘውድ አንሥቶ በራስዋ ላይ ደፋላትና በአስጢን ቦታ አነገሣት" (አስቴ 2÷17)

የቤተ መንግሥቱ ነዋሪዎች

እዚህ ላይ ከላይ ያየነውን አሳብ ሳንለቅ አንድ ትልቅ ነገር እንመለከታለን:: ይህም ከንግሥት አስጢን እምቢታ በኋላ በሱሳ ከተማ ወዳለው ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ተፈልገው ብዙ ልጃገረዶች የመጡ ሲሆን ሁሉም ተራቸው ሲደርስ ከምርጥ ሴቶች መኖሪያ ወጥተው ወደ ንጉሡ በሚገቡበት ጊዜ የፈለጉትን ልብስ መርጠው መልበስ ይችሉ

ነበር:: ከዚያም ወደ ንጉሡ ቀርበው ንጉሡን ካልማረኩት የቤተ መንግሥቱ ነዋሪዎች ብቻ ይሆናሉ::

አስቴር ወደ ንጉሡ ለትቀርብ ከሰማይ በመጣው ትእዛዝ ነበር ለንጉሡ ክብር የለበለችው:: ሌሎች ልጃገረዶች ግን ወደ ንጉሡ ሲቀርቡ ለራሳቸው ይስማማናል ያሉትን ንጉሡን እንማርከበታለን ብለው ያሰቡትን ከራሳቸው አመለካከት ያፈለቁትን ልብስ ለብሰው ነበር ወደ ንጉሡ የገቡት:: እነኚህ ልጃገረዶች ንግሥት አስጢን በራስዋ አመለካከት በወይዛዝርት መካከል ለመከበር ፈልጋ ከክብር የጎደለች እንደሆነች ያላስተዋሉ ነበሩ:: በተመሳሳይ ሁኔታም ባለንበት ዘመን ንጉሡ እንዲከብርባቸው ወደ ንጉሡ ራሳቸውን የሚያቀርቡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ወደ ንጉሡ የሚቀርቡት ግን በራሳቸው ልብስ ነው ይኸውም በራሳቸው አመለካከት÷ ወግና ሥርዓት÷ ሰማያዊ ሳይሆን ምድራዊ በሆነ ጥበብ ንጉሡ እንዲከብርባቸው የሚፈልጉ ከራሳቸው የአለባበስ ልምድ መላቀቅ የማይፈልጉ ናቸው:: እንደነዚህ ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት የንጉሡን ዓይኖች ስለማይማርኩት የክብሩ መግለጫ ሳይሆኑ የቤተ መንግሥት ነዋሪዎች ብቻ ይሆናሉ:: ማለትም በጌታ ድነዋል የዘላለም ሕይወት አላቸው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ቢሆኑም ከዚህ በላይ ማለፍን አይፈልጉም፤ የራሳቸውን ነገር መጣል ስለማይፈልጉ የቤተ መንግሥቱ ነዋሪዎች ብቻ እንጂ የሚሆኑት በምድር ላይ የንጉሡ ክብር መገለጫ አይሆኑም::

የእግዚአብሔር ቃል በጢሞቴዎስ መልእክት ላይ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ገልጾልናል:: አንዳንዶቹ እንደ አስቴር የንጉሡን ዐይን የማረኩ የከበረውንም አገልግሎት የሚያገለግሉ ናቸው:: አንዳንዶቹ ግን በንግሥት አስጢን አመለካከት የሚሄዱ የራሳቸውን ልብስ ያላወለቁ ነገር ግን በትልቅ ቤት ውስጥ የሚገኙ የቤተ መንግሥት ነዋሪዎች ብቻ መሆናቸውን ይገልፅልናል "በትልቅ ቤት ውስጥ ከወርቅና ከብር የተሠሩ ዕቃዎች ብቻ ሳይሆኑ ከእንጨትና ከሸክላ ዐፈር የተሠሩ ዕቃዎችም ይገኛሉ፤ ከእነርሱም አንዳንዶቹ ለተከበረ አገልግሎት÷ አንዳንዶቹም ለተዋረደ አገልግሎት ይውላሉ:: ከእነዚህ ክፉ ነገሮች ተለይቶ ንፁህ ሆኖ የሚኖር ሰው÷ ለተከበረ አገልግሎት የሚውል ዕቃ ይሆናል፤ ምክንያቱም ለማንኛውም መልካም አገልግሎት የተዘጋጀ÷ ለጌታው የተቀደሰና ጠቃሚ ዕቃ ነው::" (2ጢሞ 2÷20 -21)

እንግዲህ ምርጫችን ምን ይሆን ? እንደ አስቴር የራሳችንን ነገር ጥለን እስከ ዘውድ መጫን ድረስ መሄድ ? ወይስ ከራሳችን የአለባበስ ልምድ ሳንወጣ የቤተ መንግሥቱ ነዋሪዎች ሆኖ መገኘት ? ቃሉ "ማንም ራሱን ቢያነፃ" ይላል ይህ ማለት ፈቃደኛ ቢሆን መጣል ያለበትን ጥሎ ራሱን ለንጉሡ የክብር አገልግሎት ቢያዘጋጅ ለጌታው የሚጠቅም ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆናል:: ስለዚህም የምርጫና የውሳኔ ጉዳይ ነው:: እንግዲህ እንደ ኢያሱ የምንወስነውን ዛሬ መምረጥ ይኖርብናል !!

አስቴር ማን ናት ?

ለዚህ ሁሉ ክብር የበቃችው አስቴር ማን ናት ? ከመጀመሪያ ሕይወትዋ ብንነሳ አስቴር እጅግ ምስኪን የነበረች÷ እናትና አባትዋ የሞቱባት÷ አሳዳጊ አጥታ የምትንከራተት÷ ምንም ደራሽና ረዳት የሌላት÷ በእናትና በአባትዋ ሞት ምክንያት በመራራ ሀዘን የተሞላች፤ ምንም ተስፋ የምታደርግበት ነገር የሌላት ተንከራታች ልጃገረድ ነበረች:: እንኳን ለንጉሡ ክብር ለመኖር ልትታጭ ቀርቶ እናትና አባት ስለሌላት በወግና በማዕረግ ልትዳር ስለማትችል ዞር ብሎ የሚያያት ፈላጊ የሌላት ወደ ግራም ወደ ቀኝም ዓይኖችዋን የምታነሳበት የሌላት አሳዛኝና ምስኪን ልጃገረድ ነበረች::

የሚረዳት ባልነበረ ጊዜ ለእርስዋ በተለየና በተባረከው ቀን የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በሆነው በመርዶክዮስ አማካኝነት ድንገተኛ ጥሪ ደርሷት ወደ ሱሳ ከመጡት ብዙ ልጃገረዶች መካከል አንዷ ሆነች:: ለእርስዋ ይህ ሁኔታ በጣም አስገራሚና አስደናቂ ጥሪ ነበር:: ማንም የማያስባትን ምስኪን ሴት ከዓመድ ከትቢያ ላይ አንስቶ በንጉሥ ቤተ መንግሥት መገኘትን ደጋግማ የምታስበውና ራስዋን የምትጠይቅበት ጉዳይ ነበር:: ለዚህ ጥያቄዋ ወደ ውስጥዋ የሚፈሱ ምላሾች ነበርዋት እንዲህ የሚል:-

> "እግዚአብሔር ጥበበኞችን ለማሳፈር በዓለም እንደ ሞኞች የሚቆጠሩትን ሰዎች መረጠ፤ ብርቱዎችንም ለማሳፈር በዓለም እንደ ደካሞች የሚቆጠሩትን መረጠ፤ በዓለም ሰዎች ዘንድ ክቡር ሆኖ የሚታየውን ነገር ለማጥፋት÷ በዓለም የተዋረደና የተናቀ ከንቱም መስሎ የሚታየውን ነገር መረጠ:: <u>ይህንንም ያደረገው ማንም ሰው</u>

<u>በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ ነው</u>::" (1ቆሮ 1÷27-29)

አስቴር ይህንን ጠንቅቃ በመረዳት የመጣችበትን ሳትረሳ ነገር ግን <u>"የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ"</u> የሚለው የእግዚአብሔር ቃል የሕይወትዋ ዋና መመሪያ አድርጋ ከህፃንነትዋ ጀምራ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ በሆነው በመርዶክዮስ ሥር እራስዋን አስገዝታ እየታዘዘች ያደገች ነበረች::

አሁን ግን አስቴር በሕይወትዋ ትልቅ ለውጥ የሚታይባት ሆናለች ከትቢያ ያነሳትን ጌታ በአቋም ለማገልገል የወሰነች ከአምላክዋ ጋር በመጣበቅ ሰማያዊውን ምግብ የምትመገብ በዘይትና በከርቤ በጣፋጭም ሽቶ በመታሸት ያማረችና እጅግ የተዋበች ሆናለች:: ይህም ሆኖ እንደ ንግሥት አስጢን እጅግ በተዋበችበት በእግዚአብሔር ነገር ላይ ሳይሆን ዓይኖችዋ ያረፉት <u>"የሚመካ በእግዚአብሔር ይመካ"</u> በሚለው የሕይወትዋ መመሪያ ላይ ነበር ምክንያቱም ከየት እንደተነሳችና ማን ለዚህ ክብር እንዳበቃት በሚገባ ጠንቅቃ ታውቅ ነበርና:: ከዚህም አልፎ አስቴር እንደ ቲርጻ ከተማ የተዋበች እንደ ኢየሩሳሌም እጅግ ያማረች የጦር ዓርማ ይዞ እንደሚጓዝ ሠራዊት የሚያስፈራ ግርማ ኖሯት የንጉሡን ዓይኖች ማርካ የዘውድ አክሊል ባለቤት ብትሆንም እንኳን በፍፁም ትህትናና መታዘዝ የተሞላች ነበረች::

አስቴር ዘውዷን ብትደፋም እንደ ንግሥት አስጢን መኩራራትን÷ በቃኝ ማለትን÷ የራስዋን ክብር መፈለግን በፍፁም አታውቅም ምክንያቱም ያለ ጌታ መክበር እንደሌለ ብቻዋን የተራቆተችና ለምንም ከብር የማትበቃ መሆኗን ጠንቅቃ ታውቃለች:: አንዲሁም አስቴር ገና ደህንነትን ተቀብላ ወደ ንጉሡ ቤተ መንግሥት ስትመጣ "አይሁዳዊ መሆንዋን ምስጢር አድርጋ እንድትጠብቅ" መርዶክዮስ በነገራት መሠረት እንደታዘዘችለት እንዲሁም ዘውዷን ከጫነች በኋላም ያንኑ ጥያቄ እንድትታዘዝለት በጠየቃት ጊዜ አስቴር ግን አሁንም ላዳናት ጌታ ለመታዘዝ ትሁት ነበረች:: በህፃንነት ጊዜዋ እንደታዘዘችለት ምንም ሳትለውጥ አሁንም ታዛዥ ነበረች ይህንንም ቃሉ ሲያረጋግጥልን :-

> "...አርስዋም በሕፃንነትዋ ጊዜ በአርሱም ኃላፊነት ሥር ሳለች በሁሉ ነገር ትታዘዘው እንደነበር አሁንም በዚህ ነገር ታዘዘችለት" (አስቴ 2÷20)

ብዙ አገልጋዮች እንደ ሽምበቆ ተመዘው ቶሎ ቅንጥስ የሚሉት መታዘዝን ስለማያውቁ ነው:: በተለይ ያለመታዘዝ ኃጢያት ብዙ የእግዚአብሔርን ሥራ ያበላሸና ለእግዚአብሔር ሥራ ዕንቅፋት የሚሆን ነው:: ሳኦል ለእግዚአብሔር ካለመታዘዙ የተነሣ እግዚአብሔር እርሱን በእስራኤል ላይ በማንገሡ ተፀፀተ:: እግዚአብሔር ሰዎችን ከተዋረደው ቦታ አንስቶ ማክበር የሚያውቅ አምላክ ነው ነገር ግን ሰዎች ከየት እንዳነሳቸው የረሱ ይመስላሉ ፤እግዚአብሔር ካከበራቸው በኋላ ለእርሱ ለመታዘዝ ሲያፈገፍጉ ይታያሉ:: የአገልጋይ ክብሩ ዝቅ ብሎ መታዘዙ ነው:: በተለይ በመድረክ አገልግሎት የሚያገለግሉ የቃል ሰዎች ብቻ እንዳይሆኑ በጣም መጠንቀቅ አለባቸው:: ጌታን ሲቀበሉ የነበራቸው ታዛዥነት እስከ መጨረሻ ሊዘልቅ ይገባል:: አንዳንድ አገልጋዮች ሁል ጊዜ ማዘዝን እንጂ መታዘዝን አይወዱም፤ በክበሬታ ስፍራ መገኘትን እንጂ በዝቅተኛ ቦታ ተገኝተው በመታዘዝ ማገልገልን አይፈልጉም፤ባለመታዘዝ አመፀኝነት የተያዙ ናቸው::እግዚአብሔር በትንሹም በትልቁም ነገር በትህትና የሚታዘዙለትን ሰዎች ይፈልጋል::

በተለይ የመንፈስ ቅዱስ የተሐድሶ ሥራ ባለበት ባሁኑ ዘመን ለእውነተኛው የእግዚአብሔር አሳብ የማይታዘዙ፤ አሁን ያሉበትን መንፈሳዊ ደረጃ ብቻ በመመልከት የተኩራሩ ሊመጣ ላለው ታላቅ የቤተ ክርስቲያን የክብር አገልግሎት ባለመታዘዝ ተይዘው እራሳቸውን ያላዘጋጁ ባሉበት ብቻ መሄድን የሚፈልጉ፤ ልባቸው እውነትን እያወቀ ባለመታዘዝ እልህ የተያዙ በዐማሌቅ ሠንጋ የተማረኩ አገልጋዮች የሚጠብቃቸው ነገር ቢኖር እንደ ሳኦል በእግዚአብሔር መናቅ ነው:: አስቴር ግን በሕፃንነትዋ የነበራት ታዛዥነት አሁንም ዘውዷን ስትደፋ አልተለወጠም ጌታዋን በሁሉም ነገር ትታዘዘው ነበር::

ስለሆነም እንደ አስቴር በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በታላቅ ቅባት በጉባኤ ላይ ለማገልገል የሚታዘዙ እንዲሁም እግዚአብሔር የቀባኝ ነኝ ብለው ሳይኩራሩ ቤት እስከ መጥረግ እንኳን ዝቅ ለማለት ወገባቸው ባለ መታዘዝ ኃጢያት ባልደረቀ የጌታን ምሳሌ በሚከተሉ አገልጋዮች የተዋበች ናት::

አንተስ ማን ነህ ?

አስቴር ማን ናት ለሚለው ጥያቄ መልሱ ትሁትና ታዛዥ ነበረች ብቻ አይደለም:: በአስቴር የምትመሰለዋ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደ ሲሞን ያሉ አስመሳይ አገልጋዮችን እየበረበሩ የሚያወጡ ሐዋርያት፤ ቤተ ክርስቲያን በትክክል እንድትታነፅ ሁሉን በየስፍራው በማስቀመጥ መነቀል የሚገባውን በመንቀል የእግዚአብሔርን አሳብ በመትከል የሚናገሩ ነቢያትን፤ ወንጌልን ለፍጥረት ለመስበክ በማስመሰል ሳይሆን በትክክል የተቀቡ ወንጌላውያን፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር የልቡን አሳብ በመግለጥ የተሰጣቸውን ቦታ አውቀው ሕዝቡን በትክክል የሚመሩ እረኞችና የተሰወረውን ምስጢር በመግለጥ የዘመኑን የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ናት:: እነኚህ አገልጋዮች እጅግ ትሁትና ታዛዥ የሆኑ ከዚያም አልፈው ዘውድን የደፉ ናቸው::

እነዚህን አገልጋዮች ያቀፈች ቤተ ክርስቲያን እንዴት ንፅህት፥ ቅድስት፥ ያለ ነውር ሆና ዕድፈትና የፊት መጨማደድ የሌለባት፤ ለሙሽራው ሠርግ ቀን የተዘጋጀች፤ የጌታዋን መምጣት በጉጉት የምትጠባበቅ በእግዚአብሔር ክብር የተሞላች እንደምትሆን ማንም ሰው መገመት ይችላል::

በማስተዋል ለአንድ አፍታ እስኪ እናስብ የምናመልክባት ቤተ ክርስቲያን የት ደረጃ ላይ ደርሳለች ? የሚያገለግሉህ አገልጋዮች የት ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው ? አገልጋይስ ከሆንክ ደግሞ በምን ዓይነት ክብር ነው እያገለገልክ ያለኸው ? ለታላቁ የጌታ ቀን እየተዘጋጀች ያለች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለህ ይመስልሃል ወይ ? መልሱ አይመስለኝም ከሆነ መፍትሔው እውነትን በመረዳት ባለህበት ምድርና በአጥቢያህ ቤተ ክርስቲያንህ ታላቅ መነቃቃት እንዲነሳና ለጌታ ቀን በንጥቀት መንፈስ ውስጥ እንድትሆን ሙሉ ሰው ሊያደርጉህ የሚችሉትን እውነተኛ ስጦታ ያላቸውንና የተቀቡ አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ዘንድ እንዲሰጡህ ከአሁኑ ያለ ማቋረጥ መፀለይ እንደሚኖርብህ አትዘንጋ::

ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ያለ አምስቱ የአገልግሎት ስጦታ ወደ ፍፁምና ሙሉ ሰው ወደ መሆን አትደርስም:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የንግሥናዋን ዘውድ ደፍታ በክፍታ ላይ እንድትሄድ የሚያደርጓት እነኚህ

ስጦታዎች ናቸው:: ያለ እነኚህ ስጦታዎች ጠላቶችዋን ሙሉ በሙሉ መርገጥ አትችልም:: ስለዚህ ያለህበትን ሁኔታ ነቅተህ በመረዳት አስቴር ማን መሆንዋን ከገባህ እንደ አስቴር ራስህን ለንጉሡ ማዘጋጀት እንዳለብህ አትዘንጋ::

አስቴር በራስዋ ላይ ዘውዱን ከደፋች በኋላ ንጉሡ ለአለቆችና ለሥልጣናት እንድትታይ ስለ አስቴር ታላቅ ግብዣን አዘጋጀ::

> "ከዚህ በኋላ ንጉሡ ስለ አስቴር ክብር ታላቅ ግብዣ አዘጋጅቶ ባለሟሎቹ የሆኑትን ባለሥልጣኖችና አስተዳዳሪዎች ሁሉ ጠራ፤ በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት በሚገኙት አገሮች ሁሉ የደስታ በዓል እንዲደረግ ዐወጀ፤ ልግስና የተሞላበት ንጉሣዊ ስጦታም አደረገ::" (አስቴ 2÷18)

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በራስዋ ላይ ከደፋችው መንፈሳዊ ዘውድ የተነሣ የሰይጣንን አራስ የምትቀጠቅጥበት የግብዣ ዘመን ታሳልፋለች:: በዚህም የግብዣ ዘመንዋ ለብዙ ሰዎች ታላቅና አስደናቂ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የምታገለግል ትሆናለች:: ከዚህም መንፈሳዊ ዘውድ የእግዚአብሔር አሳታሚዊ የሆነ ጨረር ስለሚፈነጥቅ በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ፊት የሚቆም ምንም ዓይነት ኃይል የለም:: ስለዚህም ነው ዘውዷን ከደፋች በኋላ ንጉሡ ግብዣን አዘጋጅቶ ለአለቅነትና ለሥልጣናት በከፍታው ላይ እያስኬደ የሚያሳያት:: በተለይ ከአሁን በኋላ ባለው ጽሑፍ የምናየው የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ዘውድ ከደፋች በኋላ የምታገለግለውን አገልግሎት ይሆናል::

ምዕራፍ ሰባት

የሃማን

በጠላትነት

መነሣት

የሃማን በጠላትነት መነሣት

ሃማን የሰይጣን ምሳሌ እንደሆነና የዐማሌቅ መንፈስን የሚወክል በእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ በጠላትነት በመነሳት የእግዚአብሔርን ሥራ ለማውደምና ለማጥፋት ረቂቅ አሠራር ያለው እንደሆነ በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ በመጠኑ ተመልክተናል::

የእግዚአብሔር ቃል ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካሉ እንደሆነች ይነግረናል:: ክርስቶስ በአባቱ ቀኝ እንደተቀመጠ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከሰማያዊ ስፍራ እስከ ምድር ድረስ የክርስቶስ አካል እንደሆነች ይነግረናል:: እንዲሁም አለቅነትና ሥልጣናት በሰማያዊ ስፍራ እንዳሉ የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን 6÷12 ላይ ይነግረናል:: ስለዚህም ሁለት ሠራዊቶች በሰማያዊ ስፍራ እንዳሉ እንመለከታለን ልዩነታቸው ግን የሰይጣን መንግሥት ኃይልና ሥልጣኑ የተገፈፈ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ግን ኃያልና ባለሥልጣን ናት:: ቤተ ክርስቲያንም በሰማያዊ ስፍራ የተቀመጠችው:-

1ኛ. በሰማያዊ ስፍራ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ በረከት የባረካትን እንድትወርስ:: (ኤፌ 1÷3)

2ኛ. በሰማያዊ ስፍራ ላሉት አለቅነትና ሥልጣናት በልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ ተገልጣ የሰይጣንን ሥራ እያፈረሰች ሰዎችን ለማዳን::(ኤፌ 3÷10 -11)

ሰይጣን ንግሥት አስጢንን ወይንም የመካከለኛዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን እምቢ እንድትልና ከእግዚአብሔር ዕቅድ እንድትወጣ ካደረገ በኋላ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ሰማያዊ ስፍራዋንና ሥልጣንዋን እንድትጥል አደረገ:: ከዚህ የተነሣ በኃይልና በሥልጣን ዘውዷንም ደፍታ በሰማያዊ ስፍራ የምትመላለስ ሞገስ ያላት አስፈሪ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ስላልነበረች ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ባፈሰሰው የሰማያዊ በረከትና ሥልጣን ባለቤቱ ሰይጣን ሆነ:: የእግዚአብሔር ቃል ሲገልፅን:-

"ንጉሡም ዐዋጆችን ሁሉ ይፋ የሚያደርግበትን የቀለበት ማኅተም ወሰዶ የአጋግ ዝርያ ለሃመዳቱ ልጅ ለሆነውና በአይሁዳውያን ላይ በጠላትነት ለተነሣው ለሃማን ሰጠው::"(አስቴ 3÷10)

በዘፍጥረት 41÷42 እና በሐጌ 2÷23 ቀለበት የሥልጣን ምልክት እንደሆነ ይነግረናል:: እንዲሁም በአስቴር 3÷10 ላይ ንጉሡ ለሃማን ሥልጣኑን ሰጠው:: <u>ሰጠው</u> የሚለው ቃል በቀጥታ ሰይጣን ከክርስቶስ ሥልጣን ተቀበለ ማለት ሳይሆን ከላይ እንደተመለከትነው ንግሥት አስጢን ቦታዋን ስትለቅ ንጉሡ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው የቀለበቱ ባለቤት ሆነ ፤ ልክ አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት በነበሩበት ጊዜ በዚህ ምድር ላይ ሥልጣን የነበራቸውና ምድርን ሊገዙና ሊያስተዳድሩ የተሾሙ ነበሩ:: ነገር ግን ሰይጣን እግዚአብሔር አትብሉ ያላቸውን ፍሬ እንዲበሉ ካደረጋቸው በኋላ የዚህ ዓለም ገዢና ባለ ሥልጣን ሆነ:: እግዚአብሔር ሥልጣንን ስለሰጠው አይደለም ነገር ግን የአዳምንና የሔዋንን ሥልጣን ካስጣለ በኋላ የሥልጣኑ ባለቤት ሆነ:: ከዚህም የተነሣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሥጋን ለብሶ በመጣ ጊዜ ሰይጣን የዚች ምድር ባለ ሥልጣን ስለነበር ለጌታ ካቀረበለት ጥያቄ እንዱ :-

"ከዚህ በኋላ ዲያብሉስ ኢየሱስን ወደ አንድ ከፍተኛ ቦታ ላይ አውጥቶ የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየውና እንዲህ አለው <u>ይህን ሁሉ ሥልጣንና ክብር ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ይህ ሁሉ ለእኔ የተሰጠኝ ስለሆነ</u> ለፈለኩት መስጠት እችላለሁ:: ስለዚህ አንተ ለእኔ ብትሰግድልኝ ይህ ሁሉ የእንተ ይሆናል"

(ሉቃ 4÷5-7)

እዚህ ጥቅስ ላይ <u>"ይህ ሁሉ ለእኔ የተሰጠኝ ስለሆነ"</u> የሚል ቃል እናገኛለን:: ለሰይጣን ማንም ሥልጣንን የዚህንም ዓለም ክብር አልሰጠውም በማጭበርበር የአዳምንና የሔዋንን ሥልጣን ወስዶ እንጂ:: ኢየሱስ ግን የሰይጣንን ሥልጣን በመግፈፍ ሥልጣንን ለመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ሰጠ:: የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን በዚህ በተሰጣት ሥልጣን በደንብ ተጠቅማለች በኋላ ግን የመካከለኛዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደገና ያላትን ሥልጣን በመጣልዋ የሥልጣኑ ተጠቃሚ ሰይጣን ሆነ:: ሰይጣንም ክርስቶስን የዓለምን ክብር አሳይቶ ወድቆ እንዲሰግድለት እንደተመኘ ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ አስጢን የንግሥናዋን ሥልጣን ከጣለች በኋላ ሃማን

መርዶክዮስ ወድቆ እንዲሰግድለት ተመኘ ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል ሲነግረን:-

> "ሃማንም መርዶክዮስ ተንበርክኮ እንደማይሰግድለት በሰማ ጊዜ በቁጣ እንደ እሳት ነደደ" (አስቴ 3÷5)

ስግደት ማለት የመሸነፍ ምልክት ነው:: ሃማን ግን መርዶክዮስ እንዳልተሸነፈለት ባወቀ ጊዜ በተለይም ቤተ ክርስቲያን ወደ ቀድሞው ስፍራዋ እየተመለሰች መሆኑን ሲያውቅ ረቂቅ የሆነው የዐማሌቅን መንፈስ አሠራር ጀመረ:: የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት የራሱን ዕቅድ አወጣ:: ምን ጊዜም የዐማሌቁ ሃማን መንፈስ ሥራው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማጥፋት ማበላሸት ነው:: ንግሥት አስጢንን እንዳጠፋ የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን (አስቴርን) ለማጥፋት ዕቅድ አወጣ:: ያወጣውም ዕቅድ :-

> "... ስለዚህ በመላው የፋርስ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት ውስጥ ያሉትን አይሁዳውያን ሁሉ ለመግደል ዕቅድ አወጣ" (አስቴ 3÷6)

ዕቅዱም ማጥፋት ነበር ስለዚህ ረቂቅ የሆነውን አሠራሩን ዘረጋ በአስቴር 3÷10 ላይ የንጉሡን ቀለበት ማኅተም እንደወሰደና ቀለበቱም ሥልጣንን የሚያመለክት እንደሆነ ተመልክተናል ? ዮሴፍ በግብፅ አገር ንጉሡ ቀለበቱን ሰጠው:: ስለዚህ በቀለበቱ ሥልጣን ይጠቀም ነበር:: በተለይም የፋርስና የሜዶን ሕግ ወጥቶ የንጉሡ ቀለበት ማኅተም ካለበት አይሻርም ሌላ ዐዋጅ በቀለበቱ ማኅተም ካልወጣ በቀር::

ሃማን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማጥፋት የራሱን ዐዋጅ ካወጀ በኋላ የተጠቀሙበት ትልቅ አሠራር ሕዝቡን ግራ የሚያጋባ የንጉሡን ስም በመጠቀም የብርሃንን መልክ ይዞ በመምጣቱ ነበር:: ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል ሲገልፅልን :-

> "... ዐዋጁ በንጉሥ አርጤክሰስ ስም ተጽፎ የቀለበቱ ማኅተም ተደርጎበት ተላለፈ ::" (አስቴ 3÷12)

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን አዋጁን ያስተላለፈው ሃማን ነው የተጠቀመው ግን ቤተ ክርስቲያን በጣለችው የሥልጣን ቀለበት በንጉሡ ሥም ነበረ:: ይህ ዓይነቱ ረቂቅ የጠላት አሠራር በግልጽ አሁን ባለንበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሠራ ነው:: ዐማሌቁ ሃማን ካወጣው ትእዛዝ መካከል "...አይሁዳውያን ወጣት÷ ሽማግሌ÷ ሴት÷ ወንድ ሳይቀር ሕፃናትም ጭምር በመግደል ጠራርገው ያጠፉ ዘንድ የሚያዝ ቃል ነበረበት:: ያለ ምሕረት እንዲታረዱና ንብረታቸውም እንዲዘረፍ ትእዛዝ ወጥቶ ነበር::"(አስቴ 3÷13)

ከላይ እንዳየነው ሃማን የእግዚአብሔር ዕቅድና ሕዝቡን ለማጥፋት የተጠቀመባቸው ቀለበቱንና የንጉሡን ሥም ነበር:: በዚህም ተጠቅሞ ለማጥፋት ትእዛዝ ዐወጀ::

የዐማሌቅ መንፈስ ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ነገር ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ነው የሚፈልገው:: ስለዚህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በሦስት አቅጣጫ የዐማሌቅ አሠራር እንደሚመጣባት ማወቅና መረዳት አለባት::

ሀ) በማያምኑ ሰዎች የሚገለጥ የአማሌቃውያን አሠራር

እነዚህ ሰዎች አያምኑም ሙሉ በሙሉም በጠላት ሥልጣን ቁጥጥር ሥር ናቸው:: በተለይም በሃይማኖት ቀንበር የተያዙ ስለሆኑ አሁንም በንጉሡ ሥም ይጠቀምባቸዋል:: ስለዚህ ጭፍን በሆነ የሃይማኖት አመለካከት በዐማሌቅ መንፈስ ተይዘው በተለይም እውነተኛውን የእግዚአብሔርን አሳብ ይዘው በተነሱ ሰዎች ላይ ብዙ ጥቃት ለማድረስ ሥጋዊ በሆነ ኃይል መጠቀም የሚፈልጉ ናቸው:: ከነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ በሰይጣን መንፈስ ተሞልተው የእግዚአብሔርን ሰዎች እስከ መግደል እንኳን ሊደርሱ ይችላሉ:: ቤተ ክርስቲያንም ይህንን አሠራር በፀሎት በመትጋት ማፍረስ ይኖርባታል::

ለ) በነገሥታት የሚገለጥ የዐማሌቅ አሠራር

የዐማሌቅ አሠራር በየዘመናቱ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት የሚነሣ ስለሆነ በነገሥታትም በመጠቀም ሥራውን መሥራት ይፈልጋል:: ሙሴ በግብፅ ለነበሩ እስራኤላውያን የእግዚአብሔር የዘመኑን አሳብ

ይዞ ሕዝቡን ከባርነት ነፃ እንዲያወጣ በተወለደ ጊዜ ፈርዖን በዐማሌቅ መንፈስ የሞትን ዐዋጅ ዐወጀ:: ኢየሱስም ታላቁን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይዞ ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ ሄሮድስ በዐማሌቅ መንፈስ የሞትን ዐዋጅ ዐወጀ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማጥፋት አልቻለም::

በዘመናችን ነገሥታት በዐማሌቅ መንፈስ ተይዘው የእግዚአብሔርን ሕዝብና የዘመኑን አሳብ በመቃወም ትእዛዝና እዋጅን በማወጅ ለእግዚአብሔር ሥራ እንቅፋት ሊሆኑ ስለሚችሉ ቤተ ክርስቲያን ከእሁኑ እጥብቃ ይህንንም በፀሎት ማፍረስ ይኖርባታል:: ያለምንም ችግር የእግዚአብሔርን ሥራ አንድንሠራ አገሪቱንም በወንጌል ለማዳረስ እንድንችል መጽሐፍ ቅዱሳችን እንዲህ ሲል ይነግረናል :-

> " በመንፈሳዊነትና በመልካም ጠባይ እየተመራን በሰላምና በፀጥታ እንድንኖር <u>በተለይ ለነገሥታትና በሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ ፀልዩ::</u>" (1ጢሞ 2÷2)

ሐ) በዳኑ ሰዎች አማካኝነት የሚገለጥ የዐማሌቅ አሠራር

ይህ አሠራር ከላይ ካየናቸው ከሁለቱ ነጥቦች ለየት ያለ ነው:: ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ሳይሆን ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው በተቀበሉ መሪዎችና አገልጋዮች የሚገለጥ የጠላት አሠራር ነው:: በተለይም ባለንበት ዘመን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመምራት ላይ የሚገኙ እረኞች÷ ሽማግሌዎችና አገልጋዮች በእግዚአብሔር ፊት በመውደቅ እግዚአብሔር በእሁኑ ዘመን ምን በማድረግ ላይ እንዳለ የዘመኑን ዕቅድ በልዩ መረዳት ከመንፈስ ቅዱስ ካልተቀበሉ በቀር አሁን እየተሠራ ላለውና ሊመጣ ላለው የእግዚአብሔር ሥራ ትልቅ ዕንቅፋት ነው የሚሆኑት::

ሰይጣን ማንኛውንም ቤተ ክርስቲያን እንደሚፈታተን ግልጽ ነው:: ጴጥሮስ የዘመኑን አሳብ ባላወቀ አእምሮው የጌታችንን ታላቅ የመስቀል ሞት ለማስቀረት የሰይጣንን አሳብ ተቀብሎ አስተላለፈ:: ጌታም ጴጥሮስን የተጠቀመበት ሰይጣን እንደሆነ አውቆ :-

> "... ከአኔ ወዲያ ሂድ ሰይጣን አንተ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር ስለማታስብ መሰናክል ትሆንብኛለህ አለው:: " (ማቴ 16÷23)

እዚህ ላይ ጌታ ሁለት ነገሮችን ሲያደርግ እናያለን እንደኛው ሰይጣንን ሲገሥፀው:: ሁለተኛ ደግሞ ለጴጥሮስ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብም ሲለው እንመለከታለን::

ሃማን የዘመኑን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት <u>በንጉሡ ጸሐፊዎች</u> በኩል በንጉሡ ስም ዐዋጅ እንዲታወጅ እንዳደረገ ሁሉ ዛሬም ሰይጣን የአገልጋዮችን አእምሮ በወግ÷ በሥርዓትና በሃይማኖት ቀንበር አስሮ በመያዝ እውነተኛውን ከሰማይ የመጣውን የእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን በዐማሌቅ ስውር አሠራር ተይዘው እንደ ጴጥሮስ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አሳብ ሳይረዱ በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ በንጉሥ ስም ለሕዝቡ የሚያስተላልፉት የዘመኑን የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚቃወም እንደሆነ አይረዱትም:: ሕዝቡም ከሚነገረው ዐዋጅ የተነሣ ከዘመኑ የእግዚአብሔር ዕቅድ በጣም የራቁ ናቸው::

ባሁኑ ዘመን እግዚአብሔር እየሠራ ላለው የተሐድሶ ሥራና ሊመጣ ላለው ታላቅ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንቅፋት የሚሆኑት የዐማሌቅን አሳብ ተቀብለው እንደ እግዚአብሔር አሳብ ሳይሆን እንደ ሰው አሳብ የሚሔዱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ናቸው:: እንደ እነዚህ ዓይነት መሪዎች ሁል ጊዜ ከሰው አስተሳሰብ በመጣው ነገር ግን ከእግዚአብሔር እውነት በራቀ አመራር ቤተ ክርስቲያን እንድትመራ ይፈልጋሉ:: እንዲሁም እግዚአብሔር የገለጠውን የዘመኑን አዲስ አሳብ ይዘው የሚነሱትን አገልጋዮች ሁል ጊዜ መቃወም ይወዳሉ:: ሕዝቡም እንዳይከተላቸው የራሳቸውን ዐዋጅ አውጥተው በንጉሡ ስም ለሕዝቡ ያስማሉ:: የእግዚአብሔር ቃል ለማስተማር በከበረው የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ሲቆሙ የእግዚአብሔርን ቃል አጣመው ሕዝቡን በአመፀኝነት መንፈስ ይሞላሉ:: እንደነዚህ ዓይነት አገልጋዮችን በመፍራት እግዚአብሔር የሰጣቸውን የዘመኑን ዕቅድ የጣሉ ብዙ አገልጋዮች ናቸው:: ታዲያ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያስጥሉ ከሆነ በዐማሌቅ ረቂቅ አሠራር አእምሮአቸው እንደተያዘ ግልፅ ነው::

በተለይ በእሁኑ ዘመንና በሚመጡትም ዘመናት የእግዚአብሔርን አሳብ ይዛ ለምትነሣዋ ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ታላቅ አንቅፋት ይሆናሉ:: ስለዚህ እግዚአብሔር የዘመኑን ዕቅድ ገልጠላቸው የሰውን አሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን አሳብ ለማስተናገድ የሚፈልጉ ሁሉ ያለው አማራጭ ያዕቆብ በዐማሌቅ መንፈስ ከሚቃወመው ኤሳው ካለበት ከቤርሳቤህ ተነስቶ ዋጋን ከፍሎ የእግዚአብሔርን አሳብ አንዳገለገለ ሳይገለማመጡ ቤርሳቤህን ለቆ መውጣት ብቻ ነው:: ለተቃዋሚዎች ደግሞ አንደ ካህናት አለቆች÷ ሽማግሌዎችና ጻፎች አንዲሁም አንደ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ሥራና የዘመኑን አሳብ በመቃወም ዕንቅፋት ስትሆኑ እንዳትገኙ እንደ ኒቆዲሞስ በሌሊትም ቢሆን ወደ እግዚአብሔር አሳብ መምጣቱ ያዋጣል::

የመንፈስ ቅዱስ የሐዘን ድምጽ

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት ሃማን የተጠቀመባቸው <u>የንጉሡን ጻሐፊዎች</u> ነበር:: ይህ ማለት ዐዋጁን እንዲያስተላልፉ ሃማን የተጠቀመባቸው የንጉሡን አገልጋዮች ነበር:: ዐዋጁም በንጉሥ አርጤክስስ ስም ተፅፎ የቀለበቱ ማኅተም ተደርጎበት ተላለፈ ከዚህም የተነሣ መንፈስ ቅዱስን አሳዘኑት::

> " መርዶክዮስ ስለተደረገው ነገር ሁሉ በሰማ ጊዜ <u>በሐዘን ልብሱን ቀደደ...</u>"(አስቴ 4÷1)

ዐማሌቁ ሃማን የእግዚአብሔር የዘመኑን አሳብ ባልተረዱ ክርስቲያን አገልጋዮችና መሪዎች አአምሮ ረቂቅ የሆነውን የራሱን አሳብ አስቀምጦ በአነርሱ አንደበት በንጉሡ ስም የእግዚአብሔር የዘመኑን ዕቅድ በመቃወም ዐዋጅን አሳወጀ:: መንፈስ ቅዱስ ከሚያዝንባቸው ነገሮች አንዱ ያዳናቸው ሕዝብ አሳቡን ሳይረዱለት ሲቀሩ ተመልሰውም ተቃራኒ ሲሆኑ ነው:: የእግዚአብሔር ዕቅድ አስራኤላውያን ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ዓምድ እየመራ ክነዓን ሊያስገባቸው ነበር:: ነገር ግን ሕዝቡ ዕቅዱን መረዳት ተስኖአቸው ተቃራኒ ስለሆኑ ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አሳዘኑት:: (ኢሳ 63÷10)

በዘመናችን ያሉ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በደንብ ተቀምጠው ቢያስተውሉት በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ የሚያስተላልፉአቸው ሕዝቡን አርነት አውጥቶ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ሳይሆን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን እውነት ፈፅሞ የሚቃረን ነው:: ከዚህም የተነሣ መንፈስ ቅዱስን እያሳዘኑ ያሉ አገልጋዮች ጥቂት አይደሉም:: ይህ ብቻ አይደለም በአነኚህ ሰዎች ከሚተላለፍ ዐዋጅ የተነሳ ብዙ ሰዎች ለመንፈስ ቅዱስ ያላቸው አመለካከትና አክብሮት ፈር የለቀቀ ነው:: መርዶክዮስ በመገፋቱ አዝኖ በቤተ መንግሥቱ ደጅ እንደተቀመጠ ሁሉ ዛሬም ከዐዋጅ ነጋሪዎቹ የተነሣ ብዙ አገልጋዮችና ምእመናን መንፈስ ቅዱስንና የእርሱን የዘመኑን አሳብ ስለሚገፉት በደጅ ነው ያለው በመገፋቱም ለቤዛ ቀን የታተሙበትን የእግዚአብሔርን መንፈስ እያሳዘኑ ናቸው:: (ኤፌ 4÷30)

መርዶክዮስ በሐዘን ድምፁን ከፍ አድርጎ አየጮኸ በከተማው ሁሉ ይመላለስ እንደነበር (አስቴ 4÷1) እንዲሁም ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በሚገፉት ቤተ ክርስቲያን በተለያየ መንገድ የጩኸት ድምፁን በማሰማት ላይ ነው:: ለዚህም ድምፅ ምላሽ መስጠት የእኛ ፈንታ ነው:: ድምፁን አልሰማንም ማለት ፈፅሞ አንችልም (ዕብ 1÷1-3) ሌላው ቢቀር የተቀቡ አገልጋዮች ጩኸት የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ መሆኑን በደንብ ጠንቅቀን ማወቅ ይኖርብናል:: ሃያና ሠላሳ ሺ ምእመናን ባሉበት ቤተ ክርስቲያን አንድ የተቀባ አገልጋይ ተገፍቶ ሲወጣ ካለው የምእመን ቁጥር ብዛት እንደ ቀላል ነገር በመቁጠር ንቀነው ዝም እንል ይሆናል:: ነገር ግን የሠላሳ ሺህ ምእመን መፍትሔ በአንድ የተቀባ ሰው ቅባት ውስጥ እግዚአብሔር እንደሚያስቀምጥ ማወቅ አለብን:: የስድስት መቶ ሺህ እስራኤላውያን መፍትሔ እግዚአብሔር በሙሴ ቅባት ውስጥ አስቀምጦ ነበር:: የፈለገው ያህል የቁጥር ብዛት ቢኖረንም የያዝነው ሕዝብ በአንድ በተቀባ ሰው መገፋት ምክንያት ሊበተኑ ስለሚችሉ የተቀቡ ሰዎችም ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ልዩ ስጦታዎች ስለሆኑ አነሱን ገፋን ማለት የቅባቱ ሰጪ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ገፋን ማለት ነው:: ከዚህ የተነሣ የሐዘን ድምፁን ዛሬም በቤተ ክርስቲያን እያስተጋባ ነው::

የመንፈስ ቅዱስ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን

በመጨረሻው ዘመን የሚኖሩ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ተብለው እንደማይጠሩ ቀደም ብለን አይተናል:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ተብለው የሚጠሩት እንደ አስቴር ያሉ የእግዚአብሔርን ዕቅድ የተረዱ ያንንም ዕቅድ ይዘው የሚጓዙ ናቸው:: እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ለዘላለም በምድር ላይ እንድትኖር አልጠራትም:: መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን አስውቦና አሳምሮ ወደ ዘላለማዊው ስፍራዋ ሊወስዳት ይፈልጋል:: ስለዚህ ይህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የምትሰናዳበት ጊዜ እንደሆነ ለሁላችንም ግልፅ ነው:: ቀደም ሲል መንፈስ ቅዱስ አያዘነበት ያለበትን ሁኔታ ተመልክተናል፤ መንፈስ ቅዱስን ያሳዘነውን በእግዚአብሔር የዘመኑ ዕቅድ ላይ የሚወጣውን የዐማሌቅን አሠራር ገርስሳ የምትጥለው የዘመኑ የእግዚአብሔር ዕቅድ የገባት የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ለእንደነዚህ የዘመኑ ዕቅድ ለገባቸው መሪዎች÷ አገልጋዮችና ምእመናን ተነስተው እውነተኛውን አገልግሎት እንዲያገለግሉ የልመና ሳይሆን የማስጠንቀቂያ ድምፁን የሚያሰማበት ጊዜው አሁን ነው::

አስቴር ዘውዷን ብትጭን የዘመኑም የእግዚአብሔር አሳብ ቢገባትም ነገር ግን ሥራው በዚህ አያበቃምና ልክ ለሙሴ እንደተነገረው የዐማሌቅን መንፈስ ከምድረ ገፅ ማጥፋት አለባትና እንድትነሣ ጉዞዋንም እንዳታቆም የማስጠንቀቂያ ቃሉን እንዲህ ሲል ያስማታል :-

> "መርዶክዮስም የአስቴርን መልእክት ከተቀበለ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን ማስጠንቀቂያ ላከባት÷ <u>አንቺ በቤተ መንግሥት ለመኖር በመቻልሽ ከሌሎቹ አይሁዳውያን የተሻለ ዋስትና እንዳለሽ አይምሰልሽ ! አንደዚህ ባለው ጊዜ ችላ ብለሽ ዝም ብትዪ÷ ለአይሁዳውያን ከሰማይ አርዳታ መምጣቱ አይቀርም፤ እነርሱም በአርግጥ ይድናሉ፤ አንቺ ግን ትሞቻለሽ፤ የአባትሽም የቤተሰብ ሐረግ ተቋርጦ ይቀራል፤...</u>"
>
> (አስቴ 4÷12- 14)

መንፈስ ቅዱስ ከአሁን በኋላ መስተካከል ስላለበትና በተሐድሶ መለወጥ ስለሚያስፈልጋቸው በእግዚአብሔር ሳይሆን በሰው አመለካከት ስለተተከሉ ብዙ ነገሮች እንድናስተካክል ካለበለዚያ ግን ሊገጥሙን ስለሚችሉ ሦስት ነገሮች ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል :-

1ኛ. "በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በመቀመጥዋ የተሻለ ዋስትና እንደሌላት" ብዙ አገልጋዮችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልጋይና መሪ ስለሆኑ የተሻለ ዋስትና ያላቸው ይመስላቸዋል:: የመንፈስ ቅዱስን ደመና ከመከተል ይልቅ ደመናው እኒሱን እንዲከተላቸው ይፈልጋሉ:: ነገር ግን ደመናውን መከተል ካቆሙ ዋስትና እንደሌላቸውና ደመናውም ጥሎአቸው እንደሚሄድ በማሳወቅ ያስጠነቅቃቸዋል::

2ኛ. <u>"በእንደዚህ ባለው ጊዜ ችላ ብለሽ ዝም ብትይ ለአይሁድ ረዳት ከሰማይ መምጣቱ አይቀርም እነሱም ይድናሉ "</u> የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ጠንቅቀው ይህንን መረዳት ይኖርባቸዋል:: ከዘመኑ የእግዚአብሔር ዕቅድ ጋር ሳይራመዱ እያወቁ ችላ ብለው ዝም ቢሉ እግዚአብሔር በዐማሌቅ ሠንጋ ያልተማረኩ፤ በምድረ በዳ መቅረትን የማይፈልጉ፤ የዘመኑ የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሚገባ የተረዱ፤ ዮርዳኖስን የተሻገሩ መዳንን ለአይሁድ ሕዝብ ከሰማይ የሚያመጡ ሌላ አዲስ ትውልድ እግዚአብሔር ማስነሳት እንደሚችል የዘመኑን ዕቅድ ተረድተው ችላ ለሚሉ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን የማስጠንቀቂያ ድምፅ ይልካል::

3ኛ. <u>"አንቺ ግን ትሞቻለሽ የአባትሽም ቤት ሐረግ ተቋርጦ ይቀራል"</u> የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ማወቅ ያለባቸው ሌላው ነገር የዘመኑን ዕቅድ የተረዱ እምቢ አሻፈረኝ የሚሉትን አገልጋዮች እግዚአብሔር ከክብር እንደሚያሳድላቸው ነው:: የንግሥት አስጢን ቤተ ክርስቲያን ለንጉሡ ዕቅድ አምቢ ባለች ጊዜ ከክብር እንደጎደለች ሁሉ የዘመኑን የመንፈስ ቅዱስን አሳብ የማትቀበልና መታደስ ያለበትን ዋጋ ከፍላ የማታድስ ቤተ ክርስቲያን ምናልባት ከጥቂት ዓመታት በኋላ ኃይልዋና ፀጋዋ ከእርስዋ የተገፈፈ የሃይማኖት መልክ ያላት ኃይሉን ግን የካደች አሳዛኝ ታሪክ የሚያጋጥማት ስም ብቻ የያዘች ነገር ግን የሞተች እንደምትሆን መንፈስ ቅዱስ በማስጠንቀቅ ይነግራታል:: ተሐድሶ ዋጋን ያስከፍላል የራስን ክብር ያስጥላል መሰደብና መሰደድን ሊያስከትል ይችላል:: ነገር ግን እርስ በርሳችን ስንከባበር የእግዚአብሔርን ክብር ከመጣል የራሳችንን ክብር ጥለን በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ መኖር ይሻለናል::

ም ዕ ራ ፍ ስ ም ን ት

ለመጨረሻዋ ዘመን

ቤተ ክርስቲያን

የወርቅ በትር መዘርጋት

የወርቁ በትር መዘርጋት

አስቴር የመንፈስ ቅዱስን የማስጠንቀቂያ ቃል ከሰማች በኋላ ወደ ኋላዋ በመመለስ እንደ ንግሥት አስጢን መሆንን አልፈለገችም:: ስለዚህ በዐማሌቁ ሃማንና በአሠራሩ ላይ ለመውጣት እንዲህ ስትል ቁርጥ ውሳኔ አደረገች :-

"ከዚህም በኋላ በሕግ የተከለከለ ቢሆንም ደፍሬ ወደ ንጉሡ ዘንድ እገባለሁ ይህን በማድረጌ ብሞትም ልሙት" (አስቴ 4÷16)

ከላይ ባለው ጥቅስ "በሕግ የተከለከለ" የሚል ቃል እናገኛለን አስቴር ወደ ንጉሡ እንዳትገባና ለውጥ ለአይሁድ ሕዝብ እንዳታመጣ የፈራችው አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር ሕጉን ጥሶ ማለፍ ነበር:: ምክንያቱም ወደ ንጉሡ ገብታ ለውጥ የሚያመጣውን የወርቅ በትር እንዳትነካ በአርስዋና በአምላክዋ መካከል ሕግ ነበር:: ዛሬም ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃሉ ነገር ግን ሰው ሠራሽ ሕግ ተብትቦ ይዟቸዋል:: መሪዎቹ በሕግ የታሠሩ ናቸው እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፎች ሁሉ በብዙ ገፅ ሕግ የተያዙ ናቸው:: የመተዳደሪያ ደንብ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ ቢሆንም ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃልና አሠራር ጋር የሚቃረን ከሆነ የመተዳደሪያ ደንብ ሳይሆን ወጥመድ ይሆናል:: ብዙ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት ከመሪዎች ጀምሮ ሁሉም የአገልግሎት ዘርፍ በሕግ ራሳቸውን አጥረዋል:: አንዱ አንዱን መንካት አይችልም ቤተ ክርስቲያን እንድትሻሻል ከመንፈስ ቅዱስ የመጣ አሳብ አንዱ ሲያቀርብ ሌላኛው ተነስቶ ሕጋችን (ደንባችን) የሚል አሳብ ያቀርባል:: ከዚህ የተነሣ ከመንፈስ ቅዱስ አሳብ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ከብር የማያሳይ ሕግና ደንብ ነው::

አስቴር ከንጉሡ ጋር እንዳትገናኝ የሚያደርጋትን የፈራሳውያንና የካህናት አለቆችን ሰው ሠራሽ ሕግ ጥሳ በድፍረት ወደ ንጉሡ ለመግባት ወሰነች:: እዚህ ላይ በደንብ ማስተዋል ያለብን ስትወስን ግን ትልቅ አቋምን

ይዛ ነበር ይህም አቋም "ይህን በማድረጌ ብሞትም ልሙት" የሚል ነበር:: ለውጥን የሚያመጡ ሰዎች ራሳቸውን ከደው ለንጉሡ ክብር ብቻ ለመኖር እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ለመሆን አቋም ያላቸው ናቸው:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የዘመኑን የእግዚአብሔርን ዕቅድ አገልግሎ ለማለፍ ሞትን የማትፈራ ናት:: የዘመኑን ዕቅድ በመረዳት እግዚአብሔርን ለማገልገል አቋም ካላቸው ጋር መንፈስ ቅዱስ ለመሥራት ዝግጁ ነው::

ከዚህም የተነሣ አስቴር ጠላትዋን ሃማንና አሠራሩን የምትቀጠቅጥበት የወርቁን በትር ለመንካት ከልካዩን ሕግ ጥሳ በንጉሡ ፊት ቆመች :-

" ንጉሡ÷ ንግሥት አስቴር በሰተ ውጭ በኩል መቆምዋን በተመለከተ ጊዜ በፊቱ ሞገስን አግኝታ ስለነበር የወርቅ በትሩን ዘረጋላት፤ እርስዋም ቀረብ ብላ የወርቁን በትር ጫፍ ነካች::"(አስቴ 5÷2)

አስቴር የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ባላት ቁርጥ አቋም ንጉሡን ስለማረከችና በፊቱም ሞገስን ስላገኘች የወርቁን በትር ዘረጋላት ይህም የወርቅ በትር የኃይል በትር ነው:: ሰይጣን ረቂቅ በሆነ አሠራሩ ቤተ ክርስቲያን ወደተዘጋጀላት ስፍራ እንዳትደርስ ይዋጋል:: ቤተ ክርስቲያን ይህንን የሰይጣን አሠራር ለመምታት በጠላቶችዋ መካከል ለመግዛት የወርቁን በትር መንካት ይኖርባታል:: አስቴር የአምስቱ የአገልግሎት ስጦታ ባለቤት ሆናለች እነኚህን የአገልግሎት ስጦታ የተቀበሉ ሰዎች የወርቁን በትር ነክተው የሚያገለግሉት አገልግሎትና ሳይነኩ የሚያገለግሉት አገልግሎት በጣም ይለያያል:: የወርቁ በትር በተሰጠን የአገልግሎት ስጦታ ልዩና ታላቅ በሆነ የእግዚአብሔር ኃይል መገኘት እንድናገለግል የሚያደርግ ነው:: የወርቁን በትር የነኩ አገልጋዮች በሚያገለግሉበት ቦታ ታላቅና ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር የኃይሉ መገኘት ይኖራል::

የኤልያስ የጨርቅ መጎናፀፊያ ለኤልሳዕ ዕጥፍ ቅባት ካስገኘ ያም ቅባት ተትረፍርፎ ከእስራኤል አልፎ ለሶርያውያን ከበቃ፤ እንዲሁ ሙሴ ምድራዊ የአረኝነት በትሩ በእግዚአብሔር ቅባት ተቀብቶለት በበትሩ ተአምራትን እያደረገ ሕዝቡን በምድረ በዳ ከመራ፤ የጨርቅና የእንጨት ሳይሆን ከሰማይ የሚዘረጋውን የወርቅ በትር የነኩ አገልጋዮች በምን ዓይነት

የእግዚአብሔር የኃይሉ መገኘት ውስጥ ሆነው እንደሚያገለግሉ መገመት ይቻላል ይህ የወርቅ በትር ለሙሴ፥ ለኢያሱ፥ ለኤልያስ፥ ለኤልሳዕ እንዲሁም ለነቢያትም አልተዘረጋም:: የቤተ ክርስቲያን አዕማድ መስለው ለሚታዩት ለያዕቆብ፥ ለዮሐንስና ለጴጥሮስ አልተዘረጋም:: ብዙ የአዲስ ኪዳን ምስጢር ለተገለጠለት ለጳውሎስም አልተዘረጋም:: ይህ የወርቅ በትር ጠላቶችዋን የእግርዋ መረገጫ አድርጋ የመጨረሻውን የወንጌል ሥራ ለመሥራት ለተዘጋጀችው ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀ ልዩ የኃይል በትር ነው:: ይህንን በትር ያልነካች ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን የእግርዋ መረገጫ ማድረግ አትችልም::

ዳዊት ስለ ክርስቶስ ሲተነብይ እግዚአብሔር በጠላቶቹ መካከል የሚገዛበት የኃይል በትር ከጽዮን እንደሚልክለት በዚህም በትር በጠላቶቹ መካከል እንደሚገዛ እንዲህ በማለት ይነግረናል:-

> "እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል፤
> በጠላቶችህም መካከል ግዛ:: "(መዝ 110÷2)(የቀ.ት)

የእግዚአብሔር ቃል ክርስቶስ ገና ሙሉ በሙሉ ጠላቶቹን በመግዛት በሥልጣኑ ሥር እንዳላደረገ እስከሚያደርግለት ድረስ ግን እንደሚጠብቅ በዕብራውያን ላይ ሲናገር "ከእንግዲህ ወዲህ ጠላቶቹ በሥልጣኑ ሥር እስኪሆኑ ድረስ ይጠባበቃል::" (ዕብ 10÷13)

ጠላቶቹ ደግሞ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ በአብ ቀኝ መቀመጥ እንዳለበት በዕብራውያን 1÷13 ላይ ይነግረናል:: ጠላቶቹን የሚረግጥበት እግሩም አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ነች:: ስለዚህ ክርስቶስ ጠላቶቹን ድል ለማድረግ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን የኃይል በትር የሚልክላት ጠላቶችዋን በእግርዋ ሥር መርገጥ ለምትችለው ለመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ነው:: አንተም ስው ሆይ እንደ አስቴር ከጽዮን የኃይል በትር ተቀብለህ በጠላቶችህ መካከል ለመግዛት የተዘጋጀህ ሁን:: አስቴር ይህንን የኃይል በትር ነክታ ጠላቶችዋን ለመግዛት፥ ለመርገጥና ለማድቀቅ ግብጣን አዘጋጀች::

በግብጣ ቦታ የሰይጣን ራስ መቀጥቀጥ

> "አስቴርም፥ ንጉሥ ሆይ ! መልካም ፈቃድህ ቢሆን ለዛሬ ግታ ባዘጋጀሁት ግብጣ ላይ አንተና ሃማን ብትገኙልኝ እወዳለሁ አለችው::" (አስቴ 5÷4)

> "ግርማዊነትህ የጠየቅሁትን ነገር ሊፈፀምልኝ ፈቃደኛ ከሆነ ነገ በማዘጋጅላችሁ ግብጣ ላይ አንተና ሃማን በድጋሚ እንድትገኙልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፤ በዚያም ስዓት የምፈልገውን ነገር እገልጥልሃለሁ::"
>
> (አስቴ 5÷8)

አስቴር ያዘጋጀችው የግብጣ ሁኔታ በምዕራፍ ስባት ላይ በሙሉ በደንብ ተብራርቶ ተገልጸልናል:: አስቴር ግብጣን አዘጋጅታ የጠራችው ንጉሡን እንዲሁም ጠላትዋን ሃማን ነው:: ንጉሡ ግብጣን ቢያዘጋጅላት እምቢ ብላ በራስዋ አመለካከት ከፍ ከፍ ብላ እንድትታይ ንጉሡ በሌለበት ስፍራ ግብጣን እንዳዘጋጀችው እንደ ንግሥት አስጢን አንዳንድ ቤተ ክርስቲያን ንጉሡ በሌለበት ስፍራ ግብጣን (ኮንፍራንስን) ያዘጋጃሉ:: ንጉሡ በሌለበት እንደ ንግሥት አስጢን በወይዛዝርት መካከል ለመከበርና ለመሞገስ በመፈለግ እንዲሁም በሰው ፊት ለመታወቅና ትልቅ አገልጋይ ተብሎ ለመጠራት ከእግዚአብሔር ሳይቀበሉ በተሳሳቱ መልዕክቶችና መገለጦች ሕዝቡን ግራ ያጋባሉ::

የአስቴር ፍላጎት ግን ከዚህ በጣም የተለየ ነው:: ንጉሡ በግብጣው ላይ ምን እንዲያደርግላት በጠየቃት መሠረት ግብጣውን ያዘጋጀችው እርስዋ መክበርና መሞገስን ፈልጋ ሳይሆን ፍላጎትዋን ስትገልጽ :-

> "...የእኔ ፍላጎት እኔም ሆንሁ ወገኖቼ በሕይወት መኖር እንድንችል ነው" (አስቴ 7÷3)

የእርስዋ ትልቁ ፍላጎትና አሳብ በትክክል ለእግዚአብሔር ሕዝብ በረከትን ለማምጣት ሕዝቡን በድልና በትልቅ የእግዚአብሔር ክብር ውስጥ እንዲኖሩ አምላካቸውም በሕዝቡ ላይ እንዲከብር ስለሆነ እንደ

ንግሥት አስጢን ባልተበላሸ የልብ አሳብና ፍላጎት ለሕዝብዋ ጥቅምና ለአምላክዋ ክብር ግብዣ አዘጋጀች:: ዳዊት በጠላቶችዋ ፊት ለፊት ግብዣን ስለሚዘጋጅላት የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በትንቢት መንፈስ በመመልከት :-

"ጠላቶቼ እኔን በሚመለከቱበት ታላቅ ግብዣን አዘጋጀህልኝ፤ እንደ ክብር እንግዳ ራሴን በዘይት ቀብተህ ተቀበልኸኝ፤ እስኪትረፈረፍ ድረስ ጽዋዬን ሞላህልኝ ::"
(መዝ. 23÷5)

አስቴር በጠላቶችዋ መካከል የምትገዛበትን የወርቅ በትር ስለነካች ጠላቶችዋን እያጋለጠች መቀጥቀጥ ትልቅ ዓላማዋ ሲሆን ንጉሡንና ሃማን በግብዣዋ ቦታ ከጠራች በኋላ የሃማን አሠራርና የመጨረሻዋን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሊያጠፋ ያወጣውን ዕቅድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ከሆነው ከመርዶክዮስ ባገኘችው መገለጥ መናገር ጀመረች:: ሃማን ምስጢሩ ሁሉ እንደታወቀበት ዕቅዱም እንደሚመታ አውቆ "...ሃማን እጅግ በመደንገጥ እንዲ ወደ ንጉሡ አንዲ ወደ ንግሥቲቱ ይመለከት ጀመር::" (አስቴ 7÷6)

አስቴር አሁን ያገኘችው ትልቁ ጠላትዋ የዐማሌቁ መንፈስ ነው:: ከምድረ ገፅ መጥፋት ያለበትን፤ መታሰቢያ እንዳይኖረው የተነገረለትን፤ ያዕቆብን የተዋጋውን÷ ኢያሱንና ሙሴን የተዋጋቸውን፤ ሳአልንም እንዲናቅ ያደረገውን፤ ብዙዎቹን ልጅ አልባ ያደረገውን፤ ንግሥት አስጢንን ከክብር እንድትጎድል ያደረጋትን፤ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማጥፋት የማይተኛውን ያንን ዐማሌቁን ሃማን ነበር ፊት ለፊት ያገኘችው::

አስቴር ሃማን ለማግኘት ብዙ መክፈል ያለባትን ዋጋ ከፍላ ወደ ኋላ ሳትመለስ÷ ሳትደክምና ሳትኩራራ ሃማን አሳድዳ ይዛ ፊት ለፊት የምትረግጥበትን የኃይል በትር ልትነካ የቻለችው ዳዊት በትንቢት ገና ስለምትመጣዋ ጠላቶችዋንም አሳዳ ስለምትይዘውና የእግርዋ መረገጫ ስለምታደርገው የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ሲናገር:-

"ጠላቶቼን አሳድጄ እይዛቸዋለሁ፤ ሳላጠፋቸው ወደ ኋላ አልመለስም:: ዳግመኛ እንዳይነሱ አድርጌ እመታቸዋለሁ፤ ተሸንፈውም በእግሬ ሥር ይወድቃሉ:: ለጦርነት ኃይልን ትሰጠኛለህ፤ በጠላቶቼም ላይ ድልን ታጎናጽፈኛለህ ::"
(መዝ.18÷37-39)

በአስቴር ምዕራፍ አንድ ላይ ንጉሡ በንግሥት አስጢን እምቢታ ድምፅ እጅግ ተቈጥቶ ነበር:: በተጨማሪም አስቴርን ለማጥፋት ሃማን ያወጣውን ዕቅድ ሲሰማ ንጉሡ እጅግ ተቈጣ:: ሃማንም በበኩሉ መርዶክዮስ (መንፈስ ቅዱስ) እንዳልተሸነፈለት ባየ ጊዜ በቁጣ እንደ እሳት ነዶ ነበር:: (አስቴ 3÷5) እንግዲህ ጠላቱን ሊበቀል በቁጣ የተነሣውን ክርስቶስንና የእግዚአብሔርን ሥራ ለማጥፋት በቁጣ የተነሣውን ሰይጣንን ለእንዲና ለመጨረሻ ጊዜ በግብዣው ላይ የምታገኘኘው የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ናት:: በዚህ መሐል ደግሞ አስቴር በራስዋ ላይ ከደፋችው ዘውድ የሚፈነጥቅ እሳታማዊ ነፀብራቅ ከነካችውም በትር የተነሣ በግብዣው ላይ እጅግ ታላቅ የሆነ የእግዚአብሔር የኃይሉ መገኘትና የንጉሡ የበቀል ቁጣ ተጨምሮ ሃማን ባለበት ስፍራ ሲገለጥ መቋቋም ስላልቻለ "...ንግሥት አስቴር በተቀመጠችበት ድንክ አልጋ ላይ በግንባሩ ተደፋ..." (አስቴ7÷8) ከክብር የጎደለችው ንግሥት አስጢን በተጠራችበት የክብር ስፍራ በድንኩ አልጋ ላይ በመቀመጥና ከዚያም ከሚገኘው ከመሠረቱ በሚፈነጥቀው ነፀብራቅ እየተሞላች ሕያው አገልግሎትን ማገልገል እምቢ አለች:: አስቴር ግን በድንኩ አልጋ ላይ ተቀምጣ ሳለ ሕያውን አገልግሎት እያገለገለች ሳለ ጠላቶችዋን ከእግርዋ ሥር ጣለች:: የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ናት ሙሉ በሙሉ የክርስቶስን ሥልጣን በመጠቀም ጠላቶችዋን የምትረግጠው::

ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ጠላቶቹን ድል ለማድረግ የቅዱሳንን እግር ይጠብቃል:: የመጨረሻውን ሥራ የምትሠራውን እካሉን ይጠብቃል:: ድል መንሳት ያለባትን ያቺ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች በወርቅ አልጋ ላይ ተቀምጣ÷ የወርቅ ዘውድ ደፍታ÷ የወርቅ በትሩን ነክታ÷ እምራና ደምቃ ከፍ ከፍ ብላ የምትሄደውን÷ የክበረች÷ በከርቤና በዘይት በጣፋጭ ሽቶ የታሸችውን÷ ንጉሡን በምትሸተው ጠረንና በቅርጿ የምትማርከውን ያቺን የመጨረሻዋን ዘመን ውብ ቤተ ክርስቲያን ጠላቶቹን የእግሩ መረገጫ ለማድረግ ይጠብቃታል::

የመላእክት አገልግሎት በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን

በመጽሐፈ አስቴር ላይ የተጠቀሱት ጃንደረቦች የመላእክት ምሳሌ ሆነው የተለያየ አገልግሎት ሲሰጡ በመጽሐፉ ገጾች በመጀመሪያ ክፍል

ላይ አይተን ነበር:: በመጽሐፈ አስቴር ላይ ያሉ ጃንደረቦች ሁሉ የመላእክት አገልግሎት ነው የሚያገለግሉት ይህንንም በእግዚአብሔር ቃል በማመሳከር አንመለከተዋለን::

መጽሐፍ ቅዱሳችን መላእክት የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደሆኑ በግልፅ ይነግረናል:: መላእክት የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ ሰው ያመጣሉ እንዲሁም ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ የመስቀሉን የማዳን ሥራ ሊያወርሱ የክርስቶስ አካል በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ያገለግላሉ:: በዕብራውያን መልእክት ስለ ክርስቶስና ስለ መላእክት ማንነት ከገለፀ በኋላ በመጨረሻ የመላእክትን አገልግሎት ሲገልፅ:-

> "ታድያ መላእክት የሚድኑትን ለማገልገል የሚላኩ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የሆኑ መንፈሶች አይደሉምን ?" ይላል (ዕብ 1÷14)

ጌታ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያገለግሉ መላእክት ሲገልፅ :-

> "አውነት አውነት እላችኋለሁ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔር መላእክትም በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ " (ዮሐ 1÷51)

ያዕቆብ ወደ ካራን ሲሄድ በህልሙ ከመሬት አስከ ሰማይ የሚደርስ መሰላል አየ:: እግዚአብሔርም ተገለጠለት:: በመሰላሉም ላይ የእግዚአብሔር መላእክት ወደ ላይ ይወጡና ወደ ታች ይወርዱ ነበር:: (ዘፍ28÷12) ያዕቆብ በነበረበት ዘመን ክርስቶስ ገና ስላልተገለጠ የመሰቀሉም ምስጢር ስላልተፈፀመና ቤተ ክርስቲያንም ስማያዊውን ስፍራ ስላልያዘች ያዕቆብን መላእክት ያገለገሉት በመሰላል ላይ በመውጣትና በመውረድ ነበር:: ጌታ ኢየሱስ ግን በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ ያለው ጌታ የቤተ ክርስቲያን ራስ ሆኖ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደሚቀመጥ አካሉ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በምድርና በሰማያዊ ስፍራ ቦታዋን ስለምትይዝ ጌታ የተናገረው ከሞትና ከትንሳኤው በኋላ ስማያት ተከፍተው አካሉ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን የዳኑትን ስለሚያገለግሉ መላእክት ነው:: ስለሆነም አካሉንም ጨምሮ ነው በሰው ልጅ ላይ ያለው::

ከዚህም የተነሣ ለደቀመዛሙርቱ ገና ከዚህ የሚበልጥ ታያላችሁ ብሎ ስለሚጠብቃቸው የመላእክት አገልግሎት የነገራቸው:: ይህንንም በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ስንመለከተው ራስ ከሆነው ከንጉሡ ጀምሮ አካሉ የሆነችው አስቴር ድረስ የጃንደረቦችን (የመላእክትን) አገልግሎት እንመለከታለን::

--- አስቴር በመጀመሪያ በቁንጅና ክብካቤ ጥሩ ጥሩ ምግብ እንድትመገብ ሲደረግ መላእክት (ጃንደረቦች) ያገለግልዋት ነበር:: ኤሊያስ በመንገድ ዝሉ ባንቀላፋ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከእንቅልፍ ቀስቅሶ የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነስተህ ብላ አለው፤ ወዲያው በምድረ በዳ ውሃና ምግብ በሌለበት ስፍራ ከሰማይ በሆነ መልአክ የተላከ ምግብና ውሃ በራሱ አጠገብ አገኘ::(1ነገ 19÷5-8) ከበላና ከጠጣ በኋላ በዚህ ምግብ ኃይል አስከ እግዚአብሔር ተራራ አስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ተጓዘ:: ኮሬብ የእግዚአብሔር ክብር የሚታይበት ከሰማይ የመጣ እሳት ከተራራው ጫፍ አስከ ሰማይ ድረስ የሚነድበት እግዚአብሔር ራሱን በታላቅ ኃይል የገለጠበት ተራራ ነው:: ኤሊያስ ወደዚህ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ለመድረስ ከሰማይ የመጣ ምግብ መመገብ ነበረበት ::

አስቴር አቋም ኖርዋት የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት ቁርጥ ውሳኔ የወሰደች ስለነበረች ወደ እግዚአብሔር ተራራ ለመድረስ ሰማያዊውን ምግብ መብላት ባለባት ጊዜ እንድትመገብ የሚያገለግልዋት መላእክት ተልከውላት ነበር:: (አስቴ 2÷8-9)

--- አስቴር ውስጣዊ ጥንካሬ እንድታገኝ በከርቤ ሽቶ ስትታሽ የመላእክት ምሳሌ የሆኑት ጃንደረቦች ያገለግልዋት ነበር :: ጌታ ኢየሱስ በምድረ በዳ በሰይጣን አርባ ቀን ውስጣዊ ጥንካሬው ሲፈተን መላእክት ያገለግሉት ነበር:: "በምድረ በዳ በስይጣን አየተፈተነ አርባ ቀን ስነበተ ከአራዊት ጋርም ነበር መላእክትም አገለገሉት" (ማር 1÷13) (የቀ.ት) እንዲሁም ጌታ ወደ መስቀል ሞት የመሄጃው ሰዓት በደረሰ ጊዜ ከፊት ለፊቱ ያለውን የመስቀል ሞት አየተመለከተ በታላቅ ትካዜ ሆኖ አፅንቶ ሲፀልይ የሚያበረታታ መልአክ ከሰማይ ተላከለት:: (ሉቃ22÷43) የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስለ ጌታ ብላ የምትከፍለው ትልቅ ዋጋ ስላለ ውስጣዊውም ጥንካሬዋም ስለሚፈተን እንደ ጌታ ኢየሱስ በዓይናችን ባናያቸውም የሚያበረቱ መላእክት ይላኩላታል::

--- በዘካርያስ ምዕራፍ ሦስት ታላቁ ካህን ኢያሱን ሰይጣን ዕድፋሙን ልብስ አልብሶ በእግዚአብሔር ፊት ሊከሰው ሲል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ነጭ ልብስ እንዲያለብሱት በራሱም ላይ ጥምጥም እንዲያደርጉለት እግዚአብሔር ያዘዛቸው መላእክትን ነበር:: በተጨማሪ በሉቃስ ምዕራፍ ዐሥራ አምስት ላይ የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ሲመለስ ለእግሩ ጫማ ለጣቱ ቀለበት መልካሙንም ልብስ እንዲያለብሱት የሰባውንም ፍሪዳ እንዲያርዱለት የታዘዙት የመላእክት ምሳሌ የሆኑ የአባቱ ቤት አገልጋዮች ናቸው:: እንዲሁ አስቴር ወደ ንጉሡ ስትቀርብ ንጉሡን ደስ ያሰኘዋል ብላ ራስዋ የመረጠችውን ልብስ ሳይሆን በመላእክት አማካኝነት ክስማይ በመጣ ትእዛዝ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘውንና የሚማርከውን ልብስ እንድትለብስ የነገራት የመላእክት ምሳሌ የሆነው ጃንደረባው ነው ::

> "እርስዋም ወደ ንጉሡ ለመቅረብ ተራዋ በደረሰ ጊዜ የለበሰችው የምርጥ ሴቶች መኖሪያ ኃላፊ የነበረው ጃንደረባው ሂጋይ እንድትለብስ በመከራት መሠረት ነበር::"
>
> (አስቴ 2÷15)

በተለይም በሐዋርያት ዘመን ግልጽ በሆነ መንገድ መላእክት ያገለግልዋቸው ነበር:: ለቆርኔሌዎስ የእግዚአብሔር መልአክ ተገለፀለት እግዚአብሔር ሊያድነው እንደ ወደደ ከገለፀለት በኋላ ወደ ኢዮጴ ሰዎች ልኮ ጴጥሮስ የተባለው ስምዖንን እንዲያስመጣ ነገረው:: በባህሩ አጠገብ በሚገኘው በቁርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በእንግድነት እንደተቀመጠና ማድረግ የሚገባውን ሁሉ የእግዚአብሔር ሰው ጴጥሮስ እንደሚነግረው ገለጠለት:: (ሐ.ሥ10÷1-23) ለፊሊጶስም የጌታ መልአክ ተገልጦለት ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ለመገናኘት በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደሆነው መንገድ ሂድ አለው:: (ሐ.ሥ 8÷26)

በእነዚህ ሁለት ክፍሎች የምንማረው እግዚአብሔር ለሚፈልገው ለራሱ ሥራ በትክክል ምሪትን በመስጠት የት÷ መቼ÷ እንዴትና ከማን ጋር በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚገናኙና ምን ማድረግ እንዳለባቸው የራሱን መላእክት በመላክ የዳኑትን ሰዎች እንዲያገለግሉ ያደርጋል:: ጴጥሮስ በእሥር ቤት ታስሮ እያለ ለጴጥሮስ የተላከ መልአክ ልብሱን እንዲለብስ ነግሮት የእሥር ቤቱን ደጃፍ ካላለፈው በኋላ ከእርሱ ተለየ:: ጴጥሮስም ደቀ መዛሙርት ተሰብስበው ይፀልዩበት ወደ ነበረው ቤት በመሄድ በሩን

ሲያንኳኳ ሮዳ የተባለች የቤት ሠራተኛ ጴጥሮስ እንደሆነ በመገረምና በመደነቅ ነገረቻቸው ሌሎቹ ግን እርሱ አይደለም "<u>የእርሱ መልአክ ይሆናል</u> " አሉ:: በሐዋርያት ዘመን የነበሩ አማኞች የመልአክን አገልግሎት በደንብ የተረዱ ሲሆን ለያንዳንዱ አማኞች ክሰማይ የታዘዙ መላእክት አንዳልዋቸው ያምኑ ነበር:: ከዚህም አልፈው መላእክት ከሰማይ የሆነውን መልእክት ይዘው በሮቻቸውን እያንኳኩ እስከ ማገልገል እንደሚደደርሱ በማመን በአዲስ ኪዳን ያለውን የመላእክት አገልግሎት በደንብ የተረዱ ነበሩ::

ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ክብር ማገልገል ስትጀምር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና አሳብ ብዙ ሥራዎችን መሥራት እንድትችል ከዙፋኑ ላይ ካለው ከእግዚአብሔር መልእክትን እየተቀበሉ ወደ ምድር የሚላኩ የመላእክትን አገልግሎት ተጠቃሚ ትሆናለች:: አስቴር (የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ቅርጽ ይዛ ዘውዷን ስትደፋ የወርቁንም በትር ስትነካ የመላእክት አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በደንብ መገለጥ ይጀምራል:: አስቴር የወርቁን በትር ስትነካ በጠላቶችዋ መካከል በኃይል የመግዛት ሥልጣን ስላገኘች ባዘጋጀችው ግብዣ ላይ የመላእክት ምሳሌ የሆኑት ጃንደረቦች ናቸው ሃማን ይዘው ወደሚረገጥበት ግብዣ ያመጡት:: ይህንንም ቃሉ ሲገልጽልን :-

> "....የቤተ መንግሥቱም ጃንደረቦች ሃማን ወደ አስቴር ግብዣ ሊወስዱት በድንገት መጡ " (አስቴ 6÷14)

እንዲሁም በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን መረገጥና ድል መነሣት ያለባቸው ሰይጣንና ጭፍሮቹን በተጨማሪም በሰዎች ላይ አድረው የሚሠሩትን ጠንቋዮች÷ አስማተኞች÷ ምዋርተኞችና መናፍስት ጠሪዎች ወዘተ ከተሰጣት ሥልጣን የተነሣ ወደ ጉባኤዋ እየያዙ የሚያመጡ የመላእክት አገልግሎት ይገለጣል ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም በሥልጣንዋ ሥር ትረግጣለችና:: እንዲሁም ይዘውት የመጡትን ሃማን በአስቴር እግር ከተረገጠ በኋላ ከአስቴር እግር አንስተው ለመጨረሻ ጊዜ ርዝመቱ ሃያ ሁለት ሜትር በሆነ እንጨት ላይ የሰቀሉት የመላዕክት ምሳሌ የሆኑት ጃንደረቦች ናቸው ::

በዚህ መሠረት የዐማሌቅን አሠራር ከምድረ ገጽ የምታጠፋ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ናት:: ጌታ " <u>ከዚህ የሚበልጥ</u>

ታያላችሁ" ብሎ በተናገረው መሠረት በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ላይ የመላእክት አገልግሎት በብዛት ይገለጣል:: ብዙ አገልጋዮችና ምእመናን በመላእክት ተገልግለው አስደናቂ ምስክርነታቸውን የምንሰማበት ዘመን ሩቅ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ወደ ዘላለማዊ ቤትዋ ከመወሰድዋ በፊት በሰማይ ያሉት ቅዱሳን መላእክት በምድር ላይ በደንብ ያገለግልዋታል::

የብልፅግና ምርኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት

ሰይጣን በክርስቶስ ድል የተነሣ ነገር ግን በሰማያዊው ስፍራ ውስጥ ያለ ነው:: (ኤፌ 6÷12) ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሥልጣን የተሰጣት በሰማያዊው ስፍራም ያለችና በሰማያዊ ስፍራም ያለውን ሀብት ተጠቃሚ እንድትሆን የተጠራች ናት:: በተሰጣትም ሀብት ተጠቃሚ ለመሆን ግን ማንነትዋን ማወቅና የተሰጣትን ሥልጣን መረዳት አለባት:: በረከት ከላይ ከሰማይ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ነው:: ነገር ግን በረከታችንን እንዳንወርስ ሰይጣን ሥልጣን ስለሌለው ብዙ ክርስቲያኖችን እንደ አዳምና እንደ ሔዋን በሃይማኖታዊ አሳብ ከሸነገለ በኋላ የበረከቱ ተጠቃሚ እንዳንሆን በአመለካከት ቀንበር ያስረናል::

በእንድ አገር የምናያቸው ከንውኖች ሁሉ የመንፈላዊው ዓለም ውጤቶች ናቸው:: ለምሳሌ ለኢትዮጵያ የሚሆንን ብልፅግና እግዚአብሔር በሰማያዊ ስፍራ በቤተ ክርስቲያን በኩል ለቆላታል በየጊዜው የሚለዋወጡ ነገሥታት ባለሥልጣኖችና ትልልቅ የተማሩ ሰዎች ይህንን በረከት ለምድሪቱ ከሰማያዊው ስፍራ ማውረስ አይችሉም:: ምክንያቱም በሰማያዊው ስፍራ ሥልጣን የላቸውም በሰማያዊ ስፍራ ሥልጣን ያላት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት:: ቤተ ክርስቲያን የአመለካከት ለውጥ ኖርዋት ሥልጣንዋን እስካልተጠቀመች ድረስ የአንድ አገር ድህነት ማቆሚያ አይኖረውም:: ከዚህ በመቀጠል በዓለም ላይ ሦስት የመንፈላዊ ዓለም ክንውኖች በአገር ደረጃ እንመለከታለን:: ይህም :-

ሀ) ጣዖትን የሚያመልኩ አገሮች

በአገሪቱ ከሚመለኩ ጣዖት የተነሣ ከፍተኛ ብልፅግና ካገኙት አገሮች መካከል ትልቅ ምሳሌ የምትሆን ጥንታዊትዋ የኤፌሶን ከተማ ናት:: በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ላይ የኤፌሶን ከተማ በዘመኑ ታላላቅ የንግድ አገሮች መካከል አንድዋ እንደነበረች ተጠቅሰዋል:: የዚህ ከተማ ነዋሪዎች ሀብትና እጠቃላይ የአገሪቱ ብልፅግና የተገኘው የሕዝቡ ሁሉ አምላክ ከሆነችው አርጤሚስን ከተባለችው የሴት ምስል ጣዖት ነው:: ድሜጥሮስ የተባለ የዚህች ጣዖት አንጥረኛ የሀብታቸው ሁሉ ምንጭ መሆንዋን ሲገልፅ "... እኛ ሀብት የምናገኘው ከዚህ ሥራ እንደሆነ ታውቃላችሁ ይህ ጳውሎስ በሰው እጅ የተሠሩ ምስሎች አማልክት አይደሉም እያለ በኤፌሶን ..." ይላል (ሐ.ሥ 19÷25-26)

ሰይጣን ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠውን በሰማያዊ ስፍራ ያለውን በረከት ቤተ ክርስቲያን በሥልጣንዋ እንዳትጠቀም በመሸንገል ለራሱ ክብር ራሱን በሚያመልኩ አገሮች ላይ ያፈላል:: ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ለእርባቀን በዲያብሎስ ተፈትኖ ሲወጣ ዲያብሎስ ካቀረበለት ፈተናዎች አንዱ የዓለም ክብርና ነገሥታት ለእኔ ተሰጥቶኛል ወድቀህ ብትሰግድልኝ ለአንተ እሰጥሃለሁ የሚል ነበር:: ዛሬም ቢሆን ዲያብሎስ በግልም ሆነ በአገር ደረጃ ወድቀው በግልጽ የሚሰግዱለትን የዚህችን ዓለም ሀብት እየሰጠ በምድር ላይ ብቻ ተመቻችተው እንዲኖሩና ከዘላለም ፍርድ ነፃ እንዳይወጡ አፍኖ ይይዛቸዋል::

ጳውሎስ ግን ወደ ኤፌሶን ሲገባ የአገሪቱን የገቢ ምንጭ ከሰይጣን እንደሆነ ስላወቀ ሥልጣኑን በመጠቀም ከአርጤሚስ ምስል ጋር መንፈሳዊ ጦርነት ገጥሞ ብዙ አስማተኞችና ጠንቋዮች የገቢ ምንጫቸው የሆነውን የአስማት መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሕዝቡ ፊት አቃጠሉ:: የገንዘቡም ግምት ሃምሳ ሺህ ያህል ነበር:: ዛሬም የብዙ አገሮች የገቢ ምንጭ በብሔራዊ ደረጃ ከሚያመልኩት ከጣዖቶቻቸው ነው:: እውነተኛ ሐዋርያት በመጨረሻው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ሲነሱ እንደ ጳውሎስ በብዙ አገር ያሉትን የአገሪቱን ጣዖታት ገርስሰው ይጥላሉ:: ብዙ ሰዎችንም ወደ እውነተኛ መንገድ ይመራሉ::

ለ) ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙ አማኞች ያሉበት አገር

ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙ ቤተ ክርስቲያንና አማኞች ያሉባት አገር ክድኽነት ነፃ ናት:: አንዲት ኮሪያዊት እህት አንድ ጊዜ ስታጫውተኝ ኢትዮጵያውያንን አወዳቸዋለሁ የምወዳቸውም በሕፃንነቴ ኮሪያ በታላቅ ችግርና ድኽነት በነበረችበት ጊዜ ጋዜጣ ሳነብ ኢትዮጵያ ለኮሪያ ያደረገችውን እርዳታ አነበብኩ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ክፍተኛ ፍቅር ለኢትዮጵያዊያን አለኝ አለች:: ኮሪያ በችግር ውስጥ የነበረችው ከቅርብ ዓመታት በፊት መሆኑንና አሁን ኮሪያ ያደገችና የበለፀገች ከራስዋም አልፋ ሌሎችን የምትረዳና የምትደግፍ አገር መሆንዋን በመጨመር ገለፀችልኝ :: ረጂዋ ኢትዮጵያ ከድኽነት ያልተላቀቀችበት ተረጅዋ ኮሪያ የበለፀገችበት ምክንያቱ በሥልጣናቸው የሚጠቀሙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን ስላሉባት ብቻ ነው:: ስለዚህ የአመለካከት ለውጥ ኖሮአቸው ሥልጣናቸውን የሚጠቀሙ አገልጋዮችና ምእመናን ያሉባት አገር በአጭር ጊዜ ውስጥ ትበለፅጋለች::

ሐ) ሥልጣናቸውን የማይጠቀሙ አማኞች ያሉባት አገር

ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ያሉባት አገር አመለካከታቸው ግን ሃይማኖታዊ በሆነ ቀንበር የተያዙ አማኞች ያሏት አገር እስከ አሁን ከድኽነት መላቀቅ አልቻሉም :: ስለዚህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እረኞች ለሚመሩት ሕዝብ ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ቃል በመግለጥ የአመለካከት ለውጥ እንዲኖርና ሥልጣናቸውን መጠቀም እንዲችሉ የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው:: እንዲሁም በአገሪቱ ያሉ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እረኞች ደግሞ በአንድነት ለውጥ ኖሮአቸው በአገሪቱ ላይ ብልፅግና እንዲሆን ሥልጣናቸውን በመጠቀም የድኽነትን ቀንበር ሰብረው የሰማያዊውን ስፍራ በረከት ወደ ምድር ማምጣት ይችላሉ:: በምድራችን ላይ ብዙ የወርቅ፥ የነዳጅና የከበሩ ድንጋዮች ማዕድን እንዲወጡ፤ ብዙ ኢንዱስትሪ በምድራችን ላይ እንዲኖር፤ ታላላቅ ክርስቲያን ነጋዴዎች እንዲነሱ፤ ታሪካዊ የሆኑና ለዐይን የሚማርኩ ቦታዎች በደንብ ተይዘው አገሪቱ ከቱሪስት ከሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ እንድትሆን ለኢትዮጵያ ብልፅግና ሥልጣኑ የቤተ ክርስቲያን ነው:: ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ

የአመለካከት ተሐድሶ ኖርዋት ሥልጣንዋን ስትጠቀም በታላቅ በረከት ውስጥ ሆና የወንጌልን አገልግሎት ታገለግላለች:: እንደገናም ለአገሪቱም የበረከት ምንጭ ትሆናለች::

ነገር ግን ባለንበት ዘመን ስለ ሀብት ወይም ብልፅግና በአማኞች መካከል ብዙ ዓይነት አመለካከት አለ:: ብዙ አማኞች ስለ ብልፅግና ያላቸው አመለካከት በጣም ክእውነት የራቀ ነው:: ብልፅግና ስንል ሰው ሳይቸገር በእግዚአብሔርም ላይ ሳያጉረመርም የሚኖርበት በቂ ሀብት ማግኘት ማለት ነው:: እግዚአብሔር ሕዝቡን በመንፈሳዊ ነገር እንደሚያበለፅግ እንዲሁም በሥጋዊ ነገር በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ እንደሚያበለፅገን መጽሐፍ ቅዱሳችን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይነግረናል:: ባለንበት ዘመን ብዙ የእግዚአብሔርን ሥራ በተሳሳ ሁኔታ እንዳንሠራ የገንዘብ አጥረት ተፅእኖ እንደሚያደርግብን እሙን ነው:: ጌታ ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ የምሥራቹን ቃል እየሰበከ እያስተማረ ደዌንም እየፈወስ እርኩሳን መናፍስትንም ከሰዎች እያስወጣ ይዞር ነበር፤ "ብዙም ሴቶች ጌታን በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር" (ሉቃ 8÷1-3) ጌታን በገንዘባቸው የሚያገለግሉት ለአገልግሎቱ ገንዘብ ስለሚያስፈልገው ነበር::

ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ተፈጥሮአዊም ናት:: ሥጋን ለብሰን ስለሆነ መንፈሳዊውን ነገር የምናገለግለው የግድ ለሥጋችን በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ገንዘብ ያስፈልገናል:: አማኞች ለመብላት÷ ለመጠጣት÷ ለትንራንስፖርትና ጥሩ ቤት ለመሥራት ወዘተ እንዲሁም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ክትንሽ ወረቀት ማያያዣ እስፒል አንስቶ ትልልቅ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን ለመሥራት ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል:: አገልጋዮች ያላቸውን መንፈሳዊ ራእይ ተፈጥሮአዊ ወደ ሆነው ዓለም ለመግለጥ የግድ ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል:: ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ራእይ አለኝ ካለች የግድ ለሚታየው ዓለም ራእይዋን ለመግለጥ በገንዘብ መበልፀግ አለባት:: በየትኛውም አቅጣጫ ብንመለከተው መንፈሳዊውን አገልግሎት በዚህ ምድር ለማገልገል ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ማወቅ እንችላለን::

በሁሉ አቅጣጫ ገንዘብ እንደሚያስፈልገን ካወቅን የገንዘብ ድኾች ሆነን አንድንኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: በገንዘብ እጥረት የእግዚአብሔርን ሥራ እንደሚገባ አለመሥራት መርገም እንጂ በረከት አይደለም:: እግዚአብሔር ደግሞ ማንንም ሰው ለመርገም አልጠራም::

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብልፅግናን የሰጠ የማንንም በድኽነት መሠቃየት የማይወድ አሩሀሩህና ቸር አምላክ ነው:: ነገር ግን በረከትን የሚወርሱ ሰዎች እንደ ካሌብና ኢያሱ ማንነታቸውን የተረዱ ሰዎች ናቸው:: በረከትን ለመውረስ የማን ልጆች መሆናችንና አምላካችን ለኛ ያለውን መልካም አሳብ በሚገባ ማወቅ አለብን:: አሳቡንም የምናውቀው ደግሞ በቃሉ ነው ቃሉን በሚገባ ካላወቅን በትምህርት ነፋስ መወዛወዝን የማይቀር ነው:: እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ በየትም ስፍራ ለልጆቹ የድኽነትና የጉስቁልና አሳብ እንዳለው አይገልፅልንም:: ታዲያ እግዚአብሔር ያበለፅጋል ለብልፅግናም ጠርቶናል ብሎ መናገሩ እንደ ትልቅ ወንጀል የሚቆጠርበት ለምንድነው ? እግዚአብሔር እኮ በነገር ሁሉ እንደሚያበለፅገን ነው በቃሉ የሚነግረን:: ለሰዎች እግዚአብሔር በነገር ሁሉ በነፍስና በሥጋ ያበለፅጋል ወደ ጌታ ኑ ብለን ካልተናገርን ምኑን ወንጌል ሆነ ?

ወንጌል እንደሚያበለፅግ ምንም ጥርጥር የሌለው እውነት ነው:: ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ድኽነትን ለማስተማር ልዩ ፀጋ የተቀበሉ ይመስል የእግዚአብሔር ሕዝብ መበልፀግን እንዳያገኝ "ብልፅግና" የምትለውን ቃል ብቻ እየጠበቁ የሚቃወሙት ለምን ይሆን ? እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ተቃውሞአቸው ወንጌል አያበለፅግም ለማለት ከሆነ በጣም ከእውነት የራቀ ከአጋንንት የመጣ ትምህርት ነው የሚያስተምሩት:: ነገር ግን የምናገኘውን ብልፅግና እንደ እግዚአብሔር ቃል ከልተጠቀምንበትና ካልያዝነው ጣያት በመሆን ሌላ ጌታ ሆኖ እንዳይሰለጥንብን፤ አካሄዳችን ገንዘብን ያለመውደድ መሆን አንዳለበት፤ በገንዘብ ፍቅር ተይዘን ከቅድስና ጎዳና እንዳንወጣ ማፍቀር ያለብን ያበለፀገንን ጌታ እንጂ ብልፅግናውን እንዳልሆነ እነዚህን በመሳሰሉ ነጥቦች ላይ ከሆነ እነኚህን እውነቶች እንደሚገባ ማስተማር ነው የሚኖርብን እንጂ በተቀደሰ አሳብ አግዚአብሔር ያበለፅጋል ያለውን ሁሉ መቃወምና ማውገዝ አይኖርብንም::

አንዳንድ አገልጋዮችም ሆኑ ምእመናን ደግሞ "ብልፅግና" የሚለውን ቃል በመያዝ መሠረት በሌለው አሳብ በተጋነነ ሁኔታ ሁል ጊዜ በገንዘብ በልፅገውና ከብረው ለመታየት ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን ለራስ ክብርና ጥቅም ለመኖር ከሆነ ምኞታቸው የተሳሳተ ስለሆነ እንደ ቃሉ ሚዛናዊ በሆነ የብልፅግና አመለካከት አእምሮአቸው መታደስ አለበት::

ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው አመለካከት ነው:: የሕዝቡ መራብ÷ በጉስቁልና ማለፍ÷ አገልጋዮች

መንፈሳዊ ነገር እያላቸው በገንዘብ እጥረት አለማገልገላቸው፤ ቤተ ክርስቲያን የምታልፍበት ማንኛውም የገንዘብ ዕጥረት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው በዚህ ውስጥ እንድታልፍ እየተባለ አመለካከታችን ካለመታደሱ የተነሣ ድኽነትን አሜን ብለን መቀበላችን ነው:: ጌታ ኢየሱስ ገንዘብ መውደድ የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው አለ እንጂ በገንዘብ መጠቀምና መበልፀግ ኃጢያት አይደለም:: ብልፅግና ኃጢያት ነው ብለን ካመንን እንደ እግዚአብሔር ባለፀጋ አምላክ ስለሌለ ታዲያ እግዚአብሔርን ምን ልንለው ነው ?

በርግጥ ነው በገንዘብ ፍቅር እንዳንነደፍ ከእንደዚህ ዓይነት ጣያት አማኞች እንዲርቁ የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ቦታ ያስጠነቅቀናል እንጂ በድኽነት እንድንኖር መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም::

ዛሬ የብዙ ቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ችግር የሰይጣንን ሽንገላ በመስማት ማንነታቸውንና እግዚአብሔር የሰጣቸውን ነገር አለማወቃቸው ነው:: አለማወቅን የመሰለ ትልቅ ጉዳት የለም በተለይም በእግዚአብሔር ቃል አእምሮ ሙሉ በሙሉ ካልታደሰ እግዚአብሔር የሰጠውን በረከት መውረስ በጣም ከባድ ነው የሚሆነው:: ሰይጣን ሃይማኖታዊ መልክ ባለው ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል ፈጽሞ በራቀ የአመለካከት ቀንበር በመያዝ ብዙ ቅዱሳንን መድረስ ወደሚገባቸው ቦታ እንዳይደርሱ አድርጓቸዋል:: ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ መሥራት ሲችሉ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ያላቸው ራእይ ሳይፈፀም ብዙ ዓመታትን ይቆጥራሉ:: ቅዱሳን መልካም ኑሮን ለመኖር ሲችሉ በጥሩ ጥሩ ነገር መጠቀም እግዚአብሔርን እንደሚያሳዝነው እንደ ከባድ ኃጢያት በመቁጠር በድኽነት መኖር ፅድቅ በጉስቁልና መኖር በሰማይ ቤት የክብር አክሊል እንደሚያሰጥ በማሰብ ብዙ ዘመን እግዚአብሔር የሰጠንን በረከት ተጠቃሚ አልሆንም::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ግን ከእንደዚህ ዓይነት የአመለካከት ቀንበር ነፃ የወጣች ናት የሰይጣንን ራስ ቀጥቅጣ የህብቱ ባለቤት ትሆናለች:: የአይሁድ መሪ የሆነው ዘሩባቤል ጠላት ያፈረሰውን የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ የሆነውን ቤተ መቅደስ ወደ ቦታው ለመመለስ የተነሣ የተሐድሶ አገልጋይ ነበር:: ከዚህም የተሐድሶ አገልጋይ ጋር እግዚአብሔር ሊሠራ እንደተነሳና የሚጠብቀውም በረከት ምን እንደሆነ ሲገልፅለት :-

"በአጭር ጊዜ ውስጥ አንደገና ሰማይና ምድርን÷ ባህርንና የብስን አናውጣለሁ፤ መንግሥታትንም ገለባብጣለሁ፤ ሀብታቸውንም ሁሉ ወደዚህ እንዲመጣ አደርጋለሁ፤ ስለዚህም ቤተ መቅደሱ በሀብት የተሞላ ይሆናል:: በዓለም የሚገኘው ወርቅና ብር ሁሉ የእኔ ነው:: አዲሱ ቤተ መቅደስ ከፊተኛው ይበልጥ የተዋበ ይሆናል፤ እኔም በዚያ ለሕዝቤ ብልፅግናንና ሰላምን አሰጣለሁ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይህን ተናግሮአል::" (ሐጌ 2÷6-9)

በዚህ ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰማይንና ምድርን አናውጣለሁ የሚለው ቃል ይህ ያለንበት ሰማይና ምድር ሳይሆን የሚናገረው ስለ ስይጣን ራስ መቀጥቀጥ ነው:: ምክንያቱም ይህንን የሚታየውን ቢሆን ኖሮ የኋለኛው ቤተ መቅደስ ከብር አይኖርም ወደ ቤተ መቅደሱም የሚገባ ብልፅግናና ዘሩባቤል ራሱም አይኖርም ነበር:: ስለዚህ በሰማያዊ ስፍራ÷ በምድር÷ በባህርና በየብስ ያሉ አጋንንቶች የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የወርቁን በትር ስትነካ ይናወጣሉ:: ከዚህም የተነሣ መንግሥታት ሁሉ ይናወጣሉ ሀብታቸውም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል ቤተ ክርስቲያን በሀብት ትሞላለች::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በትክክል ሥልጣንዋን በመጠቀም ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ድኽነትንና ጉስቁልናን የምታጠፋ ናት:: በሐዋርያት ዘመን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን በመካከልዋ አንድስ አንኳን ችግረኛ አልነበረም::(ሐ.ሥ 4÷34) እንዲሁም በትንቢተ ዘካርያስ ላይ ማንነትዋንና ሥልጣንዋን አውቃ ስለምትመላለሰው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቃል ሲነግረን :-

"የይሁዳ ሰዎች ኢየሩሳሌምን ለመከላከል ይዋጋሉ፤ በዙሪያዋም ያሉትን የአሕዛብን መንግሥታት ሀብት ሁሉ ማርከው ይወስዳሉ፤ ከሚወስዱትም ምርኮ÷ ወርቅ÷ ብርና÷ የልብስ ዓይነት ስፍር ቁጥር የሌለው ይሆናል::"(ዘካ 14÷14)

የይሁዳ ሰዎች ኢየሩሳሌምን ከጠላት ለመከላከል ተዋግተው የብዙ ሀብት ባለቤት እንደሆኑ አስቴርም የአይሁድን ሕዝብ ለማዳንና ሃማን ለመቀጥቀጥ ስትዋጋ የብዙ ሀብት ባለቤት ሆነች:: ከዚህ በኋላ አስቴር የሃማን ራስ ቀጥቅጣ የወረሰችውን ሀብት ለመርዶክዮስ አሳልፋ ሰጠች::

"...አስቴርም መርዶክዮስን በሃማን ሀብትና ንብረት ላይ ኃላፊ አድርጋ ሾመችው:: " (አስቴ 8÷2)

ቤተ ክርስቲያን ወይም አማኞች መርሳት የሌለባቸው ትልቅ ነገር ቢኖር ጌታ በሰጣቸው ሀብት ላይ ኃላፊው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ነው:: ቤተ ክርስቲያን ላለችበት አገር ብልፅግና ከፀለየች በኋላ እግዚአብሔር ለአገሪቱ የሰጠውን ብልፅግና አግባብ በሆነ መንገድ እንድትጠቀምበት ለነገሥታትና ለባለሥልጣኖች መጠቀሚያ እንዳይሆን አስቴር በበዘበዘችው ሀብት ላይ መርዶክዮስን እንደሾመች ቤተ ክርስቲያንም የሀገሪቱን ሀብት መንፈስ ቅዱስ እንዲቆጣጠረው በመፀለይ ለመንፈስ ቅዱስ አሳልፋ መስጠት አለባት::

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ቀንድዋን ብረት ጥፍሮችዋን ነሐስ አድርጎ የበዘበዘችውን ሀብት እንደገና ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ማድረግ እንዳለባት የእግዚአብሔር ቃል ይህንን ያረጋግጥልናል :-

"የጽዮን ልጅ ሆይ÷ ቀንድሽን ብረት÷ ጥፍርሽን ናስ አደርጋለሁ ተነሽ አሂጂ፤ ብዙ አሕዛብን ታደቂያለሽ ትርፋቸውንም ለእግዚአብሔር÷ ሀብታቸውን ለምድር ሁሉ ጌታ ትቀድሻለሽ :: (ሚክ 4÷13)(የቀ.ት)

በአንደኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ ላይ ደግሞ ዳዊት ስለ ብልፅግና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሲገልፅልን :-

— ብልፅግና ሁሉ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው::
— ያገኘነው ብልፅግና ሁሉ በእጃችን ሆኖ የእግዚአብሔር ነው::
— ብልፅግና ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር መዋል አለበት::

እንግዲህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የአመለካከት ለውጥ ስለሚኖራት በሥልጣንዋ በመጠቀም ሰይጣን በማጭበርበር የወሰደውን ሀብት በማስመለስ የገንዘብ ዕጥረት ሳይኖርባት ከሰማይ የተቀበለችውን መንፈሳዊ ራእይ ወደሚታየው ዓለም የምትገልጥ ትሆናለች::

ም ዕ ራ ፍ ዘ ጠ ኝ

የቀለበቱ ማጎተም

ለመጨረሻዋ ዘመን

ቤተ ክርስቲያን መመለስ

የቀለበቱ ማኅተም መመለስ

"ንጉሡም የራሱ ማኅተም ያለበትን፣ ከሃማን ጣት ወልቆ እንዲመለስ የተደረገውን ቀለበት ለመርዶክዮስ ሰጠው..." (አስቴ 8÷2)

ሰይጣን ከአዳምና ከሔዋን በሽንገላ ሥልጣናቸውን እንደወሰደ ሁሉ የአስጢን (የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን) ለንጉሡ አምቢ እንድትል አደረገና አርስዋም ከክብር ከኅደለች በኋላ ሰይጣንን በቁጥጥርዋ ሥር የምታደርግ ቤተ ክርስቲያን ስላልነበረች ሰይጣን በቀለበቱ ማኅተም በንጉሡ ስም ሃይማኖታዊ መልክ አስይዞ ዐዋጅ ያላውጅ እንደነበር ቀደም ብለን ተመልክተናል:: በአስቴር ምዕራፍ ስምንት ቁጥር ሁለት ላይ ግን አስቴር የወርቁን በትር ስትነካ የሰይጣንን ራስ ስትቀጠቅጥ ማኅተም ያለበት የወርቁን ቀለበት ወደ ቤተ ክርስቲያን መመለሱን ይነግረናል:: ይህም ማለት ሰይጣን እስክዛሬ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የራሱን አሠራር በማስገባት በንጉሡ ስም ከእግዚአብሔር ያልሆነ የቃሉ ፍቺ÷ ሥርዓትና ወግ እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል የማይደግፈውን መንፈሣዊ አሠራርና አገዛዝ ወደ ቤተ ክርስቲያን በማስገባት ቤተ ክርስቲያን መድረስ ወዳለባት ክብር እንዳትደርስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሲዋጋ ኖሯል:: ከአሁን በኋላ ግን የዚህ ቀለበት ማኅተም ባለቤት የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች የዐማሌቅ ረቂቅ አሠራር ዋጋ የለውም:: እውነተኛውን አገልግሎት ታገለግላለች የሚሸቃቀጥም ነገር የለም:: ምክንያቱም አስቴር በወርቅ ድንክ አልጋ ላይ ስለምትቀመጥ ከመሠረቱ የሚፈነጥቀውን መገለጥ ስለምታገኝ ከሰማይ የመጣውን እውነተኛ አላብ ብቻ ታገለግላለች::

ዘሩባቤል እንደ አስቴር የፈረሰውን የእግዚአብሔር ዕቅድ ለመገንባት የተነሣ የተሐድሶ አገልጋይ ነው ወይም የመጨረሻውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይዘው የሚነሱ አገልጋዮች ምሳሌ ነው:: ስለዚህ በእርሱ አገልግሎት ውስጥ በመጨረሻው ዘመን የሚደረገውን ትንቢታዊ ቃል እናያለን:: ዘሩባቤል ሥልጣኑን ስለሚጠቀም ሰማይና ምድር ይናወጣሉ ÷ የብዙ ምርኮ ባለቤት ሆኖአል፣ ከፊተኛው ቤት ክብር ይልቅ የኋለኛው ቤት በክብር

ተሞልቶአል፤ አንዲሁም የማኅተሙ ቀለበት ባለቤት ሆኖአል:: ይህንን የእግዚአብሔር ቃል ሲያረጋግጥልን:-

"አገልጋዬ ዘሩባቤል ሆይ ! በዚያን ቀን አኔ አንተን ወስጄ <u>በእኔ ስም መግዛት እንድትችል</u> አነግሥሃለሁ፤ እኔ አንተን መርጨሃለሁ፤ አንደ <u>ማኅተም ቀለበቴ አደርግሃለሁ</u> ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር::" (ሐጌ 2÷23)

ዮሴፍ በግብጽ ውስጥ ሥልጣን ይኖረው ዘንድ ሕዝቡንም ያስተዳድር ዘንድ በሥልጣን ክእኔ በቀር የሚበልጥህ የለም በማለት "ንጉሡ የሥልጣኑ ምልክት ያለበትን የማኅተም ቀለበት ከጣቱ አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገው ::" (ዘፍ 41÷42) ዮሴፍ በግብጽ አገር ከንጉሡ በቀር በሥልጣን የሚበልጠው አንዳልነበረ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የወርቁ ቀለበት ባለቤት ስትሆን በዚህ ምድር ከእግዚአብሔር አብ፤ወልድ፤ መንፈስ ቅዱስ በቀር በመንፈሳዊ ሥልጣን የሚበልጣት የለም:: ስለዚህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከንጉሡ የማኅተም ቀለበት የተነሣ ትክክለኛ አገልግሎት ታገለግላለች:: ማንነትዋና የምትሠራውን እንዲሁም የምታስተምረውን በደንብ ስለምታውቅ ባገኘችው የወርቅ ማኅተም ቀለበት የአመለካከት ለውጥን ታመጣለች::

የአመለካከት ተሐድሶ ማግኘት

እግዚአብሔር ሕዝቡን ወይም ቤተ ክርስቲያንን ወደ ሙሳቱ ማስገባት ይፈልጋል:: ነገር ግን አመለካከታቸው ካለመታደሱ የተነሣ ብዙ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከበረከቱ የጎደሉ ናቸው:: ነህምያ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው:: የፈረሰው የኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከተሠራ በኋላ ቅጥሩ ግን ገና ስላልተሠራ ጠላት በቀላሉ ወደ ኢየሩሳሌም ይገባና ይወጣ ነበር:: የተሠራው ቤተ መቅደስ ዳግም የተወለደው መንፈሳችንን፤ የፈረሰው ቅጥር ደግሞ መታደስ ያለበትን የአእምሮ አመለካከታችንን ይመስላል:: ስለዚህ ነህምያ የፈረሰውን የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለማደስ በንጉሡ አርጤክስስ ፈቃድ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣ ነው:: ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ቅጥርዋ እንደፈረሰው እንደ ኢየሩሳሌም ሆናለች:: ሰዎች ዳግም ተወልደው ይድናሉ መንፈሳቸው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይሆናል ነገር ግን የአእምሮአቸው አመለካከት እንደሚገባው እንደ እግዚአብሔር ቃል ካለመታደሱ የተነሣ ቅጥር የሌላት

ጠላት በቀላሉ የሚገባባትና የሚወጣባት ሆናለች:: ስለዚህ በንጉሡ ፈቃድ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ የሆነው ነህምያ የፈረሰውን የቤተ ክርስቲያን ቅጥር ሊያድስ የተነሣበት ዘመን ነው:: ይህ ዘመን የተሐድሶ ዘመን ነውና::

የአመለካከት ተሐድሶ አሠራር በደንብ እንዲገባን መንፈስ ቅዱስ በአማኙ ሕይወት ከመጀመሪያ ጀምሮ የሚሠራውንና እንዲሁም የእእምሮ መታደስ ወይም የአመለካከት ለውጥ የማይፈልጉ ሰዎች ምን ያህል ለስይጣን አሳብ ቅርብ እንደሆኑ በቅድሚያ ከነህምያ መጽሐፍ እንመለከታለን::

"እኔም ወደ ኢየሩሳሌም ጕዞየን ቀጠልሁ፤ እስከ ሦስት ቀንም ድረስ÷ ለኢየሩሳሌም ስለማከናውነው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ለእኔ የገለጠልኝን ምስጢር ለማንም ሳልናገር ቆየሁ፤ ከዚያም በኋላ ከጓደኞቼ ጥቂቶቹን በማስከተል በእኩለ ሌሊት ተነሥቼ ሄድሁ፤ የነበረን የጭነት እንስሳ አኔ የተቀመጥሁበት አህያ ብቻ ነበር ፤ <u>በሸለቆ ቅጽር በር ወጥቼ የዘንዶ ምንጭ ተብሎ</u> የሚጠራውን ስፍራ በማለፍ በስተ ደቡብ ወደሚገኘው <u>የጕድፍ መጣያ</u> ተብሎ ወደሚጠራው ስፍራ ሄድሁ፤ <u>ጊዜውም ገና ሌሊት ነበር</u> ፤ በማልፍበትም ጊዜ የፈራረሱትን የከተማይቱን ቅጽሮችና በእሳት የወደሙትን የቅጽር በሮች ጎበኘሁ:: ቀጥሎም ከከተማይቱ በስተ ምሥራቅ በኩል በሰሜን ወደሚገኘው <u>"የውኃ ምንጭ ቅጽር በር"</u> ተብሎ በሚጠራው ስፍራና <u>ወደ ንጉሡ ኩሬ ሄድሁ፤</u> ነገር ግን ተቀምጬበት የነበረው አህያ <u>የፍርስራሹን ክምር ለማለፍ የሚያስችለው መንገድ ማግኘት አልቻለም</u>:: ስለዚህ ሌሊቱን ወደ ቄድሮን ወንዝ በመውረድ ቅጽሮችን እየጐበኘሁ አልፌ <u>ሄድሁ፤ በመጨረሻም በዚያው በመጣሁበት መንገድ ተመልሼ በሸለቆው ቅጽር በር በኩል ወደ ከተማይቱ ገባሁ ::"</u>

(ነህ 2÷11-15)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታስራ የነበረችውን አህያ ፈታችሁ እምጡልኝ ለምን ትፈትዋታላችሁ ቢልዋችሁ ለጌታ ታስፈልገዋለች በሉ (ማቴ21÷1-5) ምክንያቱም እርሱ በአህያይቱ ለመክበር ስለፈለገ ነው:: እንዲሁም ነህምያ የተቀመጠባት አህያ ከታሠሩበት ተፈትተው የሚመጡትን አማኞች ምሳሌ

ናት:: ይህቺ አህያ ነህምያ ወዳሰበው የእግዚአብሔር ዕቅድ ለመድረስ ማለፍ የሚገባትን ሁሉ ከዚህ በታች እንመለከታለን:: ይህም :-

ሀ) የዘንዶው ምንጭ

"<u>በሸለቆው ቅጽር በር ወጥቼ የዘንዶ ምንጭ ተብሎ</u> የሚጠራውን ስፍራ በማለፍ... " (ነህ 2÷13)

ከላይ ባለው ጥቅስ ሁለት ነገሮችን እናያለን የሸለቆ ቅጽርና የዘንዶው ምንጭ:: አዳምና ሔዋን በስይጣን ሽንገላ ከኤደን ገነት ከወጡ በኋላ የጠበቃቸው የሸለቆ ሕይወት ነው:: እግዚአብሔር ከሚገኝበት ስፍራ እግዚአብሔር ወደማይገኝበት ሸለቆ ወረዱ:: በኤፌሶን ሁለት ከአንድ እስከ ሁለት ላይ በሰፈረው መሠረት የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ስለተለዩ የዚህ አለም ገዢ ሰይጣን ሁለንተናቸውን በመቈጣጠር በእርሱ ፈቃድ እንደፈለገ ይመራቸው ጀመር:: ከዚህ የተነሣ የሚያደርጉት ሁሉ ከዘንዶ ምንጭ ጋር የተያያዘ ሆነ:: ሰዎች በጌታ እምነው ካልዳኑ በቀር ጌታ እንዳለው የዲያብሎስ ልጆች ናቸው፤ የሚጠጡትም ከአባታቸው ከዲያብሎስ ምንጭ ነው:: ስለዚህ አማኞችን መንፈስ ቅዱስ ያወጣቸው ከወደቁበት ሸለቆና ከዘንዶ ምንጭ ነው <u>"እርሱ ከጨለማው ሥልጣን አዳነን"</u> (ቆላ 1÷13) መንፈስ ቅዱስ በአህያይቱ ላይ እርሱ ሊከብርባት የሸለቆውን በርና የዘንዶውን ምንጭ ካሳለፉት በኋላ የወሰዳት ወደ ጉድፍ መጣያ ስፍራ ነው::

ለ) የጉድፍ መጣያ ስፍራ

"... በስተ ደቡብ ወደሚገኘው <u>የጕድፍ መጣያ</u> ተብሎ ወደሚጠራው ስፍራ ሄድሁ... " (ነህ 2÷13)

ጉድፍ ማለት ቁሻሻ ማለት ነው:: መንፈስ ቅዱስ አህያዋን ይዞ የሄደው ቆሻሻዋን ወደምታራግፍበትና ንፁህ ወደምትሆንበት ወደ ጉድፍ መጣያ ነው:: ይህ ጉድፍ መጣያ አማኞች ጌታን ሲቀበሉ ጉድፍ (ኃጢያት) የሚጥሉበት የክርስቶስ መስቀል ነው:: ሰው በኃጢያት ከወደቀ በኋላ በጉድፍ የተሞላ የቆሸሸ ስለሆነ ይህንን ኃጢያታችንን ጌታ ኢየሱስ ሊያነሳልን እርሱ በመስቀል ላይ ሞተ:: ስለዚህ "እኛ ከክርስቶስ ጋር በመተባበር የእግዚአብሔር

ጽድቅ እንድንሆን እግዚአብሔር ኃጢያት የሌለበትን ክርስቶስን የእኛን ኃጢያት እንዲሸክም አደረገው::" (2ቆሮ 5÷21)

ስለዚህ በእንጨት ላይ የሚሞት የተረገመ ነው ተብሎ እንደተፃፈ ክርስቶስ ስለኛ እርግማን ሆኖ እርኩሰታችንን÷ ነውራችንን÷ ትዕቢታችንን÷ ቅናታችንን÷ ምቀኝነታችንን ወ.ዘ.ተ በእርሱ ላይ አኖረው:: ስለዚህ የኛን ጉድፍ ማራገፊያ ሆኖ እኛን በደሙ አነፃን:: እንግዲህ በክርስቶስ የሆኑ ሁሉ በደሙ ነፅተዋል:: ነገር ግን አህያዋ ይህን ካለፈች በኋላ "ጊዜውም ገና ሌሊት ነበር" (ነህ 2÷13) የሚል ቃል እናገኛለን፤ ገና ሙሉ ለሙሉ ብርሃን አይታይም ነበር፤ የጨለማ ነገር ሰልጥኖ ነበር:: ነህምያ በዚሁ ሌሊት የፈረሰውን ቅጽር ነበኘ:: የፈረሰውን ቅጽር በሮችንም ተመለከተ የተቀመጠባትም አህያ ከሸለቆና ከዘንዶ ምንጭ ድናለች ቆሻሻዋን በመስቀሉ ላይ አራግፋ በክርስቶስ ደም ነፅታለች:: ነገር ግን በመንገድ የጨለማ ነገር ይታይ ነበር:: ስለዚህ ነህምያ (መንፈስ ቅዱስ) ወደ ፍፁም ሙላትና ወደ እግዚአብሔር ብርሃን ወደ መጨረሻው ዕቅድ ሊያደርሳት ጉዞውን ቀጠለ::

ሐ) የንጉሡ ኮሬ ወይም መዋኛ

> "ቀጥሎም ከክተማይቱ በስተ ምስራቅ በኩል በስሜን ወደሚገኘው የውኃ ምንጭ ቅጽር በር ተብሎ በሚጠራው ስፍራና <u>ወደ ንጉሡ ኩሬ</u> ሄድሁ፤ ነገር ግን ተቀምጨበት የነበረው አህያ የፍርስራሹን ክምር ለማለፍ የሚያስችለው መንገድ ማግኘት አልቻለም::"
>
> (ነህ 2÷14)

ወደ ንጉሡ ኩሬ የሚለው የቀደመው ትርጉም <u>"የንጉሡ መዋኛ"</u> ይለዋል:: መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ይዞ መሄድ የሚፈልገው ወደ ሙላቱ ነው:: ወደ ንጉሡ መዋኛ ነው:: በበረከት÷ በቅባት በታላቅ የእግዚአብሔር ክብር ከንጉሡ ጋር እንድንዋኝ ወደ ንጉሡ የመዋኛ ስፍራ ለማድረስ ይፈልጋል:: ይህቺን አህያ ከጨለማው ሥልጣን አድኖ በክርስቶስ የመስቀሉ ሥራ አሳልፎ እግዚአብሔር ወዳቀደላት ሙላት ውስጥ ሊያደርሳት ተቀምጠ ይመራት ነበር:: ነገር ግን ተቀምጠባት የነበረው አህያ ወደ ንጉሡ መዋኛ ለመድረስ የፍርስራሹን ክምር ለማለፍ የሚያስችለውን

መንገድ ለማግኘት አልቻለችም:: ነህምያ ሲናገር እኔ ማለፍ አልቻልኩም አላለም:: <u>"አህያዋ የፍርስራሹን ክምር ለማለፍ የሚያስችለውን መንገድ ለማግኘት አልቻለችም"</u> ነው ያለው:: አህያዋ መንገድ ነው እንጂ የጠፋት የፍርስራሹን ክምር ለማለፍ ትችል ነበር:: አህያዋ ቅጽሩን እንዳታልፍ በንጉሡ መዋኛ እንዳትዋኝ ትልቅ እንቅፋት የሆነባት መንገዱን አለማወቅዋ ነው:: አለማወቅ ያጠፋል "ሕዝቤ እውቀትን ከማጣት ጠፍቶአል" ሕዝቤ የሚለው የዳኑትን እንጂ ያልዳኑትን አይደለም:: የእግዚአብሔር ሕዝብ ለማወቅ መማር አለበት ለመማር ደግሞ ትሑት መሆን ያስፈልጋል:: የእግዚአብሔር ቃል ንጉሥሽ ትሑት ሆኖ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ይመጣል ይላል:: (ዘካ9÷9) ታላቁ አምላካችን ትሑት ሆኖ በእኛ ላይ ከተቀመጠ እኛ ትሑት ሆነን የእርሱን ነገር የማንቀበልበት ምክንያት ትዕቢት በውስጣችን ሲኖር ብቻ ነው:: ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት የተራቆትን ነን (ዕብ4÷13) እያንዳንዳችን በንጉሡ መዋኛ እንዳንዋኝ ወደ አዲስ ነገር እንዳንገባ አእምሮአችን የተያዘበትን ቀንበር መንፈስ ቅዱስ ያውቀዋል:: ብዙዎቻችን ከተቀመጥንበት ወንበር መውረድ ስለሚያቅተን ትሑት ሆነን መማር አንፈልግም:: ካለኛ ማን አለ ማለታችን በሰዎች ዘንድ መታወቃችን የመድረክ አገልጋዮች በመሆናችን ትሑት ሆነን እንዳንማር ዕንቅፋት ሆኖብናል በመንፈስ ቅዱስም ላይ ተኩራርተናል::

የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድ አህያዋን ወደ ንጉሡ መዋኛ ለማድረስ ነው:: ነገር ግን መንገዱን ለማወቅ መማር ለመማር ደግሞ ትሑት መሆን እንዳለባት አላወቀችም ነበር:: ስለዚህ ወደ ንጉሡ መዋኛ ለመድረስ አህያይቱ የሚያስፈልጋት አንድ ነገር ብቻ ነው <u>እርሱም ትሑት ሆኖ እግዚአብሔር ለዘመኑ የገለጠውን ወደ ንጉሡ መዋኛ የሚያደርሰውን የእግዚአብሔርን የቃሉን መገለጥ ማግኘት ብቻ ነው::</u> የዛሬ አርባና ሠላሳ ዓመት ባገኘነው የእግዚአብሔር የቃሉ መገለጥ ብቻ መኖር አንችልም:: ላለንበት ለዘመኑ የሚመጣው የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ያስፈልገናል:: አህያ አምብርት የለውም ይባላል ዝም ብሎ ይበላል ጠገብኩ አያውቅም ልክ እንደዚህ እንድንሆን ጌታ ይፈልጋል:: አንዳንድ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ነገር ለማስፋፋት ምንም አምብርት የላቸውም:: ለዘመኑ ከእግዚአብሔር ለሚመጣው አሳብ ግን ባለ አምብርት ናቸው ፤ ጠገብኩ ባሮች ናቸው፤ በድሮ በሬ ነው ማረስ የሚፈልጉት የሚበቅለውን አዲሱን ነገር ለመፈለግ ምንም ጥማት የላቸውም::

የተጠራነው በንጉሡ መዋኛ እንድንዋኝ ነው:: ነገር ግን የዘመኑን የመንፈስ ቅዱስ ዕቅድና መገለጥ በትሕትና በመማር አመለካከታችን እስካልተለወጠ ድረስ በንጉሡ መዋኛ መዋኘት በፍፁም አንችልም፤ ወደ ንጉሡ መዋኛ የመግቢያ ትኬት ትሑት ሆኖ የራስን አመለካከት በመንፈስ ቅዱስ አመለካከት ማደስ ብቻ ነው:: ነገር ግን አመለካከታችን ሙሉ በሙሉ በእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃልና በዘመኑ የእግዚአብሔር ዕቅድ ካልታደሰ ከዚህ በታች እንደምንመለከተው ከንጉሡ መዋኛ በጣም የራቅን ለሽለቆ በር የቀረብን እንሆናለን::

መ) የሽለቆ ቅጽር በር

"ስለዚህ ሌሊቱን ወደ ቂድሮን ወንዝ በመውረድ ቅጽሮችን እየጎበኘሁ አልፌ ሄድሁ፤ <u>በመጨረሻ በዚያው በመጣሁበት መንገድ ተመልሼ በሽለቆው ቅጽር በር በኩል</u> ወደ ከተማይቱ ገባሁ::"

(ነህ 2÷15)

መንፈስ ቅዱስ አህያዋን ይዞ የተነሣው ወደ ንጉሡ መዋኛ ለመድረስ ነበር:: ነገር ግን ወደ ንጉሡ መዋኛ ለመግባት አመለካከትዋን ስላላደሰች የፍርስራሹ ክምር ስለያዛት መጣል የሚገባትን ጥላ ማደስ የሚገባትን ስላላደሰች እንደገና በሌሊት ጨለማው ዙሪያዋን ከቦት ተመልሳ በሽለቆው ቅጽር በር በኩል አለፈች:: አህያዋ በመጀመሪያ የሽለቆውንና የዘንዶውን ምንጭ አልፋለች፤ በጉድፍ መጣያም በማለፍ ነፅታለች፤ ያቃታት ነገር ቢኖር የንጉሡን መዋኛ መቀበል ብቻ ነበር:: ከዚህ የተነሣ የሽለቆውን ሕይወት ለመኖር መሻሻል የሌለበትን ከርስትና መረጠች:: አህያዋ በሽለቆ እንጂ በዘንዶ ምንጭ ተመልሳ አላስፈችም:: ነገር ግን ልናየው የሚገባን ነገር ሽለቆው ለዘንዶው ምንጭ በጣም ቅርብ መሆኑ ነው (ነህ 2÷13) ስለዚህ መታደስን የማይፈልጉ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምእመናን ለዘንዶው ምንጭ የቀረቡ ናቸው:: ልክ የኢየሩሳሌም ቅጽር ፈርሶ ጠላት እንደፈለገ ይወጣና ይገባ እንደነበር የነዚህ ሰዎች አእምሮ ካለመታደሱ የተነሣ ጠላት በቀላሉ አእምሮአቸውን በመጠቀም የራሱን አሳብ ይፈፅማል::

ብዙ የዳኑ ክርስቲያን የአእምሮ መታደስና የአእምሮ ለውጥ በእውነተኛው የእግዚአብሔር የቃሉ ፍቺ ካለማግኘታቸው የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያቀርቡት አሳብና የሚሠሩት ሥራ ከእግዚአብሔር

የመጣ ሳይሆን አመለካከታቸው ካለመታደሱ የተነሣ በሽለቆ ውስጥ ስላሉ ከንጉሡ አሳብ በጣም ስለራቁ ለዘንዶ ምንጭ ቅርብ ስለሆኑ የሚያስተናግዱት የዘንዶውን አሳብ ነው:: ሌሎቹም እንዲቀበልዋቸው የሚፈልጉት ያንኑ አሳባቸውን ነው:: ሌላው ቀርቶ በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የአመለካከት ለውጥንና የአእምሮ መታደስን ያላገኙ ሰዎች ካሉ ለዘንዶ ምንጭ ቅርብ ስለሚሆኑ ቤተ ክርስቲያንን መምራት የሚፈልጉት ከዘንዶው ምንጭ ባገኙት የአእምሮ አሳብ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ችግርና መለያየትን ይፈጥራሉ:: የሽለቆው በር የሚገኘው በስተ ደቡብ ሲሆን የንጉሡ መዋኛ ደግሞ የሚገኘው በስተ ሰሜን እንደሆነ እንዲሁም አመለካከታቸው በእግዚአብሔር ቃል ባልታደሰ ሰዎችና አመለካከታቸው በታደሱ ሰዎች መካከል እንደዚሁ ከፍተኛ ልዩነት አለ ሰሜንና ደቡብ ናቸው:: በምንም ነገር አይግባቡም:: በሽለቆው ውስጥ ካለን የእግዚአብሔር ድምፅና ራእይ እንዲሁም የእግዚአብሔርን የዘመኑ አሳብ ማወቅ አንችልም:: ስለዚህ መጣል ያለብንን ጥለን ትሑት ሆነን ለመማር በእግዚአብሔር ቃል የፈረሰውን ቅጥራችንን ቀጥረን በንጉሡ የበረከት መዋኛ ውስጥ መዋኘት ይሻለናል:: ንግሥት አስቴር ግን አመለካከትዋን በማደስ ወደ ንጉሡ መዋኛ ስለገባች ሌሎችን ወደ በረከት ሙላት ለማስገባት የአመለካከት ለውጥን ለማምጣት ወደ ንጉሡ ቀረበች::

ንግሥት አስቴር የወርቁን ማኅተም ቀለበት ባለቤት ስትሆን በንጉሡ እግር ላይ ወድቃ በማልቀስ ጥያቄ አቀረበች (አስቴ8÷3-6) ጥያቄዋም ዐማሌቁ ሃማን ብዙ አይሁዳውያንን ለማጥፋትና የእግዚአብሔርን ዕቅድ ለማበላሸት በንጉሡ ስም የታወጀውን የዐዋጅ ነጋሪዎችን ትዕዛዝ እንዲሻርላት ነበር:: ምክንያቱም በዐማሌቁ ሃማን ዐዋጅ ምክንያት ብዙ ሰዎች ያላቸው መንፈሳዊ አመለካከት የተበላሸ ስለሆነ የነዚህን ሰዎች አመለካከት ተለውጦ ወደ ንጉሡ መዋኛ ደርሰው የንጉሡ የከብሩ ማንፀባረቂያ እንዲሆኑ የአስቴር ከፍተኛ ዓላማ ስለሆነ ሰዎች እንዲድኑ እንጂ እንዲጠፉ ስለማትፈልግ "የኔ ፍላጎት እኔም ሆንኩ ወገኖቼ በሕይወት መኖር እንድንችል ነው" በማለት ለንጉሡ ፍላጎትዋን አስታውቃለች:: (አስቴ 7÷3)

ከዚህም የተነሣ ላቀረበችው ጥያቄ ንጉሡ "እነሆ ሃማን በአይሁዳውያን ላይ ስለፈፀመው ሤራ በእንጨት ላይ እንዳሰቀልኩትና ህብቱን ሁሉ ለአስቴር እንደሰጠሁ የሚታወስ ነው::" (አስቴ 8÷7) እዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን አስቴር የሰይጣንን ራስ በእግርዋ እንድትቀጠቅጥና

በረከትን እንድትወርስ ለማድረግ ንጉሡ አልተቸገረም ምክንያቱም ከልጅነትዋ ጀምሮ የአስቴር አመለካከት የተበላሸ ስላልነበረ ለእርስዋ በረከቱን ለማውረስ ለንጉሡ ቀላል ነበር:: በሌሎች ውስጥ ያለውን አመለካከት ግን ለመቀየር ንጉሡ ሲነግራት "ይሁን እንጂ የቤተ መንግሥቱ ማኅተም ያለበትና በንጉሡ ስም የተላለፈ ዐዋጅ ሊለወጥ አይችልም... " አላት:: (አስቴ 8÷8)

ንጉሡ ሃማን በንጉሡ ስም ያወጀውን ዐዋጅ ሊለወጥ አይችልም ሲል ከሃማን ዐዋጅ የተነሣ በሰዎች ውስጥ ያደረውን አመለካከት በቀላሉ ሊለወጥ እንደማይችል በመግለፅ ለአስቴር ነገራት:: ምክንያቱም ብዙ ሰዎች ዐዋጁን የተቀበሉት በንጉሡ ስም ስለሆነ ነው:: አንዳንድ ሰዎች የተሳሳተ አመለካከት ያለው እምነት አላቸው ከየት አመጣኸው ሲባሉ አገልጋይ እከሌ ያስተማረኝ ነዋ ይላሉ:: እስከዛሬ ድረስ ቤተ ክርስቲያን በንጉሡ ስም እያስተላለፈች ያለችው የእግዚአብሔር አሳብ የሌለባቸው ከእውነት የራቁ ሃይማኖታዊ ወግና ሥርዓት ብቻ የሆኑ ምእመናኑ ከአእምሮአቸው ለማውጣት የሚከብዳቸው፤ አንዲሁም ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ብዙ ዓመት የመሩበትን የአሠራር ሥርዓት ለመለወጥ፤ እግዚአብሔር በዘመናችን የሚሠራው ሥራና የተቀቡትን አገልጋዮች ለመቀበል፤ ከእግዚአብሔር የዘመኑ ዕቅድ ጋር ለመሮጥ አስቀድመው ከተሞሉት ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የተነሣ ለመቀበል በጣም ያቅታቸዋል:: ምክንያቱም አንድ ጊዜ ለውጥ እንዳያገኙ በዐማሌቁ አሠራር በንጉሡ ስም ስለተነገራቸው በአእምሮአቸው ውስጥ እንደ ሙጫ ነው የተጣበቀው:: በጣም አድካሚና አስቸጋሪ ነገር ቢኖር አንዴ ውሸትን እውነት ነው ብለው የተቀበሉትን ሰዎች አመለካከት በእውነት ለመለወጥ ያለው ትግል ነው :: ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ችግር የሚፈጥሩትና ለእግዚአብሔር ሥራ ዕንቅፋት የሚሆኑት አመለካከታቸው የተበላሸና ውሸትን እውነት ነው ብለው የተቀበሉ ሰዎች ናቸው::

ስለዚህ ንጉሥ አርጤክስስ ለአስቴር መፍትሔውን ሲገልፅላት እንደነዚህ ዓይነቶች ውሸትን እውነት ነው ብለው የተቀበሉ ሰዎች አመለካከት መለወጥ የሚቻለው <u>ዐዋጅን በዐዋጅ</u> በመሻር እንደሆነ እንዲህ ሲል ይገልፅላታል :-

" ... ሆኖም እናንተ በበኵላችሁ የፈለጋችሁትን ነገር ለአይሁዳውያን ጻፉላቸው፤ በእኔም ስም ከጻፋችሁ በኋላ የቤተ መንግሥቱን ማኅተም አትሙበት::"

(አስቴ 8÷8)

ስለዚህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የማኅተሙ ቀለበት ስላላት በሰዎች አእምሮ ውስጥ ያለውን እንደ እግዚአብሔር ቃል ያልሆነውን ሃማን ሊያውጀው የከረመውን ከአእምሮአቸው ማስወገድ የሚቻለው እውነተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል መገለጥ በትክክል በንጉሡ ስም በቀለበቱ ማኅተም በማስተማር ብቻ ነው:: ደግሞ ለዚህ ዕቅድ ግሩምና ድንቅ የማስተማር ቅባት ያላቸው ዐዋጅን በዐዋጅ የሚሽሩ በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ይነሳሉ:: ነገር ግን አሁን ባለንበት ዘመን የተሐድሶውን አገልግሎት እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን መጀመር አለባት:: ያወቀችውን እውነት ማንንም ሳትፈራ ሁሉን ነገር እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲሆን ማስተማር አለባት:: ሰዎችን በመፍራት ብቻ የተረዱትን እውነት ለሌሎች የማያስተላልፉ አገልጋዮች ወይንም ቤተ ክርስቲያናት ትልቅ ተጠያቂነት እንዳለባቸው መዘንጋት የለባቸውም:: የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የኮሚቴ ስብሰባና ድርድር ወይም የቁልምጫ ንግግር ሳይሆን የሚያስፈልገው ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ ሰማያዊ ትምህርት ብቻ ነው:: ለውጥን ለማምጣት ዐዋጅን በዐዋጅ የሚሽሩ ሰዎች አቋም ያላቸው መሆን ያስፈልጋቸዋል:: ገና ለገና ተቃውሞን በመፍራት ያወቅነውን እውነት ከማስተማር ወደ ኋላ ማለት የለብንም:: አለበለዚያ ግን የእስራኤል ሕዝብ በቃዴስ በእግዚአብሔር ላይ ባጉረመረሙ ጊዜ ሙሴና አሮን ስለ እግዚአብሔር ያወቁትን እውነት በሕዝቡ ፊት ገልጠው ባልተናገሩ ጊዜ የእግዚአብሔር ተግሣፅ ወደ እነርሱ እንዲህ ሲል መጣ :-

"ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ ሲል ገሠጻቸው፤ የተቀደሰው ኃይሌን በእስራኤል ሕዝብ ፊት ለማሳየት የሚያበቃ እምነት ስለሌላችሁ÷ ልሰጣቸው ቃል ወደ ገባሁላቸው ምድር የዚህ ሕዝብ መሪዎች ሆናችሁ አትገቡም::"(ዘኁ 20÷12)

ዛሬም ቢሆን ስለ እግዚአብሔር ያወቅነውን እውነት ሕዝቡን ነፃ የሚያወጣውን የእግዚአብሔር ኃይል የሆነውን ቃሉን በሕዝቡ ፊት ማንንም ሳንፈራ መግለጥ ካልቻልን በጣም ትሑት የሆነውን ሙሴን ያላሰፈ እግዚአብሔር እኛንም እንደማያልፈን መረዳት ይኖርብናል::

ነገር ግን የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን አመለካከትዋን በማደስ ሌሎችም እንዳይጠፉ አመለካከታቸው እንዲታደስ፣ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች በማስተማር ዐዋጅን በዐዋጅ በመሻር ብዙ ስዎችን ወደ ንጉሡ የበረከት ሙላት የሚያስገቡ የማኅተሙን ቀለበት በእጃቸው ባደረጉ በእግዚአብሔር ባሪያዎች ትሞላለች::

ስለዚህ :-

— ሰይጣን የፈረስውን ቅጥር አንዳያገኝ !

— ለቅሶና ዋይታ እንዳይበዛብን !

— የእግዚአብሔርን ክብር እንድናይ !

"... ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን ኑና
የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንሥራ..."
(ነህ2÷17)(በቀ.ት)

ምዕራፍ አሥር

የቤተ ክርስቲያን

በትንሳኤው ኃይል

በታላቅ ክብርና

ቅባት መመላለስ

የበቀል ቅባት በቤተ ክርስቲያን መፍሰስ

"... በዚህ ዓይነት አይሁዳውያን ያ ዕለት በሚደርስበት ጊዜ በጠላቶቻቸው ላይ <u>የበቀል እርምጃ</u> መውሰድ ይችሉ ዘንድ ሁኔታው ተመቻቸላቸው" (አስቴ 8÷13)

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ዐዋጅን በዐዋጅ የምትሽር ስለሆነ ከምታውጀው እውነተኛ የአግዚአብሔር የቃሉ ብርሃን የተነሣ ከምትቀበለው ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ጠላትዋን የምትበቀልበት የበቀል ቅባት ማግኘት ነው:: እስከ ዛሬ ድረስ የኤልያስ አምላክ ወዴት ነው ያለህ የሚያሰብል ከጠላት የሚደርስብንና የምናያቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም አግዚአብሔር ግን በየዘመናቱ የሚፈፅመው የራሱ የሆነ የበቀል ጊዜ አለው፤ ይህንንም በኢሳያስ 63÷4 ሲነግረን "የምበቀልበት ቀን በልቤ ነው " ይላል:: በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ከተቀመጡ የበቀል ቀናቶች ውስጥ አንዱና ትልቁ ጠላትን ለመጨረሻ ጊዜ የሚበቀልበት በመጨረሻው ዘመን ለወንጌል አገልግሎት በሕዝቡ ላይ በሚያፈሰው ቅባት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከሚጠብቃት ታላቅ ነገር አንዱ በልዩ ልዩ የአገልግሎትና በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታ በኩል ከአሁን በፊት ተለማምዳ በማታውቀው ሁኔታ ጠላቶችዋን ለመበቀል በልዩ የበቀል ቅባት ማገልገል ነው:: ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን ወደፊት ከቀስበቱ ማኅተም የተነሣ የአመለካከት ለውጥ ስለምታገኝ አግዚአብሔር ቀንድዋን ብረት ጥፍርዋን ናስ አድርጎ እንደ ኃያልና እንደ ጨካኝ ጠላትዋን ለመቀጥቀጥ በበቀል ከእርስዋጋር ስለሚወጣ በፊት ለፊትዋ የሚቆም ምንም ኃይል አይኖርም:: ስለዚህም በመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚፈሰው የበቀል ቅባት ምሳሌ የሆኑትን ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን::

ሀ) የሳምሶን ምሳሌነት

ሳምሶን አግዚአብሔር በታላቅ ኃይል የሚጠቀምበት እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው ለማዳን ብዙ ዘመን ያስጨነቃቸውንና በዙሪያቸው ያሉትን ጠላቶች አንዲበቀል የተቀባ ነበር:: ነገር ግን ሳምሶን በደሊላ ከተታለለ በኋላ

ጠላቶቹን የሚበቀልበትን ኃይሉን አስላጨ፤ በአስር ቤትም ገባ :: ልክ እንደዚሁ ቤተ ክርስቲያን ረቂቅ በሆነው የሰይጣን ሽንገላ ተታላ ጠላትዋን የምትበቀልበት ኃይል አጥታ ለብዙ ዘመን ለዓለም ብርሃን ሳትሆን በጠላት ምርኮ በአስር ውስጥ ነበረች:: ሳምሶን እንደገና ለመታደስና ጠላቶቹን ለመበቀል ፀጉሩ እስኪበቅል ድረስ ጊዜ እንደፈጀበት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን የደህንነትን ተሐድሶ ካገኘችበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን ሙሉ በሙሉ ጠላትዋን የምትበቀልበት ፀጉርዋ በማደግ ላይ ነው:: ሳምሶን ፀጉሩ ባደገ ጊዜ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከዚህ ምድር ከመሔዱ በፊት በበቀል ጠላቶቹን እንደፈጀ፤ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ፀጉርዋ አንዲበቅል ለመታደስ ራስዋን ያዘጋጀች ስለሆነች ሙሉ በሙሉ ፀጉርዋ ስለሚበቅል ከዚህ ምድር ከመወሰድዋ በፊት በበቀል ቅባት የጠላቶችዋን ምስሶ በመያዝ እስከ አሁን ተለማምዳ በማታውቀው በአግዚአብሔር የበቀል ኃይል ጠላቶችዋን በመበቀል የአግርዋ መረገጫ ታደርጋለች::

ሳምሶን የበቀል ኃይል ያለበትን ፀጉሩን በፍልስጤማውያን ከማስላጨቱ በፊት ከአንበሳ ጋር ታግሎ አሸንፎአል፤ በቀበሮችም በመጠቀም ጠላቶቹን ተበቅሎአል፤ በተጨማሪም በአህያ መንጋጋም ብዙ ሰዎች ገድሎአል:: አንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ያላትን ኃይል በጠላት ከማስበዝበዝዋና ከወንጌል አውነት ከመውጣትዋ በፊት ጠላቶችዋን የተበቀለችበት ብዙ መንገድ ነበር:: ነገር ግን ሳምሶን ለሁለተኛ ጊዜ መታደስ አግኝቶ ፀጉሩ ባደገ ጊዜ ጠላቶቹን ለመበቀል የአህያ መንጋጋ አላስፈለገውም፤ ነገር ግን ጠላቶቹ ተሰብስበው የተቀመጡበትን ዋናውን ምስሶ በማፈራረስ ነበር የተበቀላቸው:: ቤተ ክርስቲያንም ለሁለተኛ ጊዜ መታደስን ስታገኝ የበቀል ቅባትዋ ከፊተኛው ዘመን እጅግ የተሻለና ልዩ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን ለመበቀል የአህያ መንጋጋና ቀበሮዎች የምትፈልግበት ዘመን አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ቀበሮችን ለማግኘት ጫካ የምትወርድበት የአህያ መንጋጋ ለማግኘት ጋጣ (ግርግም) የምትወርድበት ዘመን አይደለም:: አሁን ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን ለመበቀል መሮጥ ያለባት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጠላቶችዋን በሙሉ የምታገኝበት ምስሶውን ለመያዝ መሆን አለበት::

ሳምሶን ምስሶውን ለመያዝ ጠላቶቹን ለመበቀል ዐይን የሚሆነውና አጁን ይዞ የሚመራው ሌላ ሰው አስፈልጎት ነበር:: ምክንያቱም የአርሱ ዐይኖች ታውረው ነበርና ሳምሶን ጠላቶቹን ለመበቀል ዐይኖቹ መታወራቸው በጣም አስፈላጊ ነበር:: ምክንያቱም የአርሱ ዐይኖች

ባይታወሩ ኖሮ የጠላትን ምሰሶ ሳይሆን የሚመለከተው የደሊላን ውበት ነበር:: ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን እንዳታይና ምሰሶውን እንዳትጨብጥ ትልቅ እንቅፋት የሆነባት በራስዋ ዐይን ስለምትመላለስና የምታየው÷ የምትነካው÷ የምትሠራው ነገር ሁሉ ከራስዋ የዐይን አመለካከት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን ዐይን መጠቀም እስካላቆመች ድረስ ምሰሶውን በፍፁም ልትይዝ አትችልም:: ሳምሶን ምሰሶውን ለመያዝ ዐይን የሚሆነውን ሌላ ረዳት እንዳስፈለገው ሁሉ እንዲሁም አስቴር ጠላቶችዋን ለመርገጥ መርዶክዮስ እንዳስፈለጋት ሁሉ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያንም በራስዋ ዐይን ሳይሆን ሁሉን ነገር የምትመለከተው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ስለሆነ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጠላትዋን የምትበቀልበትን ምሰሶውን የምትጨብጥ ናት::

ለ) የሙሴ ምሳሌነት

ሙሴ ከዚህ ምድር ከመወሰዱ በፊት እግዚአብሔር በእርሱ ላይ የበቀል ቅባት አፍስሶ ምድያምን መበቀል እንዳለበት እንዲህ ሲል ነገረው:-

> "እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው÷ ስለ እስራኤል ልጆች <u>በቀል</u> ምድያማውያንን <u>ተበቀል</u> ከዚያም በኋላ ወደ ወገኖችህ ትከማቻለህ::"
>
> (ዘኁ 31÷1)(የቀ.ት)

ሙሴ በበቀል ቅባት ምድያማውያንን ለመጨረሻ ጊዜ ተዋጋቸው፤ ብዙ ምርኮንም በዘበዙ፤ የሰይጣን ምላሌ የሆኑትን አምስቱን ነገሥታትን ገደሉ፤ የስሕተት አሠራር ምላሌ የሆነውንም በለዓምን ገደሉት:: እንዲሁም የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደ ሙሴ ከመወሰድዋ በፊት በእግዚአብሔር የበቀል ቅባት ጠላቶችዋን ለመጨረሻ ጊዜ የምትበቀልበት የበለዓምን የስሕተት አሠራር ፤ የማስመሰል አሠራር፤ የብርሃንን መልክ ይዞ በንጉሡ ስም የሚወጣውን የሰይጣንን አሠራር ሰይፍ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል የምትበቀል ናት::

ሐ) የበቀል ቅባት የሚፈሰባቸው ሰዎች

የእግዚአብሔር ቃል በትንቢተ ኤርምያስ የበቀልን ቅባት ስለሚቀበሉ ሰዎች ሲናገር :-

> " የአምላካችንን የእግዚአብሔርን በቀል የመቅደሱንም በቀል በጽዮን ይነግሩ ዘንድ ሸሽተው <u>ከባቢሎን አገር ያመለጡ</u> ሰዎች ድምጽ ተሰምቶአል" ይለናል:: (ኤር 50÷28)

በጥቅሱ መሠረት የአምላካቸውንና የመቅደሱን በቀል የሚያውጁ ከባቢሎን ያመለጡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ናቸው:: ባቢሎን የእግዚአብሔር ሕዝብ እውነተኛ አምልኮና አገልግሎት እንዳያገለግሉ በአምላካቸውና በሕዝቡ መካከል የገባች ናት:: ባቢሎን የእግዚአብሔር አሳብ መገኘትና ክብሩ የሌለባት የጣዖት አገር ነች:: ጽዮን ደግሞ የእግዚአብሔር እውነተኛ መገኘት÷ ክብሩና አሳቡ ያለባት የተቀደሰች አገር ናት:: በባቢሎን ቁጭ ብለን የአምላካችንን የበቀል ጦርነት መዋጋት አንችልም:: የበቀል ቅባት የሚወርድባቸው ሰዎች በባቢሎን ነገር ሕይወታቸውን ለምርኮ ያልሰጡ ናቸው:: ሳአል ሙሉ የጦር ልብስ ለብሶ ሳልያድን ድል ያላደረገበት ምክንያት እግዚአብሔርን በማያስከብር እንደ ባቢሎን በሆነ የዐማሌቅ ሠንጋ ተማርኮ ስለነበር ነው:: በዐማሌቅ ሠንጋ የተማረኩ ሰዎች በሚገዳደራቸው በሳልያድ ፊት ዘመናቸውን በፍርሃት ያሳልፋሉ እንጂ እንደ ዳዊት በሳልያድ አንገት ላይ በበቀል አይወጡም::

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ወደ ዘላለማዊ ቤትዋ ከመወሰድዋ በፊት በታላቅ ቅባት የአምላካቸውንና የመቅደሱን በቀል የሚያውጁ ሰዎች ለባቢሎን ምርኮ እምቢ ያሉና የእግዚአብሔርን ክብር ፍለጋና እውነተኛውን አሳብ ለማገልገል ወደ ጽዮን የተጓዙ ከነኩትም ከወርቅ በትር የተነሣ ከእጆቻቸውና ከእግሮቻቸው ወርቃማውን ቅባት የሚያንጠባጥቡ የመቅደሱን በቀል ለመናገር ውስጣቸው እንደ እሳት የሚነድ በእግዚአብሔር የበቀል ቅባት የተቀቡ አገልጋዮች በመጨረሻው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ይነሣሉ::

የመንፈስ ቅዱስ እውነተኛ ቦታውን መያዝ

"መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ ልብስ መንግሥት ለብሶ፥ ሐምራዊ ካባ ደርቦና ውብ የሆነ የወርቅ አክሊል ደፍቶ ከቤተ መንግሥት ብቅ አለ፤ በሱሳም ከተማ የሆታና የእልልታ ድምፅ አስተጋባ::"

(አስቴ 8÷15)

መርዶክዮስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ እንደሆነና እስከ አሁንም ባየናቸው የመጽሐፉ ክፍሎች ቤተ ክርስቲያንን ወደ ተጠራችበት የክብር ስፍራ ይዞ በመሄድ ላይ እንዳለና እንዲሁም ዐማሌቁ ሃማን ባወጣው ረቂቅ ዐዋጅ የተነሣ አመለካከታቸው ባልታደሰ አማኞች እንደተገፋና በደጅ በመቆም የሐዘን ድምፁን በጩኸት በማሰማት ላይ እንደነበረ ተመልክተናል:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን የወርቁን በትር በመንካት የወርቁ ቀለበት ባለቤት ስትሆን ዐዋጅን በዐዋጅ በመሻር የሃማን ዕቅድ ካፈረሰች በኋላ የሰዎች አመለካከት በቃሉ ብርሃን ሲታደስ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ትከክለኛ ቦታና ክብር ያገኛል:: ስለዚህ ከዚህ በፊት እንደሆነው በመገፋት፥ በሐዘንና በጩኸት ላይሆን በታላቅ ክብር በቤተ መንግሥት ውስጥ ተገለጠ:: ከዚህም የተነሣ ሦስት ነገሮች እንደተከሰቱ ከዚህ በታች እንመለከታለን::

ሀ) የቤተ ክርስቲያን በትንሳኤው ኃይል መመላለስ

"መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ ልብስ መንግሥት ለብሶ፥ ሐምራዊ ካባ ደርቦና ውብ የሆነ የወርቅ አክሊል ደፍቶ ከቤተ መንግሥት ብቅ አለ፤" (አስቴ 8÷15)

መርዶክዮስ ቀደም ብለን እንዳየነው ንጉሥ አርጤክስስን ከሞት ባዳነበት <u>በትንሳኤው ኃይል</u> በቤተ ክርስቲያን መመላለስ አልቻለም ነበር:: ነገር ግን አስቴር መንፈስ ቅዱስ የሚገፋበትን በንጉሡ ስም የሚነገረውን የሃማን ዐዋጅ በመሻር ተሐድሶን ስላመጣች መንፈስ ቅዱስም እውነተኛ ቦታውን ሊይዝ በመቻሉ ንጉሡን ባዳነበት በትንሳኤው ኃይል በቤተ መንግሥት ውስጥ ራሱን በታላቅ ክብር በመግለጥ ብቅ አለ:: በዚህ ጊዜ ነው

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለን " ከፊተኛው ቤት ይልቅ የኋለኛው ቤት ክብር እጅግ ታላቅ የሚሆነው " (ሐጌ 2÷9) ምክንያቱም ይህ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን የምትኖረውና የምታገለግለው በትንሳኤው ኃይል በታላቅ በእግዚአብሔር ክብር ስለሆነ ሰምተናቸው የማናውቃቸው አስደናቂ ተአምራቶችና ድንቆች ይከተልዋታል:: እንዲሁም መንፈስ ቅዱስ በዚህ መልኩ ሲገለጥ ቤተ ክርስቲያን ነቀፋ፥ የፊት መጨማደድ፥ ነውር የሌለባት፥ ንፅህትና ድንግል ኃጢያትም የማይገዛት ሆና በትንሳኤው ኃይል ስለምትኖር ከአምላክዋ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀች ትሆናለች::

ለ) የመንፈስ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን መዘጋጀት

"መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ ልብስ መንግሥት ለብሶ፥ ሐምራዊ ካባ ደርቦና ውብ የሆነ የወርቅ አክሊል ደፍቶ ከቤተ መንግሥት ብቅ አለ፤" (አስቴ 8÷15)

በዚህ ሁኔታ የተገለጠበት :- ንግሥት አስቴር የንግሥናዋን ልብስ ለብሳ የወርቅ ዘውዷን በራስዋ ላይ እንደደፋች ልክ እንደ አስቴር መርዶክዮስም የመንግሥቱን ልብስ ለብሶ የወርቅ አክሊል ደፍቶ የወጣበት ትልቁ ምስጢር የቤተ ክርስቲያንን መዘጋጀት ሲያመለክት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ለመነጠቅ የተዘጋጀች ስትሆን ሙሽራይቱ ብቻ ሳትሆን ጌታ ኢየሱስን ተዘጋጅቻለሁ "ና" የምትለው መንፈስ ቅዱስም ጭምር ነው አብሮ "ና" የሚለው:: በዮሐንስ ራእይ 22÷17 ላይ <u>"መንፈስ ቅዱስና ሙሽራይቱ ና ይላሉ"</u> ስለዚህም የመንፈስ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን የወርቅ አክሊል መድፋት መንፈስ ቅዱስም ሙሽራይቱም መዘጋጀታቸውንና አንድ ዓይነት ድምፅ ማሰማታቸውን ያመለክታል:: ያም ድምፅ ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅታለች "ና..ና" የሚል ነው:: መንፈስ ቅዱስም ቤተ ክርስቲያንን ካዘጋጀ በኋላ እርሱ ራሱ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለመሄድ የተዘጋጀ ይሆናል :: ከዚህ በኋላ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መንፈስ ቅዱስ የሚጠብቁት በዐይን ቅፅበት ለመሄድ ድንገት የሚነፋውን የመለከት ድምፅ ብቻ ነው::

"መንፈስ ቅዱስና ሙሽራይቱ ና ይላሉ የሚሰማም ና ይበል"

(ራእ 22÷17-18)

ሐ) የአምልኮ መታደስ

" መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ ልብሰ መንግሥቱን ለብሶ÷ ሐምራዊ ካባ ደርቦና ውብ የሆነ የወርቅ አክሊል ደፍቶ ከቤተ መንግሥት ብቅ አለ፤ <u>በሱሳም ከተማ የሆታና የእልልታ ድምፅ አስተጋባ</u>"

(አስቴ 8፤15)

ይህ የሆታና የእልልታ ድምፅ የተሰማው መንፈስ ቅዱስ በአምላክነት ክብሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመገለጡ ነበር:: የአመለካከት ለውጥ ስለመጣና መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛ ስፍራውን በቤተ ክርስቲያን ስለያዘ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የተዘጋጀች መሆንዋንና መንፈስ ቅዱስም ራሱ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ለመሄድ የተዘጋጀ መሆኑን አማኞች ስለተረዱ ወደማይናወጥ መንግሥት ድንገት እንደሚነጠቁ ስለገባቸው በሕዝቡ ላይ ልዩ የሆነ የአምልኮ ፀጋ ፈሰሰ:: ምክንያቱም የማይናወጥን መንግሥት እንደምትወርስ በተረዳችና በተዘጋጀች ቤተ ክርስቲያን ላይ ቃሉ ሲገልፅልን "ስለዚህ <u>የማይናወጥን መንግሥት</u> ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን <u>የምናመልክበትን ፀጋ እንያዝ</u>"(ዕብ 12÷28)(የቀ.ት) እንግዲህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ክብር በታላቅ ኃይል ስለምታይ አምላክዋን በማወቅና በመረዳት የምታመልክበት ታላቅ የሆነ የአምልኮ መታደስ ታገኛለች::

የቤተ ክርስቲያን መፈራት

"...በዚሁ ሳቢያ አይሁዳውያንን ከመፍራት የተነሣ ከሌሎች አሕዛብ ወገን ብዙዎቹ አይሁዳውያን ለመሆን ወሰኑ::" (አስቴ 8÷17)

በተለይም ቤተ ክርስቲያን በትንሳኤው ኃይል መመላለስ ስትጀምር የመንፈስ ቅዱስ ታላቅ የተአምራት÷ የድንቅና የምልክቶች አሠራር ከፍተኛ በሆነ ሁኔታ ስለሚገለጥ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ቅድስና ስለምትመላለስ የአስፈሪነት ሞገስዋ ለሰዎች ሁሉ ይገለጣል:: በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ይፈጽማቸው

የነበረውን አስደናቂ ተአምራቶች በሰሙትና ባዩት ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ይሆን ነበር:: በኋለኛው ቤት ደግሞ የሚፈፀመው የመንፈስ ቅዱስ ተአምራት በክብርም በዓይነትም እጅግ ታላቅ ይሆናል:: ምክንያቱም የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ከሴቶች ሁሉ ይልቅ የተዋበች÷ እንደ ንጋት ብርሃን የምትፈነጥቅ÷ እንደ ጨረቃ የምትደምቅ÷ እንደ ፀሐይ የምታበራ÷ የጦር ዓርማ ይዞ እንደሚጓዝ ሠራዊት ሆና ስትመላለስ ባያት ሁሉ ፊት ግርማዋ እጅግ የሚያስፈራ ትሆናለች:: (መኃ.መኃ 6÷10) ቤተ ክርስቲያን በእሁኑ ዘመን አስፈሪ እንዳትሆን ካደረግዋት ከብዙ ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ:-

<u>የአገልጋዮችና የአማኞች በቅድስና አለመመላለስ</u> ብዙ ምእመናን የሚያገለግሉዋቸውን አገልጋዮች ቅድስና የሌለውን ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን በሚገባ ስለሚያውቁ፤ ያልኖሩበትንና ያልተለማመዱት ስለሆነ አድርጉ ብለው የሚያስተምሩዋቸው ከዚህ የተነሣ በምእመኑ ፊት የተናቁ ናቸው:: ምእመኑም የአገልጋዮችን ሕይወት በማየት በቅድስና ስለማይኖሩ በማያምኑ ሕዝብ ፊት የተናቁ ናቸው::

<u>የአሰመሳይ አገልጋዮች አገልግሎት</u> ይህ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን እንድትደፈር ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ነው:: አሰመሳይ አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ሳይቀበሉ ተቀበልን ስለሚሉ እግዚአብሔር ሳያደርገው እግዚአብሔር አደረገው የሚሉ ስለሆነ ብዙ የሐሰት ትንቢቶች ይናገራሉ ነገር ግን አይፈፀሙም፤ ብዙ የፈውስ መገለጦች ያመጣሉ ነገር ግን የሚፈወስ አይኖርም፤ አገልግሎታቸው ጩኸት ብቻ ነው:: ከዚህም አልፈው እንደ ንግሥት አስጢን ራሳቸውን በሴት ወይዛዝርት መካከል ማክበር ስለሚፈልጉ ስለ አገልግሎታቸው እጅግ በማጋነን ዐዋጅን ስለሚያውጁ አንድ ሰው ከዳነ አሥር ሰው ድነዋል ብለው ስለሚያስወሩ የኋላ ኋላ ነገሩ በአማኞችና በማያምኑ ጆሮ ስለሚደርስ ከእነዚህ አገልጋዮች የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ታፍራለች እንጂ አትፈራም:: ለእንደነዚህ ዓይነት አገልጋዮች ጳውሎስ ጥሩ ትምህርት ትቶልን አልፎአል ::

"አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ÷ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል÷ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል <u>በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር</u> ምንም ልናገር አልደፍርም ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ እስከ አልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ:: "

(ሮሜ 15÷ 18-19) (የቀ.ት)

እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን በመንፈስ አንድነት አለመራመድ፤ ቀደም ብለን እንዳየነው የቤተ ክርስቲያን ቅጥ ያጣ የአመራር ሁኔታና የመሳሰሉት ቤተ ክርስቲያን እንዳትፈራ ካደረጓት ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ግን ምንም ጥቅም ከሌለው ከተት ራስዋን ያነፃች ስለሆነች ውበትዋ አምላክዋን እንደማረከ ሁሉ ሰዎችን የሚማርክ፤ እውነተኛውን የክርስትና ኑሮን በመኖር አገልግሎትዋን የምታገለግል ስለሆነች ብዙ ሰዎችን ወደ ጌታ የምታመጣ የአስፈሪነት ሞገስ በግልፅ የሚታይባት ናት::

የብዙ ሰዎች መዳን

"በየትኛውም አገርና በማንኛይቱም ከተማ የንጉሡ ዐዋጅ በተነበበበት ስፍራ ሁሉ አይሁዳውያን ታላቅ የበዓል ቀን አድርገው በተድላና በደስታ ዋሉ፤ በዚህም ላቢያ <u>አይሁዳውያንን ከመፍራት የተነሣ ከሌሎች አሕዛብ ወገን ብዙዎቹ አይሁዳውያን ለመሆን ወሰኑ</u>::"

(አስቴ 8÷17)

ቤተ ክርስቲያን በትንሳኤው ኃይል ስትመላለስ መፈራትን ታገኛለች፤ ከመፈራትዋ የተነሣ ብዙ ሰዎች ክርስቲያን ለመሆን ይወስናሉ:: አስቴር ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ካደረገቻቸው ድርጊቶች የተነሣ በተለይ እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል በመግለጥና ዐዋጅን በዐዋጅ በመሻር አይሁዳውያን እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በጠላቶቻቸው ላይ በድል እድራጊነት መመላለስ ስለጀመሩ፤ ከማንኛውም ሕይወታቸውን ባሪያ አድርጎ ሊገዛው ከተነሣው ጠላትሁሉ ነፃ ስለወጡ÷ እስፈሪነታቸውን እሕዛብ ሁሉ ስላወቁ ብዙ አሕዛብ አይሁዳውያንን በመፍራት አይሁዳውያን ለመሆን ወሰኑ::(አስቴ8÷17) ይህ ማለት ቤተ ክርስቲያን በትንሳኤው ኃይል ስትኖርና ስትመላለስ በድል አድራጊነት ኃጢያትንና ሰይጣንን ስትቀጠቅጥ መፈራትን ታገኛለች ፤ ከመፈራትዋ የተነሣ ብዙ ሰዎች ክርስቲያን ለመሆን ይወስናሉ:: በትንቢተ ዘካርያስ ምዕራፍ አራት ላይ የፈረሰው ቤተ መቅደስ እንደገና በማደስ እንደሚሠራው በዘካርያስ በኩል ለዘሩባቤል እግዚአብሔር

ተስፋን ሲሰጠው እናያለን:: እንደገና በምዕራፍ ስምንት ደግሞ ከታደሰ በኋላ ኢየሩሳሌምን በመፍራት ስለሚሆን የብዙ ሰዎች መዳን ሲገልፅ :-

"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሌሎች ሕዝቦችና በብዙ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም የሚጎርፉበት ጊዜ ይመጣል:: ከአንዱ ከተማ የመጡት ከሌላው ከተማ የሚመጡትን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ልንሰግድና በረከትን ይሰጠን ዘንድ ወደ እርሱ ልንፀልይ መሄዳችን ነውና ኑ አብረን እንጓዝ ይሉዋቸዋል:: በዚህ ዓይነት ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ለመስገድና የእርሱንም በረከት ያገኙ ዘንድ ለመፀለይ ብዙ ሕዝቦች ይልቁንም ታላላቅ መንግሥታት ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣሉ:: በእነዚያን ቀናት አሥር የባዕድ አገር ሰዎች ወደ አንዱ አይሁዳዊ ቀርበው የልብሱን ዘርፍ በመያዝ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር መሆኑን ስለሰማን ከእናንተ ጋር ተባብረን ለመኖር እንፈልጋለን ይሉታል::" (ዘካ 8÷20-23)

ጌታ ኢየሱስ ስለ ዘመኑ ፍፃሜ ወይም የዓለም መጨረሻ ሲደርስ ብዙ ምልክቶች እንደሚሆኑና እንዲሁም ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወንጌል ለመላው ዓለም ይሰበካል አለ፤ በዚያም ጊዜ መጨረሻው ይመጣል:: (ማቴ 24÷14) ለፍጥረት ሁሉ ወንጌል ሳይሰበክ መጨረሻው አይመጣም ነገር ግን በጣም ልናስተውል የሚገባን በዘመኑ ፍፃሜ ለፍጥረት ሁሉ ወንጌል የምትሰብከው በጣም የምታስፈራና ግርማ ያላት በከፍታ ላይ የምትሄድ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች በትንቢተ ሚክያስ ላይ እንዲህ በማለት ይገልጸልናል :-

"የዘመኑ ፍፃሜ ሲደርስ÷ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የተሠራበት ተራራ ከሌሎች ተራሮች ሁሉ በልጦ ይታያል፤ ከኮረብቶችም ሁሉ እጅግ ከፍ ይላል፤ የብዙ መንግሥታት ሕዝቦች ወደ እርሱ ይጎርፋሉ፤ ስለዚህ ብዙ ሕዝቦች እንዲህ ይላሉ÷ ሕግ ከጽዮን÷ የእግዚአብሔርም ቃል ከኢየሩሳሌም ስለሚገኝ÷ ኑ ÷ወደ እግዚአብሔር ተራራ እንውጣ፤ ወደ ያዕቆብም አምላክ ቤተ መቅደስም

እንሂድ፤ እርሱ ፍቃዱን እንድናደርግ ያስተምረናል፤ እኛም በእርሱ መንገድ እንሄዳለን::" (ሚክ 4÷1-2) (ኢሳ 2÷1-4)

ስለዚህ የትንቢቱ ቃሎች እንደሚያረጋግጡልን የመከሩ ሠራተኞች የሚሆኑት እንደ ዘሩባቤል ቤተ መቅደሱን ያደሱና በአስፈሪነት ግርማ የሚመላለሱ ናቸው፤ እንዲሁም ነቢዩ ሚክያስ እንደሚነግረን ከተራሮች ሁሉ በላይ በተራሮች ከፍታ ላይ የምትራመደውን ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ መዘንጋት የለብንም:: ስለሆነም መከሩን ለመሰብሰብ በታላቅ የእግዚአብሔር ክብር ውስጥ መሆን ያስፈልገናል ለዚህም የሚያበቃንን የተሐድሶ ዘመን በቀላሉ ማለፍ አይኖርብንም::

በድል ላይ ድል መጨመር

" አስቴርም÷ የግርማዊነትህ መልካም ፈቃድህ ከሆነስ በሱሳ ከተማ የሚኖሩት አይሁዳውያን ዛሬ ያደረጉትን በነገውም ዕለት ደግመው እንዲያደርጉት ይፈቀድላቸው፤ የአሥሩም የሃማን ልጆች አስከሬን ተወስዶ በእንጨት ላይ እንዲሰቀል ዕዘዝ ስትል መለሰች::" (አስቴ 9÷13)

አስቴር ጠላቶችዋን የእግርዋ መረገጫ በማድረግ ሙሉ በሙሉ የዐማሌቅን አሠራር ከምድረ ገፅ የምታጠፋ ስለሆነች ጠላቶችዋን ድል ለማድረግ ወደ ኋላ የማትመለስ በአንድ ድል ብቻ ረክታ መቀመጥን ስለማትፈልግ በንጉሡ ፊት በመቅረብ ሌሎች ድሎችን እንዲሰጣት ጠየቀች:: ንጉሡም ፈቀደላት:: ስለዚህ አስቴር በድል ላይ ድልን እየተጎናፀፈች ጠላቶችዋን ረገጠች እነዚህም ድሎች :-

1. በግብግ ቦታ የሃማን ራስ መቀጥቀጥ (አስቴ 7÷6-10)
2. የብልፅግና ምርኮ ባለቤት መሆን (አስቴ 8÷1)
3. የቀለበቱ ማኅተም ባለቤት መሆን (አስቴ 8÷2)

4. ዐዋጅን በዐዋጅ በመሻር የሰዎችን አመለካከት መለወጥ (አስቴ8÷3-14)
5. ብዙ አሕዛብን ወደ ጌታ በማምጣት የመከሩ ሰብሳቢ መሆን (አስቴ 8÷17)
6. በብዙ አሕዛብ ፊት በመፈራት በሞገስ መመላለስ (አስቴ 8÷17)
7. የአይሁድ መናገሻ በሆነች በሱሳ ከተማ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ጠላት የሆነውን የሃማን ተባባሪ የሆኑትን አምስት መቶ ሰዎች መግደል (አስቴ 9÷6)
8. አሥሩን የሃማንን ልጆች በመግደል በሱሳ ከተማ በይፋ በእንጨት ላይ መስቀል (አስቴ 9÷14)
9. አይሁዳውያን አንድነታቸውን በማጠናከር የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የሆኑትን ሦስት መቶ ሰዎች መግደል (አስቴ 9÷15)
10. በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት በየአገሩ የሚገኙ አይሁዳውያን ሁሉ አንድነታቸውን በማጠናከር ተደራጅተው ራሳቸውን በመከላከል ይጠሉአቸው የነበሩትን ሰባ አምስት ሺህ ሕዝብ በመግደል ከጠላቶቻቸው እጅ ራሳቸውን ማዳን (አስቴ 9÷16)

እንግዲህ ከእግዚአብሔር ቃል እንዳየነው የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን በተጎናፀፈችው መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች በእግዚአብሔር ክብር ተሞልታ ከዚህ ምድር እስከምትሄድበት ድረስ በድል ላይ ድልን እየጨመረች ሁሉን በሥልጣንዋ ሥር ትረግጣለች::

የቤተ ክርስቲያን ወደ እምነት አንድነት መምጣት

"... አይሁዳውያን እንደገና <u>በአንድነት ተደራጅተው</u> በተጨማሪ ሦስት መቶ ሰዎችን ገደሉ..."(አስቴ 9÷15)

"እንዲሁም በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት በየአገሩ የሚኖሩ አይሁዳውያን ሁሉ <u>አንድነታቸውን በማጠናከር ተደራጅተው</u> ራሳቸውን ተከላከሉ፥..." (አስቴ 9÷16)

በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ አይሁዳውያን ጠላቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ለመርገጥ የግድ አንድነታቸውን ማጠናከር ነበረባቸው:: ቃሉ እንደሚለን "<u>በንጉሡ ነገሥቱ ግዛት በየአገሩ የሚኖሩ...</u>" ይህ ማለት ወደ አንድነት የመጡ የማይተዋወቁ በየአገሩ የሚኖሩ፤ እንደየአገሩ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ነገር ግን ሁሉም አይሁዳውያን ነበሩ:: ምንም አይሁዳዊ ቢሆኑ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ጠላቶቻቸውን ድል ለማድረግ ከየአሉበት ቦታ በአንድነት መደራጀት ነበረባቸው:: ክርስቶስ ፍፁምና ሙሉ እንደሆነ እኛም ሙሉ እንድንሆንና ጌታ እንዲመጣ የግድ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ልጅ በማወቅና በማመን ወደሚገኘው አንድነት መድረስ እንዳለባት በኤፌሶን 4÷13 ላይ ይነግረናል:: በእምነት ወደሚገኝ አንድነት ደርሳ ሙሉ ሰው እንድትሆን ሊያደርጋት የሚችለው ደግሞ የእግዚአብሔርን ልጅ ክርስቶስን ማወቅ ነው:: ክርስቶስ ደግሞ ቃሉ እንደሆነ በዮሐንስ ወንጌል 1÷1 ላይ ይነግረናል የእግዚአብሔርን ቃል ወይም የእግዚአብሔርን ልጅ በደንብ እንድናውቅ የሚያደርጉን ከፍ ብሎ በኤፌሶን 4÷11 ላይ የተጠቀሱት የአምስቱ የአገልግሎት ሥጦታዎች ናቸው:: ካለነዚህ የአገልግሎት ሥጦታዎች ቤተ ክርስቲያን ወደ እምነት አንድነት ከዚያም ሙሉ ሰው ወደ መሆን ደርሳ ሞትና መውጊያውን ድል መንሣት አትችልም::

እግዚአብሔር የተለያዩ አገልግሎቶችን እያደለ አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: በተለይም በቤተ ክርስቲያን በአምስቱ የአገልግሎት ሰጦታዎች በመጠቀም ከአሁን በኋላ በሚመጡት ዘመናት ግን እግዚአብሔር

የሚያድሰው የቃሉን እውነት ነው:: ቤተ ክርስቲያን በቃሉ እውነት እንጂ በሌላ በምንም ነገር ወደ እምነት አንድነት አትደርስም ::

የቤተ ክርስቲያን የእምነት እንድነት ሊበላሽ የቻለበት ምክንያት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳቸው አእምሮ እንደሚስማማ ትርጉም ስለሚሰጡት ከቃሉ አመለካከት የተነሣ ብዙ ልዩነቶች ተፈጥሮአል:: ስለዚህ የእምነት አንድነት ለማግኘት የግድ በእግዚአብሔር የቃሉ እውነተኛ ፍቺ መሠረት የአመለካከት ለውጥን ማግኘት አለብን:: እውነተኛ አንድነት የሌለበት ማንኛውም ህብረት ክቃሉ ውጭ ስለሆነ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምንም ዓይነት መታሰቢያ አይኖረውም:: የራሳችንን አመለካከት ጥለን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ክርስቶስን መምሰል እንድንችል የእግዚአብሔር ቃል በኤፌሶን 4÷15 ላይ ቁልፍ የሆነውን እውነት ሲገልጽልን እንዲህ ይለናል "<u>ይልቁንም እውነትን በፍቅር እየተናገርን ራስ የሆነውን ክርስቶስን ለመምሰል በሁሉ ነገር እናድጋለን::</u>" እዚህ ላይ እውነት የሚለን <u>የእግዚአብሔርን ቃል</u> ነው:: (ዮሐ 17÷17) ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን በመምሰል ሙሉ ሰው እንድትሆን ተአምራትና ድንቆች ሳይሆኑ የሚያስፈልጉን የቃሉን እውነት በፍቅር መናገር ነው::

ፍቅር የሚለው ቃል ለእንዳንዶቹ <u>"ሁሉን ነገር በፍቅር እንለፈው"</u> በሚል በተጋረደ አስተሳሰብ የበደል መሸፈኛ ሆኗል:: ጌታ ኢየሱስ ለሰው ልጆች በትክክል ያሉበትን እውነት በግልፅ ይነግራቸው የነበረው ስለማይወዳቸው ሳይሆን የእግዚአብሔር ፍቅር ከእውነት ጋር ደስ ስለሚለው ነው:: (1ቆሮ 13÷6) ፍቅር የኃጢያትን ብዛት ይሸፍናል ማለት ኃጢያትን ዝም ብሎ ያልፋል ማለት አይደለም:: ሐዋርያው ዮሐንስ ሲፅፍ <u>ፍፁም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል</u> ይለናል:: ይህ ማለት በፍቅር ውስጥ ፍርሃት ስለሌለ የሰዎችን ኃጢያት በመግለጥ በድፍረት እንዲያስተካክሉ እንናገራለን ክዚያም "እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል" ተብሎ እንደተጻፈ ከተናገርነው እውነት የተነሣ ሰዎች ከታሠሩበት ነገር ነፃ ይወጣሉ የዛን ጊዜ እንተ በፍቅር እውነትን ከመናገርህ የተነሣ ሰዎች በንስሃ በክርስቶስ ደም ኃጢያታቸውን ይሸፍናሉ ወይም ያስወግዳሉ ማለት ነው:: ያለበለዚያ ግን እውነትን በፍቅር መናገር ካልቻልን በፍርሃት ውስጥ ነን ፍርሃት ደግሞ ቅጣት አለው:: (1 ዮሐ 4÷18) ስለዚህ እግዚአብሔር ከአሁን በኋላ በቤቱ የሚያድሰው ታላቅ ነገር ቤተ ክርስቲያንን ወደ ፍፁም አንድነትና ሙሉ ሰው ወደ መሆን የሚያደርሳትን

ሽንገላ የሌለበትን በፍፁም ፍቅር የሚነገረውን "የቃሉን እውነት" ነው:: ከዚህም የተነሣ ነው የእምነት አንድነት የሚመጣው::

እንግዲህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክለኛው ፍቺ እንደ ጌታ ኢየሱስ ማንንም ሳይፈሩ በፍቅር እውነትን የሚያስተምሩ ናቸው:: ካስተማሩትም እውነት የተነሣ ለዎችን ከብዙ ነገር አርነት በማውጣት ወደ እምነት አንድነትና ክርስቶስም ሙሉ እንደሆነ ሙሉ ሰው ወደ መሆን ወደ ሙላቱ የሚያደርሱ ናቸው:: ስለዚህ ታላቅና አስደናቂ የሆኑ እውነቶች ገና በቤተ ክርስቲያን ይፈላሉ:: ከዚህም የእግዚአብሔር ቃል እውነታ የተነሣ በኤፌሶን 5÷25 እንዳለው የቃሉ ውኃ በተቀቡ አገልጋዮች እየተነገረ ቤተ ክርስቲያን ዕድፈት÷ የፊት መጨማደድና ነውር የሌለባት ንፅህት ሆና ለባልዋ እንደተዘጋጀች ሙሽራ ስለምትሆን የቤተ ክርስቲያን መወሰድ (ንጥቀት) ይሆናል::

የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ

"እነዚህ ዕለታት አይሁዳውያን ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው እጅ በማዳን ዕረፍት ያገኙባቸው ቀኖች ናቸው፤ ከሐዘንና ከተስፋ መቁረጥ ወደ ደስታና ወደ ሐሴት የተላለፉበት በዚህ ወር ነበር፤..."(አስቴ 9÷22)

እስከ አሁን በመጽሐፈ አስቴር እውነተኛ የእዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ምን መሆን እንዳለባት ተመልክተን ነበር:: በዚህ ክፍል ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ፍፃሜ ከመመልከታችን በፊት የፑሪም በዓል ምሳሌነቱን አስቀድመን እንመለከታለን::

ሀ) የፑሪም በዓል (መነጠቅ)

የፑሪም በዓል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጽሐፈ አስቴር ብቻ የሚገኝ ነው:: ይህ በዓል የአይሁድ ሕዝብ ጠላቱን ሃማን ድል በመንሣት ነፃ የወጣበት ቀን ነው፤ የነፃነት የድልና የግብጥ በዓል ነው:: ሃማን በመጀመሪያ

ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ሲነሳ ፑሪም ተብሎ የተሰየመውን ዕጣ በመጣል አይሁዳውያን ለማጥፋት ወሰነ::

"የአይሁዳውያን ጠላት የነበረው የአጋግ ዝርያ የሆነው የሃመዳታ ልጅ ሃማን÷ ፑሪም ተብለው የሚጠሩትን ዕጣዎች በመጣል አይሁዳውያንን በሙሉ ከምድረ ገፅ ጠራርጎ ለማጥፋት የሚችልበትን ዕለት ለማወቅ ዐቅዶ ነበር" (አስቴ 9÷24)

ዐማሌቁ ሃማን ፑሪም የሚባሉትን ዕጣዎች በመጣል የፑሪም በዓል መቼ እንደሚሆን ለማወቅና ያ ቀን ከመድረሱ በፊት አይሁዳውያንን በሙሉ ከምድረ ገፅ ጠራርጎ ለማጥፋት ዕቅድ ነበረው:: ይህ ማለት ታላቁን የቤተ ክርስቲያን የግብጥ ቀን ለማወቅ ዕቅድ ነበረው እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ወደ ክብር እንዳትገባ ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ዕቅድ ነበረው:: ነገር ግን አስቴር ወደ ንጉሡ ገብታ የወርቁን በትር ከነካች በኋላ የእርሱ ዕቅድ ሁሉ ጠፋ:: ስለዚህ ፑሪም ማለት ጠላታችን ሃማን ቤተ ክርስቲያን ተዘጋጅታ እንዳታየው የሚፈልገው የግብጥ በዓል ሲሆን የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ልታየው የምትናፍቀው የበጉ ሠርግ ግብጥ ምሳሌ ነው:: የአይሁድ ሕዝብ ይህንን የፑሪም በዓል ለማክበር የበቁት ጠላቶቻቸውን የእግራቸው መረገጫ ካደረጉ በኋላ ነበር:: እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን የእግርዋ መረገጫ እስካላደረገች ድረስ ፑሪም ተብሎ የተሰየመውን የበጉን የሠርግ ግብጥ አታይም::

የአይሁድ ሕዝብ በዚህ ፑሪም ተብሎ በሚጠራው የግብጥ ዕለት ወደ አንድ አዲስ ነገር የተላለፉበት ጊዜ ነበር ይህንንም የእግዚአብሔር ቃል ሲነግረን :-

"እነዚህ ዕለታት አይሁዳውያን ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው እጅ በማዳን ዕረፍት ያገኙባቸው ቀኖች ናቸው፤ ከሐዘንና ከተስፋ መቁረጥ ወደ ደስታና ወደ ሐሴት የተላለፉት በዚህ ወር ነበር:: " (አስቴ 9÷22)

ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት ወደ አዲስ ነገር የተላለፉት :-

1ኛ. ከጠላቶቻቸው እጅ በመዳን ወደ ዕረፍት ተላለፉ የዕብራውያን ጸሐፊ የእግዚአብሔር ሰዎች ገና ስለሚጠብቃቸው ዕረፍት ሲነግረን

"እንግዲህ የእግዚአብሔር ሕዝብ <u>የሰንበት ዕረፍትን የመሰለ</u> ዕረፍት ገና ይቀረዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ÷ እንዲሁም እግዚአብሔር ወደሚሰጠው <u>የዕረፍት</u> ቦታ የሚገባ ከሥራው ያርፋል:: ስለዚህ ማንም የእነዚያን ሰዎች አለመታዘዝ ተከትሎ እንዳይወድቅ÷ወደ እግዚአብሔር <u>የዕረፍት</u> ቦታ ለመግባት እንትጋ::"

(ዕብ 4÷9-11)

2ኛ.<u>ከሐዘንና ከተስፋ መቁረጥ ወደ ደስታና ሐሴት ተሳለቆ</u> ይህንንም በራእይ መጽሐፍ ላይ ሲገልፅልን

"እንባን ሁሉ ከዐይናቸው ላይ ይጠርጋል፤ <u>ሞት</u> ወይም <u>ሐዘን</u> ወይንም <u>ልቅሶ</u> ወይም <u>ስቃይ</u> ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም፤ ምክንያቱም የቀድሞዎቹ ነገሮች ሥርዓት አልፈዋል::" (ራእይ 21÷4)

አይሁዳውያን ከሐዘንና ከተስፋ መቁረጥ ፍፁም ደስታና ሐሴት እንዲሁም ፍፁም ዕረፍት ወዳለበት ክብር እንደተሳለቆ ሁሉ ባለንበት ዘመን ቤተ ክርስቲያን የምትጠብቀው ትልቅ ነገር ቢኖር ፍፁም ወደ ሆነው የሰንበት ዕረፍት ለመግባት የምትተላለፍበትን(የምትነጠቅበትን) ጊዜ ነው:: ነገር ግን ለሁላችን ግልፅ ሊሆን የሚገባው ቤተ ክርስቲያን እንደምትነጠቅ ሳይሆን፤ ምን ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ናት የምትነጠቀው ? የሚለውን ነው:: ለዚህም አጭር መልስ ጠላቶችዋን የእግርዋ መረገጫ ያደረገች እንደ አስቴር ያለች ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት የምትነጠቀው:: ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣው ሁለት ነገሮች ከተፈፀሙ በኋላ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል::

አንደኛው "እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነቢያቱ አፍ የተናገረው ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማያት ሊቀበሉት ይገባል" (ሐ.ሥ 3÷21) (የቀ.ት) ስለዚህ ጌታ ከመምጣቱ በፊት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሰፈረው የአገልግሎት ስጦታዎች ሙሉ በሙሉ ይታደሳሉ ተአምራቶችና ድንቆች እንዲሁም የእግዚአብሔር የቃሉ እውነቶች መታደስን ያገኛሉ:: በአጠቃላይ መታደስ ያለበት ሁሉ ነገር ይታደሳል::

ሁለተኛ "እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀመጠ÷ <u>ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ</u> እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል::" (ዕብ10÷12-13) (መዝ110÷1) (1ቆሮ15÷25) በእነኝህ ጥቅሶች መሠረት ክርስቶስ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ እስኪሆኑ ድረስ በሰማይ ይቆይ ዘንድ ይገባዋል:: እግዚአብሔር ለክርስቶስ ያላስገዛለት ነገር የለም "ሁሉ ነገር በሥልጣኑ ሥር ሲያደርግ፤ በሥልጣኑ ሥር ሳያደርግለት ያስቀረው ምንም ነገር የለም:: ነገር ግን አሁን ሁሉ ነገር በእርሱ ሥልጣን ሥር እንደሆነ ገና አላየንም::" (ዕብ 2÷8) በዚህ ጥቅስ ለክርስቶስ ያልተገዛ እንደሌለ ነገር ግን ሁሉ ነገር አሁን እንዳልተገዛለት ይነግረናል:: ስለሆነም ሁሉ እስኪገዛለት ድረስ በአብ ቀኝ ይቀመጥ ዘንድ ይገባዋል ይለናል::

አሁን ሁሉ ነገር እንዳልተገዛለት እናያለን ሲል ምን ማለቱ ነው ? ያልተገዛለት ወደ ፊት ግን የሚገዛለት ነገር እንዳለ ያመለክተናል:: ያም ወደፊት ድል በመነሣት የእግሩ መረገጫ የሚሆነው ጠላት ሞት ነው:: "ተሸንፎ በመጨረሻ የሚደመሰሰው ጠላት ሞት ነው" (1ቆሮ 15÷26) ሞት ድል በመነሣት የሚሸነፈው መቼ ነው ? መልሱ ጠላቶቹ የእግሩ መረገጫ ሲሆኑ:: የክርስቶስ የእግሩ መረገጫ ደግሞ የሚያመለክተው በመጨረሻው ዘመን ያለችውን ጠላቶችዋን የምትረግጠውን አካሉ የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ነው::

የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን በመርገጥ ሞትን ድል የምትነሣ ናት:: ጠላቶችዋን ድል የምትነሳ ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት እንደሆነች ለማወቅ ከፊለግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረውንና ከዚህ በላይ በሆነ አገላለፅ ልትገለጽ የምትችለውን የአስቴርን ቤተ ክርስቲያን መመልከት በቂ ነው:: አስቴር ጠላቶችዋን ረገጠች ማለት ሰይጣንንና የኃጢያት አሠራሩን ሁሉ ረገጠች ማለት ነው:: ስለዚህ እርስዋ ኃጢያትን ድል በመንሣት ተመላልሳ ኃጢያትን ድል ከነሣች በኋላ ሞት ደግሞ ድል እንደሚነሣ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል::

"እነሆ አንድ ምስጢር እነግራችኋለሁ:: ሁላችንም <u>አንሞትም</u>፤ ነገር ግን ሁላችንም እንለወጣለን:: የምንለወጠውም የመጨረሻው መለከት በሚነፋበት ጊዜ እንደ ዐይን ቅፅበት በአንድ ጊዜ ነው:: መለከቱ ይነፋል፤ የሞቱትም

ሰዎች የማይጠፉ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን ምክንያቱም ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን÷ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን መልበስ አለበት:: ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን÷ይህም የሚሞተው የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ÷ "ሞት በድል ተዋጠ" ተብሎ የተፃፈው ይፈፀማል:: እንዲሁም÷ "ሞት ሆይ ! ድል መንሳትህ የት ነው ? ሞት ሆይ ! ሰውን የምትጎዳበት ኃይል የት ነው ?" ተብሎአል:: የሞት መንደፍያ ኃይል ኃጢያት ነው ፤ የኃጢያትም ኃይል ሕግ ነው::" (1ቆሮ 15÷51-56)

ጠላቶችዋን የእግርዋ መረገጫ የምታደርግ ቤተ ክርስቲያን ሞትን ድል በመንሳት ሞት እንዲዋጥ የምታደርግ ናት:: "ሞት በድል ተዋጠ" የሚለው ቃል በደንብ እንድንረዳው ያስፈልጋል እስከ ዛሬ ድረስ ሞትን ማንም ድል በመንሣት እንዲዋጥ ያደረገ የለም:: ሄኖክ እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘ እግዚአብሔር ወሰደው አልተገኘም:: (ዘፍ5÷24) ኤልያስም በእሳት ሰረገላ በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ተወሰደ:: (2ነገ 2÷11) ሄኖክም ሆነ ኤልያስ ለአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን የመነጠቅ ምሳሌ አድርገን ብንጠቀምባቸውም እነርሱ ግን ሞትን ድል በመንሣት ወደ ሰማይ እንደሄዱ መጽሐፍ ቅዱስ አይነግረንም:: የቤተ ክርስቲያን መነጠቅ ግን በጣም ልዩ የሚያደርገው ከአዳም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ሰዎችን ያሸነፈውን ሞትንና መውጊያውን ድል በመንሣት እንዲዋጥ ካደረገች በኋላ ነው ወደ ሰማይ የምትሄደው::

ስለዚህ ጠላቶችዋን በመርገጥ በድል የምትመላለስ ቤተ ክርስቲያን በሰው ልጅ ላይ ሰልጥኖ የነበረውን የሞት መውጊያ ድል በመንሳት ድንገት የሚሞተው ሥጋ በማይሞተው ሥጋ ድል በመነሳት ይዋጣል:: በሌላ አገላለፅ የሚነጠቁ ሰዎች ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ስለማይወርስ ሞትን ሞተው አዲሰ ሥጋ ለብሰው አይደለም የሚነጠቁት:: ሞትን ሳያዩ ሞት ሰልጥኖበት የነበረውን ሥጋ ድል በመንሣት በማይሞተው ሥጋ ይዋጣል:: ስለዚህ ይህ የሚጠፋው የማይጠፋውን ይህ የሚሞተው የማይሞተውን በሚለብስበት ጊዜ " ሞት በድል ተዋጠ " ተብሎ የተፃፈው ይፈፀማል:: እንዲሁም ሞት ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ ? ሞት ሆይ ሰውን የምትጎዳበት ኃይል የት ነው ? ተብሎ የተፃፈው ይፈፀማል:: (1ቆሮ 15÷55)

ስለዚህ የመጨረሻዋ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን በእግርዋ በመርገጥ የሞት መንደፊያ የሆነውን ኃጢያት ድል ስለምትነሣ ሞት በእርስዋ ላይ ሥልጣን አይኖረውም:: እንደዚች ዓይነትዋ ቤተ ክርስቲያን የትእዛዝ ድምፅ÷ የመላእክት አለቃ ድምፅ÷ የእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ሲሰማ በቅፅበት ዐይን ሞትን ድል በመንሳት ጌታን በአየር ለመቀበል በዳመና ትነጠቃለች:: ሃሌ ሉያ !! ከዚያም ለዘላለም ከጌታ ጋር ትሆናለች:: (1ተሰ 4÷13-18) አሜን !!!

ለ) የማትነጠቅ ቤተ ክርስቲያን

(ማቴ 24÷40-41 እና ማቴ 25÷1-13) ተመልከቱ:: አማኞች ማወቅ የሚገባቸው ትልቅ ነገር የማትነጠቅ ቤተ ክርስቲያን እንዳለች ነው:: ብዙ ጊዜ ስለ ጌታ መምጣት ቀኑ እንደደረሰ ምልክቶች ረሀብ÷ ቸነፈር÷ ጦርነት ወዘተ እየታዩ እንደሆነ በብዙ የቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ ይነገራሉ:: ነገር ግን ጌታ ሲመጣ ስለሚታዩት ምልክቶች አሥር ሺህ ጊዜ ቢሰበክ ሰዎችን ለንጥቀት የሚያዘጋጅ አይሆንም :: ንጥቀትን የምትጠባበቅ ቤተ ክርስቲያን ጠላቶችዋን ድል ያደረገች በከፍታ ላይ የምትሄድ አክሊልዋን የደፋች የወርቁን በትር በመንካት በጠላቶችዋ መካከል በመግዛት የምትመላለስ ኃጢያትን ድል በመንሣት የምትኖር መሆን አለባት::

የዘመኑ ፍፃሜ ላይ እንዳለን ለሁሉ ግልፅ ከሆነ የቤተ ክርስቲያን እረኞችና አገልጋዮች እያገለገላችሁት ያለው ሕዝብና እናንተም ራሳችሁ እየተማራችሁና እያስተማራችሁ ያላችሁት ጠላትን ሙሉ በሙሉ በመርገጥ ድል የምንነሣበትን የሕያው የእግዚአብሔርን ቃል ነው ? ወይስ የሃይማኖት ካባ የተላበሰ ወደ ድል ላይሆን ወደ ሽንፈት የሚወስድን እርኒት የማያወጣውን ከእውነት የራቀውን ትምህርት ነው ? በቃሉ እውነት ሙሉ በሙሉ በመታደስ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀው ሙላት ውስጥ ለመድረስ የማትጓዝ ቤተ ክርስቲያን በአስቴር መጽሐፍ ውስጥ መጠናቀቅ የማትፈልግ ወደ ሌላ ምዕራፍ በማለፍ መከራንና ስቃይን ለማየት በራስዋ ላይ የወሰነች ናት:: ስመነጠቅም ሆነ ላለመነጠቅም ምርጫው የእንተው ነው:: ይኸውም እምቢ በማለት እንደ ንግሥት አስጢን መሆን ወይም ዋጋ ከፍሎ እንደ ንግሥት አስቴር መሆን:: የቱን ትመርጣለህ?

ማጠቃለያ

መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ !

"መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ ! ድል ለነሣ በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ካለው ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እንዲበላ አደርገዋለሁ::" (ራእ 2÷7)

"መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ ! ድል የነሣ በሁለተኛው ሞት አይጎዳም::" (ራእ 2÷11)

"መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ ! ድል ለነሣ ከተሰወረው መና እሰጠዋለሁ፤ አዲስ ስም የተጻፈበትን ነጭ ድንጋይ እሰጠዋለሁ፤ ከተቀባዩም በቀር ይህን ሌላ ማንም አያውቀውም:: "(ራእ 2÷17)

"ድል ለነሣ÷ በሥራዬም ላይ እስከ መጨረሻ ለፀና በሕዝቦች ላይ ሥልጣን እሰጠዋለሁ፤ በብረትም በትር ይገዛቸዋል፤ እንደ ሸክላ እቃም ቀጥቅጦ ያደቃቸዋል፤ ይህም ሥልጣን እኔ ከአባቴ እንደ ተቀበልሁት ዓይነት ነው፤ የንጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ:: መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ !" (ራእ 2÷26-29)

"ድል የነሣ እንደ እነርሱ ነጭ ልብስ ይለብሳል፤ ስሙን በአባቴና በመላእክቱም ፊት አስታውቅለታለሁ፤ የሕያዋን ስም ከሚመዘገብበት ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስሰውም:: መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ !" (ራእ 3÷5-6)

"ድል የነሣውን በአምላኬ ቤተ መቅደስ አምድ አደርገዋለሁ ከዚያም ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም በእርሱ ለይ እጽፋለሁ፤ ይህቺም ከተማ ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት፤ የእኔንም አዲስ ሰም በእርሱ ላይ እጽፈዋለሁ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ ! " (ራእ 3÷12-13)

" እኔ ድል ነስቼ ከአባቴ ጋር በአባቴ ዙፋን ላይ እንደተቀመጥሁ÷ እንዲሁም ድል የነሣ ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲቀመጥ እደርገዋለሁ:: መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ !"(ራእ 3÷21-22)

መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት
የሚለውን ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ !!

አሜን !!

ስለ መጽሐፉ ማንኛውም አስተያየት ቢኖርዎት በዚህ አድራሻ ይጻፉልን::

PASTOR MEKONNEN MOGES
P.O.BOX 38
BAB-EL-LOUK 11513
CAIRO
EGYPT

TEL (202) 5182516